የቡድን ፀብ መጨረሻ ገጽ 11

አዕምሮን መቆጣጠር ገጽ 14

የመሬት ምልከታ ሳተላይቶች ተልዕኮ ገጽ 18



# አዲስ ዘመን

እንድ

84ኛ ዓመት ቁጥር 060 ጥቅምት 30 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# በሀገራዊ ምክክሩ የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕይታ

ቃልኪዳን አሳዬ

ዜና ሀተታ



በኢትዮጵያ ባህሎች ችግሮች ሲፈጠሩ ተቀራርቦ በመነጋገር ለችግሮቹ መፍትሄ ማበጀት የተለመደ ነው፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ መደበኛ በሆነው የህግ አሰራር ሊፈቱና ሊቋጩ ላልቻሉ ጉዳዮች ምላሽ እንዲያገኙ ለማድረግ በክልል ደረጃ አጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ እያካሄደ ነው። ኮሚሽኑ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የባለድርሻ አካላት አጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር መድረክ በቦንጋ ከተማ አካሂዷል፡፡

በዚህ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ፤ በክልሉ ከሚገኙ 57 ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የተመረጡ የማህበረሰብ ተወካዮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የተቋማትና ማህበራት እንዲሁም የመንግሥት አካላትና የተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰብ ተወካዮች ተሳትፈዋል፡፡ ለመሆኑ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለሀገራዊ የምክክር ሂደቱ ምን ዕይታ አላቸው? እና ተሳትፎአቸውስ እንዴት ይገለጻል? በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የምክክሩ ተሳታፊ ፓርቲ ተወካዮች ሃሳባቸውን ሰጥተውናል፡፡

የካፋ አረንጓዴ ፓርቲ ፕሬዚዳንትና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን አየለ እንደሚናገሩት፤ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከተሳታፊዎች ልየታ


በሀገራዊ ምክክሩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





## ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ በምግብ ራሷን በመቻል ለዓለም ተምሳሌት እንደምትሆን አገልግሎቱ አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በአጭር ጊዜ በምግብ ራሳችንን በመቻል ለዓለም ተምሳሌት ሀገር እንሆናለን ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

አገልግሎቱ ባወጣው መግለጫ፤ አሁን የታዩ አበረታች ውጤቶችን በማስቀጠል ከምግብ እርዳታ ጥገኝነት ተላቀን ራሳችንን መቻል ሉዓላዊነታችንን የተሟላና የፀና ያደርገዋል ብሏል።


ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ወይዘሮ ሰናይት ሰለሞን

## በአርባ ምንጭ ከተማ ለሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቋል


ገጽ 4


## “የባሕር በር ጥያቄን በሸሸነው ቁጥር የሀገራችን ህልውና እየተቃወሰ ይሄዳል”

- አቶ ዳኛው ገብሩ
የታሪክ ምሁር



አስቴር ኤልያስ

አዲስ አበባ፡- የዓለም ሀገሮች 24 ሰዓት ዓይናቸውን የማይነቅሉበትን ቀይ ባሕርን በሸሸነው ቁጥር የሀገራችን ሕልውና እየተቃወሰ ይሔዳል ሲሉ የታሪክ ምሁሩ አቶ ዳኛው ገብሩ አስታወቁ፡፡

አቶ ዳኛው በተለይ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ መውጫ ኮሪደር እፈልጋለሁ ስትል የባህር በር ብቻ ሳይሆን ህልውናዋንም ጭምር ለማስጠበቅ በማሰብ ነው፡፡ ቀይ ባሕር የባህር በር ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ በአንድ አጋጣሚ በስህተት ያጣችውን ቀይ ባሕር በሸሸነው ቁጥር የሀገራችን ህልውና እየተቃወሰ ይሄዳል፡፡

የታሪክ ምሁሩ አቶ ዳኛው ገብሩ እንዳሉት፤ ቀይ ባሕር ጥንትም ቢሆን የተወሰነው ክፍል የኢትዮጵያ ይዞታ እንደነበር ይታወቃል። ቀይ ባሕርን ያጣነው አለአግባብ ነው። ሰዎች የባህር በር ጉዳይን ከሸቀጥ ጋር ቢያመሳስሉትም፤ ይህ በጣም የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው። እኛን ጨምሮ ዓለም በቀይ ባሕር ላይ ያለው ፍላጎት የባህር በር ብቻ ሳይሆን የህልውናም ጉዳይ ጭምር መሆኑን አብራርተዋል፡፡


የባሕር በር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







አቶ ኤሊያስ ከድር

# በኦሮሚያ 250 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ መደበኛ ኮምፖስት እየተመረተ ነው

## - 287 ማዕከላት ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ከ2017 በጀት ዓመት ጀምሮ 250 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ መደበኛ ኮምፖስት እየተመረተ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ 287 ማዕከላት ተገንብተው ወደ ሥራ መግባታቸውም ተገልጿል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊና የተፈጥሮ ሀብትና የምግብ ዋስትና ኃላፊ አቶ ኤሊያስ ከድር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘንድሮ ዓመት 250 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ መደበኛ ኮምፖስት የማምረት ሥራ የተጀመረ ሲሆን እስካሁንም 65 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ማምረት ተችሏል፡፡

እንደ አቶ ኤሊያስ ገለጻ፤ በዘንድሮው ዓመት አራት ሚሊዮን ኩንታል ተፈጥሯዊ ማዳበሪያ (ቨርሚኮምፖስት) ለማምረት በእቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው፡፡

በክልሉ በ2016 በጀት ዓመት በአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር 287 የተፈጥሯዊ ማዳበሪያ ማዕከላት በሁሉም ወረዳዎች ላይ መገንባታቸውን የገለጹት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ጤናማ አፈርን ለትውልዱ ማስተላለፍ በሚያስችል መልኩ ማዕከላቱ ተገንብተዋል ብለዋል፡፡

በክልሉ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሥራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ያለው በመደበኛ ኮምፖስት 250 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ለማምረት ነው፡፡

በኦሮሚያ ክልል ለሚስተዋለው የአፈር ለምነትና ጤንነት መቀነስ የመሬት መሸርሸር፣ የኬሚካል ማዳበሪያ ዋጋ መጨመር እና የአርሶ አደሩ መሬትን የመንከባከብ ባህል እያነሰ መምጣት እንደም ክንያትነት የሚጠቀስ መሆኑን ጠቅሰው፤ የአፈርን ጤናማነትን ለመጠበቅ ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረጉ ሥራዎች በስፋት እየተሰሩ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

በወረዳዎች የተገነቡትን ማዕከላት ተከትሎ ንዑስ ማዕከላት በየቀበሌው ተገንብተው ወደ አገልግሎት እንደሚገቡ የገለጹት አቶ ኤሊያስ፤ አርሶ አደሮች ከባለሙያዎች በሚሰጣቸው ሙያዊ ድጋፍ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

እንደ ኦሮሚያ ክልል አማራጭ የምርት ማሳደጊያ ሥራዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶበት እየተሰራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በተለይም በመደበኛና በቨርሚ ኮምፖስት ላይ በስፋት እየተሰሩ የሚገኙ ሥራዎች አርሶ አደሩን ውጤታማ በማድረግ ላይ እንደሚገኙም ጠቁመዋል፡፡

# የጨርቃጨርቅ ዘርፉን የሚደግፉ ፖሊሲዎችና የመሠረተ ልማት ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የጨርቃጨርቅ ዘርፉን የሚደግፉ ፖሊሲዎችና መሠረተ ልማቶችን የማጠናከር ተግባራት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ከ250 በላይ የፋሽን፣ ጨርቃጨርቅና ቆዳ ኢንዱስትሪዎች የተሳተፉበት ኤግዚቢሽን ትናንት በአዲስ አበባ ተከፍቷል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በመክፈቻ መርሃ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ የጨርቃጨርቅ ዘርፉን የሚደግፉ ፖሊሲዎችና መሠረተ ልማቶችን የማጠናከር ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡




ኤግዚቢሽኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ በጥጥ፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ የተሰማሩ አካላትን ለማገናኘት እድል ይፈጥራል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በአፍሪካም የዘርፉን አሁናዊ ቁመና ለመቃኘት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ተጨባጭ ውጤቶች መመዝገባቸውን ጠቅሰው፣ የጨርቃጨርቅ ዘርፉን የሚደግፉ ፖሊሲዎችና መሠረተ ልማቶችን የማጠናከር ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል።

ተወዳዳሪና ውጤታማ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪውን በቴክኖሎጂ መደገፍና ዓለም አቀፍ የገበያ ትስስር ማሳደግ እንደሚገባ በመግለጽ፤ መድረኩ የእርስ በእርስ ትስስርን ለመፍጠር የሚያስችል ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳሉት ተናግረዋል፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትር ወይዘሮ ሰላማዊት ካሳ በበኩላቸው፤ የባህል ጨርቃጨርቅና ፋሽን ኢንዱስትሪው ለቱሪዝሙ ዘርፍ ያለው አበርክቶ ከፍተኛ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በእጅ የሚሰሩ ጨርቃ ጨርቅ የማምረት ጠንካራ የተከበረ ባህል አላት ያሉት ሚኒስትሯ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የባህል ጨርቃጨርቅ፣ የጥጥ አምራችነት በበርካታ ዓመታት ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ ባህላዊ ጥበብ ነው ብለዋል፡፡

ፋሽን ዲዛይነሮችን፣ ጨርቃጨርቅ አምራቾችን፣ ሻጮችና የፋሽን ኢንዱስትሪው ተሳታፊዎች የዕደ-ጥበብ ስራቸው አስደናቂ መሆኑን ጠቅሰው፤ የአለባበስ ባህል የማህበረሰብን ማንነት፣እምነት፣ባህልና ቦታ ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በተለያዩ መልከዓ ምድሮች የሚኖሩ ከ80 በላይ ብሔረሰቦች እንዳላት በመግለጽ፣እያንዳንዳቸው ወጎች፣ ልማዶች፣ የአኗኗር ዘይቤዎች፣ እምነትና የአለባበስ ዘይቤዎች እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

የባህላዊ አልባሳት ዲዛይነሮች የፈጠራ ችሎታና ጥበብ የብዙዎችን ትኩረት መሳቡን ገልጸው፤ በቱሪዝም ላይ ጉልህ የሆነ አንድምታ ያላቸው በመሆኑ ሊጠበቁና ሊተዋወቁ ከሚገባቸው ቅርሶች መካከል መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ብዙ የቱሪስት መስህቦችና አስደናቂ የቱሪዝም አቅሞች ባለቤት ናት ያሉት ወይዘሮ ሰላማዊት፤ የጨርቃ ጨርቅ ምርት ባህል፣ አልባሳት፣ የጨርቃጨርቅ ምርቶችንና ሀገር በቀል ክህሎቶች ጎብኚዎችን ለመሳብ እድል ይፈጥራል ብለዋል።

በሀገር በቀል የጨርቃ ጨርቅ ምርቶቻችን ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ እንደ የቱሪስት መስህብነት ማስተዋወቅና ለአምራቾች የሚያመጡትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማረጋገጥ እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

ኤግዚቢሽኑ የንግድ ትስስር፣ ምርቶችን ለማስተዋወቅ፣ መስተጋብር ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን በመግለጽ፣ የኢንዱስትሪ ትስስር ለመፍጠር፣በጨርቃ ጨርቅና ፋሽን እሴት ሰንሰለት ላይ አጋርነት ለማጠናከር እድሎችን የሚፈጥር መሆኑን አስረድተዋል፡፡

10ኛው የአፍሪካ ሶርሲንግና ፋሽን ሳምንት ለአምስት ቀናት እንደሚቆይና ከ30 ሀገራት የተውጣጡ ከ250 በላይ የፋሽን የጨርቃጨርቅና ቆዳ ኢንዱስትሪዎች እንደሚሳተፉበት ተገልጿል።

# ተኪ ምርቶችን 60 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ተኪ ምርቶችን ከ40 በመቶ ወደ 60 በመቶ ለማድረስም ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ገለጸ፡፡

ኢንዱስትሪው በሚፈለገው ልክ እንዳያድግ እያደረጉ ያሉ ማነቆዎችን በመፍታት ከአደጉ ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባት እየተሰራ ነው ሲሉ አቶ አብዱልፈታ የሱፍ ተናገሩ፡፡

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዳይሬክተር አቶ አብዱልፈታ የሱፍ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የአምራቾችን ምርት፤ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የሚያስችል የንቅናቄ መድረክ ከትናንት በስቲያ ከባለድርሻ አካላት ሲካሄድ እንደገለጹት፤እስካሁን በተሰራው ውጤታማ ስራ 40 በመቶ የሚሆኑ ከውጭ ይገቡ የነበሩ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ተችሏል፡፡ በመጪዎቹ ስድስት ዓመታት ደግሞ የተኪ ምርቶችን 60 በመቶ ለማድረስም እየተሰራ ነው፡፡




አቶ አብዱልፈታ የሱፍ

ኢንዱስትሪው በሚፈለገው ልክ እንዳያድግ እያደረጉ ያሉ ማነቆዎችን በመፍታት ከአደጉ ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባት እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ፈትቶ የሀገር ብልፅግናን እውን ለማድረግና በዓለም ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባት ሰፊ ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ኢንዱስትሪዎችን በምርቶች ጥራት፣ በምርታማነት፣ በተዳራሽነትና በዋጋ እርስ በርስ ተወዳዳሪ ከመሆን አልፈው ዓለም ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መስራት አስፈላጊ ነው፤ ተወዳዳሪ ለማድረግም ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ምርታማነትን ለማሳደግ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የስራ ባህሎችን ማላመድ፤ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በሙሉ አቅማቸው ጥራት ያለው ምርት እንዲያመርቱ አስፈላጊውን ድጋፍ የማመቻቸት ስራ እየተሰራ ነው ያሉት አቶ አብዱልፈታ፤ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር የተሻለ ዋጋ እንዲያወጡ የማድረግ ስራም ከጅምሩ ውጤት እየተገኘ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በኢንዱስትሪው፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርናው ዘርፍ ላይ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሚሽን በመፍጠር ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ለመገንባትና ብልፅግናን እውን ለማድረግ እየተሰራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

በኢንዱስትሪው ዘርፍ ያለውን ማሽንና የሰው ጉልበት በመጠቀም ጥራት ያለው፤ የተሻለ ዋጋ የሚያወጣ፤ በዓለምም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ለማምረት መስራት አስፈላጊ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና አዳዲስ የስራ ባህሎችን ተግባራዊ ማድረግ ካልተቻለ ተወዳዳሪ ለመሆን ይቅርና በገበያው ላይ ለመቆየት ያዳግታል ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ ኢንዱስትሪዎች በገበያው ላይ ለመቆየት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና ጠንካራ የስራ ባህሎችን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በኢንዱስትሪው፣ በትምህርት፣ በጤና በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ጥራት ያለውና ተወዳዳሪነትን ከፍ የሚያደርግ ስራ መስራት ያስፈልጋል፤ ጥራት ያለው ምርታማነት ከአምራች እስከ ሸማች ያለውን ሰንሰለት ብቻ ሳይሆን ተጠቃሚ የሚያደርገው መንግሥትንም ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ኢንዱስትሪዎች 20 በመቶ ብቻ በማምረት ተወዳዳሪ መሆን አይችሉም፤ ተወዳዳሪ ለመሆን ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም አለባቸው ብለዋል፡፡

# ከተሞች በእቅድ ሊመሩ ይገባል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ከተሞቻችን በእቅድ ሊመሩ ይገባል ሲሉ በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የከተማና መሠረተ ልማት ተመራማሪ አቶ ተፈራ በዬራ አስታወቁ።

ተመራማሪው አቶ ተፈራ በዬራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዋነኛው የሀገራችን ችግር ከተሞች እየቀደሙን እኛ ከኋላ እየተከተልን ስንሄድ ቆይተናል፡፡ከተሞች በህገወጥነት ወደጎንዮሽ እየተስፋፉ ሲሄዱ እየተከተልን ከተማ ስንል ቆይተናል። ከዚህ አካሄድ ተላቀን ዘመን ተሻጋሪና ውብ ከተሞችን ለመፍጠር ቀድሞ አስቦና አቅዶ መምራት ተገቢ ነው።

የከተማና የገጠር ትስስርን በመሰረተ ልማት አስቀድሞ በማቀድ፤ የመሬት አጠቃቀማችን ላይ የትኛው አካባቢ ለየትኛው መዋል እንደሚገባው በመለየትና ቀድሞ በማቀድ የሚመራ ከሆነ በሚፈለገው መልኩ ከተሞችን ማሳደግ ይቻላል ያሉት ተመራማሪው፤ በገጠርና በከተማ ያለው ትስስር በተቀናጀ መልኩ የሚመራ ከሆነ ከተሞቻችን የሚመሩን ሳይሆን እኛ ወደ ምንፈልገው ደረጃ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ከተሞቻችንን መምራትና ማሳደግ የሚያስችል መሆኑን አብራርተዋል።

ከተማ ዞሮ ዞሮ ወደ ገጠር እየሰፋ የሚሄድ በመሆኑ ቀድመን ገጠርን የምንሰራ ከሆነ፤ ሰዎች መንገድ ዳር መጥተው እንዳይሰፍሩ አስቀድሞ በእቅድ መምራት ያስፈልጋል። ከተሞቻችንን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ወደ ምንፈልገው ደረጃ መምራትና ማሳደግ ተገቢ መሆኑን አመላክተዋል።



**አቶ ተፈራ በዬራ**

በሀገራችን እንደ ችግር የሚታየው የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ አለመኖሩ ነው ሲሉም የትኛው አካባቢ ለየትኛው መዋል እንዳለበት የሚያሳይ ለቤት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለንግድ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪና ለአረንጓዴ ስፍራዎች የሚለውን ቀድሞ ማቀድ እና ማስተዳደር እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

አሁን በኮሪደር ልማቱ የሚታዩ ማስተካከያዎች እና ከተማን እንደገና የማደስ ስራዎች ቀድሞ የማቀድ ችግሮች መሆናቸውን አውስተው፤ ከተሞቻችን በእቅድ እና በእቅድ ብቻ እንዲመሩ ማድረግ ከተቻለ በቀጣይ ሊከሰቱ የሚችሉ የመሰረተ ልማት ችግሮችንም አስቀድሞ መፍታት እንደሚቻል አቶ ተፈሪ አስገንዝበዋል።

አረንጓዴ ስፍራዎች የከተማ ሳንባ በመሆናቸው በእቅድ መካተት አለባቸው። ይህ ካልሆነ ሁሉንም አካባቢ በፎቅ የሚሞላ ከሆነ፤ ከተማ ሳንባ የሚያጣ ይሆናል። በመሆኑም ለአረንጓዴ ስፍራዎችም ጭምር አስቀድሞ በማቀድ ከተሞችን በእቅድ መምራት ተገቢ መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ ተፈሪ በሰጡት ምክረ ሀሳብ እንዳመላከቱት፤ የሀገራችን የከተሞች እድገት አስፈላጊውን መሰረተ ልማት አሟልተው በእቅድ እንዲመሩ ከወዲሁ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ላይ መሰራት አለበት።

በሀገራችን የምንፈልገውን የከተማ ደረጃ ለማምጣት የኮሪደር ልማት ተጀምሯል። ይህ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው። አሁን ባለንበት የከተማ ደረጃ መቀጠል አይቻልም። የህዝብ ቁጥሩ እየሰፋና እያደገ ነው። ከፍተኛ ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት አለ። ይህንንም ችግር ለመቀነስ በእያንዳንዱ ከተማ ላይ መስራት ይጠበቅብናል ነው ያሉት።

ለምሳሌ በመዲናዋ የሚታየው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር በእያንዳንዱ ከተማ አስፈላጊ መሰረተ ልማትና ኢኮኖሚያዊ ምቹ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ሚዛናዊ እየሆነ የሚሄድ መሆኑን ገልጸው፤ የተመጣጠነ የከተማ እድገት ለማምጣት የገጠር እና የከተማ ትስስሮችን ማጠናከር ያስፈልጋል ብለዋል።

አሁን ባለው ሁኔታ ቀድመው ባደጉ ከተሞች ኮሪደር ልማት ላይ መስራት ያስፈልጋል። ለዚህም ቀጣይነት ያለው ውይይት አስፈላጊ ነው። የህብረተሰቡን ደጋፊነት ለማስቀጠል ቀደም ሲል የተሰሩት ስራዎች ያስገኙትን ውጤቶች ለህብረተሰቡ የማስገንዘብ ስራ መስራትም ተገቢ መሆኑን አመላክተዋል።



**ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ**

## በመዲናዋ የሚከሰቱ የደንብ መተላለፎች 61 በመቶ ቀንሰዋል

### - በሩብ ዓመቱ አንድ ሺህ 358 ሕገወጥ ግንባታ ላይ ርምጃ ተወስዷል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የሚከሰቱ የደንብ መተላለፎችን በ61 በመቶ መቀነስ መቻሉን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡በሩብ ዓመቱ አንድ ሺህ 358 ሕገወጥ ግንባታ ላይ ርምጃ መውሰዱን ጠቁሟል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው ዓመት ሦስት ወራት ውስጥ የደንብ ጥሰትን በተሰራ የመከላከል እና የመቆጣጠር ሥራ በከተማው የሚታዩ የደንብ ጥሰቶች 61 በመቶ ቀንሰዋል፡፡

ባለስልጣኑ ወንጀልና ደንብ መተላለፍ ከመፈጸማቸው በፊት የስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በስፋት የተሠራና የተሻለ ለውጥ የመጣበት መሆኑን አንስተው፤ በተያዘው ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የባለስልጣኑ የስልጠና እና ግንዛቤ የማስጨበጥ አቅም ማደጉን ገልጸዋል፡፡

ባለስልጣኑ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የደንብ መተላለፍና ተያያዥ ሕገወጥ ተግባራትን የመከታተልና የመቆጣጠር ብሎም እርምጃ የመውሰድ ሥራ በትኩረት መሥራቱንም ጠቅሰዋል፡፡

በዚህም አንድ ሺህ 358 ሕገወጥ ግንባታ፣ 14 ሺህ 300 በላይ ሕገወጥ ንግድ፣ ሁለት ሺህ 722 ሕገወጥ ደረቅ ቆሻሻ እና ፍሻሽ አያያዝ፣ ሦስት ሺህ 156 ሕገወጥ መንገድ አጠቃቀም ላይ እርምጃ ተወስዷል፡፡

እንዲሁም ሁለት ሺህ የሚጠጉ አዋኪ ድርጊቶች እና 40 ሺህ 425 ሕገወጥ ማስታወቂያ ላይ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን አንስተው፤ ስድስት ሺህ 459 ካሬ መሬት ጥበቃ የተደረገ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በሩብ ዓመቱ የተደረገ የመሬት ወረራ አለመኖሩንም ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በሶስት ወራት ውስጥ ብቻ ከተለያዩ የደንብ መተላለፎች ቅጣቶችን ጨምሮ 42 ሚሊዮን 410 ሺህ በላይ ገቢ ብር ማስገባት መቻሉንም ገልጸው፤ ከአለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ34 ሚሊዮን ብር ጭማሪ የታየበት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እንዲሁም የከተማውን የኮሪደር ልማት መሰረተ ልማት የማስጠበቅ ኃላፊነት ከከተማ አስተዳደሩ ተረክቦ ያስተዳደረበት ሩብ ዓመት መሆኑን ሻለቃ ዘሪሁን ገልጸው፤ የከተማዋን ፅዳት ለማስጠበቅ በደንብ ቁጥር 167/2016 መሰረት ጠንካራ የደንብና የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በዚህም በከተማዋ የተሠሩ የኮሪደር ልማት ሥራዎች በመጠበቅ ከተማውን ጽዱና ሰላም በማድረግ ለነዋሪዎቿ ምቹ እንዲሆን ከፍተኛ ሥራ በመሥራት በሩብ ዓመቱ የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገቡን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ባለስልጣኑ በሩብ ዓመቱ በተቋም ግንባታ፣ የስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በስፋት በማከናወን የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የተቻለበት መሆኑን አንስተው፤ የተሰጠውን የደንብ ጥሰትን የመከላከል፣ የመቆጣጠርና እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

# የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ መጠናከር ለኢኮኖሚ መጎልበት ከፍተኛ ሚና አለው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ መጠናከር የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እንዲሁም የፈጠራ ዘርፉን ለማሳደግ ወሳኝ ሚና እንዳለው የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ከዓለም አቀፉ የአዕምሯዊ ንብረት ድርጅት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ሀገር አቀፍ የአዕምሯዊ ንብረት ሳምንት የማጠቃለያ መርሃ ግብር ትናንት ተካሂዷል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ወልዱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ መጠናከር ለሀገሪቱ ኢኮኖሚና ፈጠራ ዘርፍ መጎልበት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ መጠናከር የውጭ ኢንቨስትመንት ከማሳደግ ጎን ለጎን በየዘርፉ ፈጠራ ላይ ለተሰማሩ ዜጎች ተጠቃሚ የሚያደርግና ለፈጠራ እንዲነሳሱ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር የሚያግዝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በተለይ በሀገሪቱ በቅርቡ የተጀመረው ስታርት አፕ ከፍተኛ የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ የሚሻ ነው ያሉት አቶ ወልዱ፤ በዚህ የሚሰማሩ አካላትም የባለቤትነት መብቱ አግኝተው በፍጥነት የፋይናንስ ድጋፍ የሚያገኙበት እድል እየተመቻቸ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ሀገር አቀፍ የአእምሯዊ ንብረት ሳምንት የተዘጋጀው ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ግንዛቤ ለመፍጠር ያለመ መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

እንደ አቶ ወልዱ ገለጻ፤ በሳምንቱ ለፖሊሲ አውጪዎችና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የአነስተኛና መካከለኛ ተቋማት፣ ለምርምር ተቋማትና ለዩኒቨርሲቲዎች የአእምሯዊ ንብረት ምዝገባ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ኢኮኖሚ የገነቡ ሀገራት በአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባቸው ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ናቸው፡፡



**አቶ ወልዱ ይመስል**

አቶ ወልዱ፤ በተፈጥሮ ሀብት ብቻ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ መወዳደር አይቻልም ያሉ ሲሆን፤ የአዕምሯዊ ንብረት በማይዳሰስ ሀብት ውስጥ ሆኖ ከፍተኛ ልዩነት እየፈጠረ ያለ ዘርፍ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ሰፋፊ የሪፎርም ስራዎች እያከናወነ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የሕግ ማሻሻያዎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መፈረም፣የዲጂታል አገልግሎት ማስፋት፣ የግንዛቤ መፍጠር እንዲሁም የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ላይ ይበልጥ ትኩረት ተደርጓል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የዓለም አዕምሯዊ ንብረት ድርጅት አባል ከሆነች በርካታ ዓመታት የተቆጠሩ ቢሆንም የብዙ ስምምነቶች ፈራሚ እንዳልነበረች ጠቅሰው፤ ስምምነቱን ባለመፈረሟ የሀገሪቱ የአዕምሮ ንብረት ውጤቶች በዓለም አቀፍ ዙሪያ ጥበቃ ሳይደረግለት መቆየቱን አስታውሰዋል፡፡

በሳምንቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አጽድቋል ያሉ ሲሆን፤ በቀጣይም የሀገሪቱን አዕምሮ ንብረት ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኙ ስምምነቶች ይፈረማል፡፡

# በአርባ ምንጭ ከተማ ለሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቋል

**አማን ረሽድ**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በአርባ ምንጭ ከተማ ለሚከበረው 19ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል አስፈላጊው ዝግጅት መጠናቀቁን የክልሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሰናይት ሰለሞን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የክልሉ መንግሥት ከፌዴሬሽን ምክር ቤትና ከአርባምንጭ ከተማ አስተዳደር ጋር በመሆን “ሀገራዊ መግባባት ለህብረ ብሔራዊ አንድነት” በሚል መሪ ሃሳብ ኅዳር 29 ቀን 2017 ዓ.ም በአርባምንጭ ከተማ ለሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን አስፈላጊውን ዝግጅት አጠናቋል፡፡

አርባ ምንጭ የተለያዩ ብሔሮች በአብሮነትና በወንድማማችነት ተቻችለው የሚኖሩባት ከተማ ናት ያሉት ኃላፊዋ፤ የከተማው ሕዝብ ለ19ኛ ጊዜ ለሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል እንግዶቹን ለመቀበል ደማቅ ዝግጅት እያደረገ ነው ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት በዓሉን በልዩ ሁኔታ ለማክበር የተለያዩ ኮሚቴዎችን ማቋቋሙን ገልጸው፤ የመሰረተ ልማት፣ የአካባቢ ውበት ሥራ፣ የአደባባይ ማክበሪያ፣ የፓናል ውይይት ማድረጊያ ቦታዎችን፣ የሆቴል ዝግጅትን ጨምሮ የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ መቀየቱን ገልጸዋል፡፡

የከተማውን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ከነዋሪዎች ጋር ውጤታማ ሥራ መሠራቱን የጠቆሙት ወይዘሮ ሰናይት፤ በዚህም የኢንቨስትመንት ተመራጭ ከተማ እንድትሆን ማስቻሉን ገልጸዋል።

በዓሉ በክልሉ መከበሩ የክልሉን የቱሪዝም ጸጋዎች ለማስተዋወቅና ለማልማት ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

ቀደም ሲል አርባ ምንጭ ከተማ የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን እንዳላስተናገደች የሚናገሩት ኃላፊዋ፤ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ለማክበር የባሕል አምባሳደር ሆነው ወደ ከተማዋ የሚመጡ ዜጎችን በበቂ ሁኔታ ለማስተናገድ የሚያስችል ዝግጅት መደረጉን አስረድተዋል።

ከከተማው የሆቴል ባለቤቶች ጋር ውይይትና የግንዛቤ ማስጨበጫ መካሄዱን ጠቅሰው፤ ሁሉም ሆቴሎች እንግዶችን ለመቀበል የሚያስችል ዝግጅት ማድረጋቸውን እንዳሳወቁ ጠቁመዋል።

በከተማዋ የሚከበረውን ሀገር አቀፍ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል ለመታደም የሚመጡ እንግዶችን ከኅዳር 20ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ በዓሉ ዋዜማ ድረስ ባሉ ቀናት ለመቀበል የሚያስችል መርሐ ግብር መዘጋጀቱንም አስታውቀዋል።

ከበዓሉ ጎን ለጎን የከተማዋን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማሳየት ጥረት እንደሚደረግ አመላክተው፤ በአሁኑ ጊዜ ከተማዋ ውጤታማ የኢንቨስትመንትና ቱሪዝም መዳረሻ መሆኗን ተናግረዋል፡፡

በዓሉ በሰላም እንዲከበር የክልሉ ሕዝብ እንዲሁም የአርባ ምንጭ ከተማ ነዋሪዎች የኢትዮጵያዊ ባህልን መሰረት ባደረገ መልኩ እንግዶችን ተቀብለው እንዲያስተናግዱ ወይዘሮ ሰናይት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በሀገራዊ ምክክሩ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጀምሮ ተሳትፈዋል፡፡ እንዲሁም እየተከናወነ በሚገኘው የአጀንዳ የማሰባሰብ ሂደት በክልሉ የሚገኙ 11 የፖለቲካ ፓርቲዎች በመረጧቸው ተወካዮች አማካኝነት ተሳትፈዋል ይላሉ፡፡

የሀገራዊ ምክክር ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን የፖለቲካ ፓርቲዎችና ማናቸውም ቡድኖች ወደጫካ መግባት እንደሌለባቸው ያነሱት አቶ ሰለሞን፤ በሀገሪቱ የሚስተዋሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮችን በውይይትና በንግግር ብቻ መፍታት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ፡፡

የፖለቲካ ፓርቲ ሲባል የሕዝቦችን ችግር በመፍታት የመፍትሄ አካል የሚሆን እንጂ ችግሮችን የሚያባብስ አይደለም፡፡ እነኝህ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሀገርን ወደ አንድነትና ትብብር የሚያመጡ ሃሳቦችን ማፍለቅ ይጠበቅባቸዋል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ይህ የምክክር ሂደት አንዱ ከአንዱ የሚማርበት፣ ሀገርና ሕዝብ የሚጠቅሙ ሃሳቦች በነጻነት የሚገልጹበት አውድ መሆኑን አውስተዋል፡፡

እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ፤ ኮሚሽኑ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሰባስበው ያመጧቸውን አጀንዳዎች የሚያቀርቡበት አውድ ፈጥሯል፡፡ ለዚህም ኮሚሽኑ የቆመለት ዓላማ ከግብ እንዲመታ የጋራ ምክር ቤቱ ከማህበረሰብ ተወካዮች ምልመላ ጀምሮ በርካታ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ይህ የምክክር ሂደት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው በመሆኑ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች እድለኛ መሆናቸውን ያነሱት አቶ ሰለሞን፤ ሌሎች ሀገራት ሀገራዊ ምክክር አድርገው ያልተሳካላቸው የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በመኖሩ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ምክክር ተስፋ የሚጭረው መንግሥት ጣልቃ ከመግባት ይልቅ እራሱን ባለድርሻ አካል አድርጎ እየተሳተፈ መሆኑ ነው ይላሉ፡፡

የቤንች ሸኮ ዞን የኢዜማ ፓርቲ የመንግሥት ክንፍ መሪና የዞኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ክፍሌ ሽፈራው በበኩላቸው፤ ሀገር የአንድ ሰው ወይም የጥቂት ቡድኖች ሳትሆን የሁሉም የጋራ መሆኗን በማንሳት፤ ለዚህም ለደረሰባት ችግር መፍትሄ ሊያመጣ የሚችለው ሁሉም በነጻነት መመካከር ሲችል መሆኑን ይናገራሉ፡፡

እንደ አቶ ክፍሌ ገለጻ፤ የምንመካከረው ሀገራችንን ከችግር በሚያወጡ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የምክክር ሂደቱ ጊዜውን የዋጀ ነው፡፡ የምክክር ሂደቱ ሁሉም ፓርቲዎች ኢትዮጵያን ሰላምና ዴሞክራሲ የሰፈነባት ሀገር ለማድረግ በሚያስችሉ ሃሳቦች ዙሪያ መምከር የሚያስችል ነው፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች በዋናነት የሚፎካከሩት ሃሳባቸውን ለሰፊው ሕዝብ በማቅረብ ነው የሚሉት አቶ ክፍሌ፤ ሀገር የምትለማውና ሰላም የሚሰፍነው በሃሳብ ፍጭቶች እንጂ ጦር በመማዘዝ አይደለም። ከዚህ አኳያም ወደጫካ የገቡ ቡድኖችም የእውነትም ለዜጎቻቸው የሚታገሉ ከሆነ ዜጎች ወደ ተሻለ ለውጥ እንዲመጡ ሃሳቦቻቸውን ይዘው ወደ ኮሚሽኑ መምጣት እንዳለባቸው አንስተዋል፡፡

አቶ ክፍሌ፤ ይህንን አጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር ሂደት ስንመኘው የነበረ ነው፡፡ ሀገሪቱ ከመከፋፈልና ከመለያየት ይልቅ አንድነቷን ማጽናት የምትችለው በኢትዮጵያዊነት ላይ በተመሰረተ የፖለቲካ እሳቤ ስትመራ ነው፡፡ ለዚህም ሁሉም ፓርቲዎች በአንድነት ሲቆሙ የኢትዮጵያን ውድቀት የሚሹ አካላት ሴራቸው እንዲመክን ያደርጋል ነው ያሉት፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የሚሰሩት የሕዝብን ችግር ለመፍታት እስከሆነ ድረስ በጋራ መስራታቸውን አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው የሚገልጹት ደግሞ የቤንች ሸኮ ዞን የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ ፓርቲ ሰብሳቢ ተመስገን ሰለሞን ናቸው፡፡

ኮሚሽኑ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አጀንዳዎችን አሰባስቦ ምላሽ ይሰጣል የሚል እምነት አለን የሚሉት አቶ ተመስገን፤ ፓርቲያቸው አብን በክልሉም ሆነ ከክልሉ ውጪ ኮሚሽኑ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ከተሳታፊዎች ልየታ ጀምሮ ድጋፎችን እያደረገ እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡

አቶ ተመስገን፤ ኮሚሽኑ የምክክር ሂደቱን እያከናወነ የሚገኘው በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ችግር ባለበት ሁኔታ መሆኑን በማንሳት፤ በየቦታው የሚስተዋሉ ግጭቶችን በማስቆም ሰላምን ለማስፈን የምክክር በር ለመክፈት እያደረገ ያለውን ጥረት አጠናክሮ ማስቀጠል እንዳለበት ይገልጻሉ፡፡

# ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በአባቶቻችን ተጠብቆ የቆየ ሉዓላዊነታችን በጀግኖች አርሶ አደሮቻችን፣ በየእርከኑ ባሉ አመራሮች፣ ባለሙያዎችና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ላብ ሉዓላዊነታችን ፀንቶ ይቀጥላል ሲል ገልጾ፤ በአጭር ጊዜ በምግብ ራሳችንን በመቻልም ለዓለም ተምሳሌት ሀገር እንሆናለን ሲል አስታውቋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ወቅቶች በውጭ ወራሪዎችና ጠላቶች የሚቃጡባትን ጥቃቶች በጀግኖች ኢትዮጵያውያን ደምና አጥንት ሉዓላዊነቷ ተከብሮ፣ የነፃነት ተምሳሌት ሆና ኖራለች ያለው አገልግሎቱ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ የቀደምት ስልጣኔዎች ባለቤት፣ በተፈጥሮ ሀብቶች የበለጸገች፣ የሰው ልጅ እና የቡና መገኛ፣ በቅኝ ያልተገዛች የነፃነት ተምሳሌት ናት ብሏል።

መግለጫው እንዳለው፤ በአባቶቻችን ደምና አጥንት ተጠብቆና ተከብሮ የኖረው ሉዓላዊነታችን በላባችን ማፅናት ባለመቻላችን በስንዴ ልመና እና እርዳታ ነፃነታችን ተሸራርፏል፡፡ ሕዝቡን ለመመገብ የሌለውን እጅ የሚጠብቅ ነፃነቱና ሉዓላዊነቱ የተሟላ አይሆንም፡፡

በመሆኑም ይህንን የእርዳታ ጥገኝነት ሁኔታን ለመቀየር፣ “በደም የተጠበቀውን ሉዓላዊነት በላባችን እናፅናል” በሚል ቁርጠኛ አቋምና ርዕይ በምግብ ራስን ለመቻል ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ ተጀምሯል ሲል አስታውሷል፡፡ በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል በልዩ ትኩረት መስራት ከተጀመረ ጊዜ ወዲህ ተጨባጭ ለውጦች እየተመዘገቡ መምጣታቸውን ጠቁሟል።

ቁርጠኝነት በተሞላበት የመንግሥት አቅጣጫን በመከተል ሀገሪቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በስንዴ ምርት ራስን ለመቻል በተደረገው ርብርብ ሀገራችን ስንዴን ከመሸመት ወጥታ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ጭምር ችላለች ብሏል፡፡ በዘርፉ በተመዘገበው ውጤት እውቅናና ሽልማትም ተቸሯታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በምግብ ራስን ለመቻል ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን ገልጿል።

ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር፣ የበጋ ስንዴ፣ የሌማት ትሩፋትና መሰል ስኬታማ ንቅናቄዎች በምግብ ራስን ለመቻል የተደረጉ ጥረቶች ማሳያዎች መሆናቸውን አመላክቷል።

በመስኖ በሚለማ የበጋ ስንዴ ምርት አስደናቂ እመርታ በማስመዝገብ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት በእጅጉ በመቀነስ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ወጪን ማዳን እንደተቻለ ተጠቁሟል።

በአትክልትና ፍራፍሬ ልማትም ራስን ከመቻል ባሻገር እንደ አቮካዶ ያሉ ምርቶችን ለዓለም ገበያ ማቅረብ ጀምረናል ሲል አገልግሎቱ ጠቅሷል።

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

በግብርናው ዘርፍም ቴክኖሎጂና ሌሎች ዘመኑን የዋጁ ግብዓቶችን መጠቀም መጀመራችን ይበልጥ መደላድልን ፈጥሯል፡፡ ለዚህ አመቺ መደላድል ለመፍጠርም የግብርና ቴክኖሎጂዎች ከቀረጥ ነፃ የሚገቡበት የሕግ ማሻሻያ በለውጡ ማግሥት ተደርጓል ብሏል፡፡

እንደ አፈር ማዳበሪያ ያሉ ግብዓቶችም በበርካታ ቢሊዮን ብር የመንግሥት ድጎማ ለአርሶ አደሩ እየቀረቡ ይገኛል፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ ከዓለማችን በግብርና ምርት ፈጣን ለውጥ ካመጡ ሀገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች ሲል አንስቷል።

አሁን የታዩ አበረታች ውጤቶች በማስቀጠል ከምግብ እርዳታ ጥገኝነት ተላቀን ራሳችንን መቻል ሉዓላዊነታችንን የተሟላና የፀና ያደርገዋል ያለው አገልግሎቱ፤ በአባቶቻችን ተጠብቆ የቆየ ሉዓላዊነታችን በጀግኖች አርሶ አደሮቻችን፣ በየእርከኑ ባሉ አመራሮች፣ ባለሙያዎችና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ላብ ሉዓላዊነታችን ፀንቶ ይቀጥላል ሲል አስታውቋል።

ሰሞኑን ኢትዮጵያ ከረሃብ ነፃ ዓለም ጉባኤን የማስተናገዷ አንዱ ምሥጢርም በግብርናው ዘርፍ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ ያስመዘገበችው ስኬት መሆኑን ገልጿል። ጉባኤው በርካታ ተሞክሮዎች የቀረቡበት፣ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ ኢትዮጵያ አብነት ተደርጋ የተወሰደችበት፣ መሰል ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን የማስተናገድ የመሠረተ ልማትና የመስተንግዶ ባህል አቅሟና ልምዷ በእጅጉ ማደጉን ያሳየችበት ሆኖም በስኬት መጠናቀቁን አገልግሎቱ አመላክቷል።

# “የባሕር በር ጥያቄን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ቀይ ባሕር በርካታ ጸጋዎች ያሉት ነው፡፡ ከጤና ጥቅም አንስቶ እስከ ትራንስፖርት ድረስ ባለው አገልግሎቱ ከፍ ያለ ፋይዳ አለው ያሉት አቶ ዳኛው፤ አንደኛ ዓለም ተጠቃሚ የሚሆነው ሸቀጦችን እና ጥሬ ሀብቶችን ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ ለማጓጓዝ ርካሽ የሚባለው የውሃ ላይ ትራንስፖርት ነው፡፡ የዓለም ሸቀጥና ጥሬ ሀብት በውሃ ላይ መጓጓዝ ካለበት ደግሞ ዋናው ማዕከሉ ቀይ ባሕር ነው ብለዋል፡፡

አካባቢው ብዙ ጸጋ ባለበት በእስያ እና በአፍሪካ እንዲሁም በአውሮፓ መካከል ያለ ስትራቴጂክ ቦታ ነው ሲሉ አቶ ዳኛው ገልጸዋል፡፡

የታሪክ ምሁሩ እንደገለጹት፤ ለአፍታም ቢሆን እንኳ ከቀይ ባሕር ላይ ዓይናቸውን መንቀል የማይፈልጉ ሀገሮች ዋና ፍላጎታቸው የባህር በር አይደለም። ለፖለቲካዊ፣ ለኢኮኖሚያዊና ለወታደራዊ አቅም ስትራቴጂክ ቦታ የመፈልግና የመያዝ ጉዳይ ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም ቀይ ባሕር ላይ በመራኮት ላይ ያሉ ሀገሮች የባህር በር የሞላቸው ናቸው፡፡

እኛ ሸቀጦቻችንና ጥሬ ሀብቶቻችን በሰላም በባህሩ ላይ እንዲተላለፉ ባለቤት በመሆን ጥቅማችንን ማስከበር መቻል አለብን ያሉት አቶ ዳኛው፣ ቀይ ባሕርን ከመሸሽ ይልቅ ልንጋፈጥ ያስፈልገናል ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የትኛውም ሀገር እኛን እንዳይተነኩሰን የራሳችንን ኃይል ቀይ ባሕር ላይ መፍጠር መቻል ይጠበቅብናል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ቀይ ባሕር ከባህር በር በዘለለ የኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ ነው፤ በመሆኑም ቀይ ባሕር ላይ መውጫ ኮሪደር ያስፈልገናል በሚል የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የወሰዱት አቋም ወሳኝ ነው፡፡

ስለቀይ ባሕር በር ስናነሳ መሸኮርመም የሚያዋጣ አይሆንም፡፡ ባለቤቶች ነን፤ ያሉት የታሪክ ምሁሩ፤ ጥያቄው ሲነሳ መላ ኢትዮጵያዊ ሊተባበር ይገባል። ምክንያቱም ቀይ ባሕር ላይ ድርሻ የማይኖረን ከሆነ ህልውናችን አደጋ ላይ ይወድቃል ነው ያሉት፡፡

ኢትዮጵያ በታኅሳስ ወር 2016 ዓ.ም ከራስ ገዟ ሱማሌላንድ ጋር የባህር በር ለማግኘት የሚያስችላትን ስምምነት ማካሔዷ የሚታወስ ነው፡፡

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

# በኮሪደር ልማቱ ብዙ ተሠርቷል፤ ብዙ ሊሠራበት ይገባል!

**እስመለአለም**

በከተሞች እየተካሄደ ያለው የኮሪደር ልማት ከተሞች የተሟላ መሰረተ ልማት የተዘረጋባቸው፣ ለነዋሪዎች ለቱሪስቶችና እንግዶችም የተመቻቹ እንዲሆኑ ለማድረግ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ስለመሆኑ በአዲስ አበባ ግንባታቸው የተጠናቀቀ የኮሪደር ልማት አካባቢዎች ጥሩ ማሳያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የአራት ኪሎ መገናኛ፣ የቦሌ መገናኛ፣ የሜክሲኮ ሳር ቤት፣ የሳር ቤት ቄራ ወሎ ሰፈር መንገዶች በሚገባ በመመልከት፣ በሙሉ ልብ በመመልከት ይህን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

አይን ጥሩ ይወዳል፤ እነዚህን አካባቢዎች ተዟዙሮ በመመልከት አይንን ከሚወደው ማገናኘትም መልካም ነው። ይህ ሲሆን የተሰራውን የኮርደር ልማት በሚገባ መቃኘት ይቻላል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርቡ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ‹‹በሀገሪቱ ማየት የሚፈልግ ካለ ሊታይ የሚችል ብዙ ነገር አለ›› ሲሉ እንደገለጹት ሁሉ የኮሪደር ልማቱን በሚገባ መመልከት ይገባል፤ ቀጥሎም ለተከናወኑ ታላላቅ ሥራዎች እውቅና መስጠት ያስፈልጋል።

በእዚህ የኮሪደር ልማት የከተናወኑትን ሁሉ ጠቅሶ እዚህ ለመግለጽ ይቸግራል። በመሬት ውስጥ ከመሬት በላይ፣ በሙብራት፣ በሕንጻ እድሳትና በመሳሰሉት በርካታ የመሰረተ ልማት ሥራዎች ተከናውነዋል። መንገዶቹንና የአረንጓዴ ስፍራዎቹን እንኳ ብንመለከት ብዙ ብዙ ምስክርነታችንን አድናቆታችንን ልንገልጽላቸው የሚገቡ፣ እነዚህን ሁሉ ሥራዎች የወጠኑ፣ የመሩ፣ የሰሩ እጆች ምስጋና ይገባቸዋል ብለን ልንናገርላቸው የሚገቡ ሥራዎች በብዛት ተሠርተዋል።

ጠባብ የነበሩ ጎዳናዎች እንዲሰፉ ተደርገዋል፤ የእግረኞች፣ የአይነስውራን መንገዶች በአግባቡ በሰፊው ተገንብተዋል። በመኪናም ሆነ በእግረኞች መንገድ አጓጉልነት ስንማረር የኖርን ሁሉ እነዚህ መንገዶች በመገንባታቸው እየተካስን ነው፤ ይህን የማይል ካለ ግን ራሱን መለስ ብሎ ማየት ይኖርበታል እላለሁ።

የትራንስፖርት ተርሚናሎች/መጫኛና ማውረጃዎች/፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራዎች፣ በእንዴት እንዴት ያሉ ውድ እና ወሳኝ ቦታዎች ላይ ተገንብተው ማየት በእጅጉ ያስደስታል። ታክሲና አውቶብስ ሲጠብቁ ከመንገድ በወጣ ሌላ ተሽከርካሪ ስንቶች እንደሞቱ፣ አደጋ እንደደረሰባቸው ለሚያውቅ የእነዚህ ተርሚናሎች መገንባት ብቻውን የኮሪደር ልማቱን አስፈላጊነት በሚገባ ያመለክታል። እነዚህ ተርሚናሎች በቀጣይም ቁጥራቸው እንዲበዛ የኮሪደር ልማቱን ከማድነቅ በተጨማሪ መደገፍ ይገባል፡፡

በኮርደር ልማቱ አዲስ አበባ ሌላ መሰረተ ልማትም አግኝታለች። ሀዋሳን፣ ባህር ዳርን አዳማን ብቻ ለብስክሌት የተመቹ ከተሞች በማድረግ፣ አዲስ አበባ ለብስክሌት ያልተፈጠረች ከተማ ተደርጋ ቆይታለች። በከተማዋ ማስፋፊያ አካባቢዎች ከነበረ ጥቂት ሙከራ ውጪ ከተማዋ ለብስክሌት የሚሆን መንገድ አልነበራትም።

የኮሪደር ልማቱ ይህን ቀይሮታል። መሀል አዲስ አበባ፣ ቸርችል ጎዳናን ጨምሮ ብዙ ኪሎ ሜትሮች የሚገመቱ መንገዶች ተገንብተዋል። ከተማዋን ለብስክሌት ያልተፈጠረች ይሉ የነበሩ ሁሉ አሁን በከተማዋ የተገነቡ እነዚህን የብስክሌት መንገዶች ሲመለከቱ ምን ይሉ ይሆን?

በእዚህ የኮሪደር ልማት አዲስ አበባን ለሰሚም ለተመልካችም በሚገርም መልኩ አፍ የሚያስይዙ የብስክሌት/ ሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች/ መንገዶች ባለቤት ማድረግ ተችሏል። አሁን በመንገዶቹ ብስክሌቶች / አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር/ ባይታዩም፣ በቀጣይ በስፋት እንደሚጋልቡባቸው ይጠበቃል።

ከተሞች እንዲሁም መሰረተ ልማቶቻቸው እንዲህ አይደሉም የሚገነቡት፤ ብዙ ታስቦባቸው ነው። መጪው ትውልድ፣ አሁን ያለውም በቀጣይ የሚጠበቀው የምጣኔ ሀብትና ሌሎች ዘርፎች እንቅስቃሴ፣ ወዘተ ጭምር ታሳቢ ይደረጋሉ። እናም እነዚህ ብስክሌቶች አሁን ብስክሌት ሲጋለብባቸው ባይታዩም ከጥቂት ዓመታት በሁዋላ የብስክሌቶች መርመስመሻ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ከተማዋ የቱሪስቶች ምርጫ እንድትሆን ጭምር እየተሰራ እንደመሆኑ ብስክሌቶች ጎዳናዎቹን ለመቀላቀል ብዙም ጊዜ አይወስድባቸውም። ዋናው መሰረተ ልማቱ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መገንባቱ ነው፡፡

የሕዝብ ትራንስፖርት እጥረት ባለበት ከተማ ብስክሌት ጥሩ አማራጭ እንደሚሆን ማንም አይስተውም፤ በርካታ የቱሪስት መዳረሻዎች ባሏት አዲስ አበባ ደግሞ እነዚህን መዳረሻዎች ቢያንስ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት በብስክሌት መጎብኘት ጥሩ አማራጭ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይህም ቀጣይ የአዲስ አበቤዎች ባህል እንደሚሆን ይጠበቃል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሳምንቱ መጨረሻ አንዳንድ መንገዶች በእግርና በሞተር አልባ ተሽከርካሪ መጓዝ እየተለመደ መምጣቱም ይህንኑ ያመላክታል፤ ይህ ጉዳይ በሕዝቡ ዘንድ እንዲሰርጽ ለማድረግ እየተሰራ እንደመሆኑ የእነዚህ መንገዶች ፋይዳ ከፍተኛ ይሆናል፡፡

ማንም ሊገነዘብ እንደሚችለው፣ በመሰረቱም መሰረተ ልማት የሚዘረጋው ለአሁኑ ትውልድ ብቻ አይደለም፤ በእርግጥ የአሁኑን ትውልድ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሰራል። ይህም ቢሆን አቅም አንሶ መሰረተ ልማቱን በስፋትና በሚገባ አለመገንባት ውስጥ ሊገባ ይችል ይሆናል እንጂ መሰረተ ልማቶቹ የሚገነቡት ለቀጣይ ዘመናትም ነው። ቢያንስ አቅም ሲገኝ መገንባት እንዲቻል የመሰረተ ልማት መገንቢያውን ቦታ በአረንጓዴ ስፍራነት እንዲለማ እየተደረገም ቢሆን ተከብሮ መቆየት ይኖርበታል። በአዲስ አበባ አንዳንድ ጎዳናዎች ይህ እየተደረገ ነው።

የዋና ዋና መንገዶች ግንባታ ሲታሰብ በቀን ይህን ያህል ተሽከርካሪዎች ሊያመላለስ፣ ለእዚህ ዓመት ያህል ሊያገለግል፣ በእዚህ በእዚህ ጥራት ሊገነባ ይገባል የሚሉት ይታያሉ። የሚገነቡት ግን የአሁኑን ችግር፣ ሕዝብ አቤት ያለበትን ችግር ታሳቢ በማድረግ ብቻ አይደለም፤ ቀጣይ ጊዜያት ታሳቢ ያደርጋሉ። በተቻለ መጠን ግን መመላለስ፣ ማፍረስ መገንባት ያልበዛበት እንዲሆን ተደርጎ ይገነባል።

የኮሪደር ልማቱ እነዚህ ያነሳሳሁዋቸውን ሁሉ ታሳቢ ያደረገ ነው። ለተሽከርካሪ፣ ለእግረኛ፣ ለአረንጓዴ ስፍራ ሰፊ ቦታ የተሰጠ ከመሆኑ በተጨማሪም አንድ ነገር እንዲቀመጥ አድርጓል። የሕንጻ ግንባታ ከዋና መንገድ ሊኖረው የሚገባው ርቀትም በሚገባ ተቀምጧል። ከዚህ በሁዋላ መንገድ ጥራዝ ላይ ሕንጻ የሚገነባ አይኖርም። ይህ አንዱ የኮሪደር ልማቱ ስኬት ነው።

በመንገድ ግንባታው በኩል አንድ ጉዳይ ላንሳ። በኮርደር ልማቱ አንዳንድ ጎዳናዎች ከተማዋ አይታቸው የማታውቃቸው አይነት ተደርገው ተገንብተዋል። ከመገናኛ ቦሌ መንገድ የኮሪደር ልማት መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው። መንገዱ በአንድ አቅጣጫ ብቻ አምስት መኪኖችን ማስተናገድ የሚችል ተደርጎ የተገነባ ነው። ይህ መሆኑ በዚህ መንገድ ላይ ይታይ የነበረውን የትራፊክ መጨናነቅ ምን ያህል ሊያስተነፍሰው እንደሚችል አስቡት።

የእግረኞች ማቋረጫ ላይ የሚታየውን መጨናነቅ ለማስቀረትም ልማቱ አዲስ ግንባታ ይዞ መጥቷል፤ የእግረኞች የምድር ውስጥ መተላለፊያ። በመገናኛ ቦሌ ጎዳና አንድ መተላለፊያ የተገነባ ሲሆን ሌላ መተላለፊያም በእዚሁ ጎዳና እየተገነባ ነው። ይህ ስራ በአራት ኪሎ አደባባይ ላይም ተከናውኗል። በዚህ ላይ በቀጣይም በትኩረት ሊሰራበት ይገባል።

ከተማዋ የተራበችውን የአረንጓዴ ስፍራም በኮሪደር ልማቱ እንድታገኝ እየተደረገች ስለመሆኑም ግንባታቸው የተጠናቀቀ የኮሪደር ልማቱ የተካሄደባቸው አካባቢዎች በሚገባ ያመላክታሉ። የአረንጓዴ ስፍራ ያሌለው የኮሪደር ልማት የተካሄደበት አካባቢ የለም። አንዳንድ ቦታዎች ደግሞ በጣም ሰፋፊ የአረንጓዴ ስፍራዎች እንዲኖራቸው ተደርጓል። ግንፍሌ እና ቀበናን ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የከተማ ነዋሪ የእግረኛ መንገድ በማጣት በመኪና መንገድ እየሄደ ለአደጋ የተጋለጠባት ከተማ፣ በአንጻሩ ተሽከርካሪውም የተሻለ መንገድ ለመፈለግ ብሎ እግረኛ መንገድ ላይ ሲወጣ መሰረተ ልማት እየሰበረ፣ መንገደኛ እየገጨ የተጠየቀባት፣ መኪናውም ለአደጋ የተጋለጠባት ከተማ፣ የኮሪደር ልማቱ በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች እነዚህ ችግሮች የማይከሰቱበት ሁኔታ እንዲኖር ተደርጓል፡፡

ከተማዋ ለሁሉም ወገን ምቹ መንገድ መገንባቷን ከትናንቱ ጋር አስተያይተን ዛሬ ማድነቃችን አንድ ትልቅ ለውጥ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ መጪው ትውልድ በተደላደለ መልኩ የሚንቀሳቀስበትን ምቹ ሁኔታ በእዚህ ትውልድ መፍጠር መቻሉም ሌላው ተሻጋሪ ስራ የተሰራበት ሁኔታን ያመላክታል።

የኮርደር ልማቱ በከተማ ልማት ስራቸው ተጠቃሽ በሆኑ የአፍሪካም የሩቅ ምስራቅ ሀገሮችም ተሞክሮ እንደተካተተ መገመት ይቻላል። የፌዴራል መንግስትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ኃላፊዎች በእነዚህ ከተሞች ያደረጓቸው ጉብኝቶችን አስመልክቶ ከወጡ መረጃዎች መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው።

ተሞክሮዎቹ ልማቱ በማያዳግም መልኩ እንዲካሄድ ለማድረግ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ እንደ መሆኑ ይህ ተሞክሮ የመቅሰሙ ጉዳይ በቀጣይም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ጉብኝቱ ከመሪዎች ባሻገር በልማቱ የተሰማሩ መሀንዲሶች፣ ተቋራጮች እንዲሁም በከተማ ልማት ባለሙያዎች ጭምር እንዲካሄድ ቢደረግ ስራውን የበለጠ ውጤታማ ሊያደርገው ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል።

ልማቱ ተጀመረ እንጂ አልተጠናቀቀም። በአዲስ አበባ የተካሄደውና እየተካሄደ ያለው የኮሪደር ልማት ያስገኘው ውጤት ሲታሰብ፣ እኔ ግንባታውን ገና ለማሳያ የሚሆን አይነት ነው ብዩ አስባለሁ። ሰፊው የአዲስ አበባ ጉዳይ ገና እንደመሆኑ፣ ክልሎችም ወደ ልማቱ እንደመግባታቸው ሲታይ የኮሪደር ልማቱ ገና ብዙ ሥራዎች እንደሚጠብቁት አስባለሁ፡፡

የከተማ ነዋሪ የእግረኛ መንገድ በማጣት በመኪና መንገድ እየሄደ ለአደጋ የተጋለጠባት ከተማ፣ በአንጻሩ ተሽከርካሪውም የተሻለ መንገድ ለመፈለግ ብሎ እግረኛ መንገድ ላይ ሲወጣ መሰረተ ልማት እየሰበረ፣ መንገደኛ እየገጨ የተጠየቀባት፣ መኪናውም ለአደጋ የተጋለጠባት ከተማ፣ የኮሪደር ልማቱ በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች እነዚህ ችግሮች የማይከሰቱበት ሁኔታ እንዲኖር ተደርጓል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “ኢትዮጵያ የቀይ ባሕርም፤ የዓባይም ባለይዞታና ባለቤት ናት”

\- አቶ ዳኛው ገብሩ ተስፋው የታሪክ ምሁር

አስቴር ኤልያስ



**የዛሬው የዘመን እንግዳችን አቶ ዳኛው ገብሩ ተስፋው ይባላሉ። ተወልደው ያደጉት ደቡብ ጎንደር ጥናፋ ወረዳ፤ ቀደም ሲል ደራ ገብረመስቀል፣ በአሁኑ ወቅት ወሰላ ባሕር በመባል በሚታወቅ ቦታ ነው። እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም የቄስ ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርታቸውን —ሀ“ ብለው ጀምረዋል፡፡**

**የቄስ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁም በአካባቢያቸው ወዳለ መደበኛ ትምህርት ቤት በመግባት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። በወቅቱ የተሻለ ግንዛቤ አዳብረው የመጡ ስለነበረም የተወሱ ክፍሎችን መዝለል የቻሉበት አጋጣሚ ተፈጥሯል።**

**እንግዳችን፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እዛው ደቡብ ጎንደር ውስጥ በሚገኘው በደብረ ታቦር ዳግማዊ ቴዎድሮስ ትምህርት ቤት አጠናቀዋል። በአገር ውስጥ የተለያዩ ኮሌጆች ገብተው የመማር እድልም አግኝተዋል፤ በዚህም በተለያዩ ሙያዎች ለመመረቅ በቅተዋል።**

**ትምህርታቸው በኮሌጅ ትምህርት ብቻ እንዲወሰን ያልፈለጉት አቶ ገብሩ፣ ወደ ባህር ማዶ በመሻገር ሞስኮ እስቴት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በታሪክ ትምህርት በተለይም በማኅበረሰብ ተመራማሪነት ሁለተኛ ዲግሪ አግኝተዋል፡፡**

**ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት፤ እንደዚሁም የሶስት ልጆች አያት የሆኑት እንግዳችን አቶ ዳኛው፣ ዘጠኝ ያህል መጻሕፍትን በመጻፍ ለንባብ አብቅተዋል። ከዘጠኙ መጻሕፋቸው ውስጥ ሁለቱ የሚያጠነጥኑት በትምህርት ላይ ሲሆን፣ የቀሩት ደግሞ በታሪክ እና ፖለቲካ ጉዳይ ላይ ነው፡፡**

**ከጻፏቸው መጻሕፍት —ቀይ ባሕር“ እና —በሰላም ውስጥ ያለ ጦርነት“ በሚል ርዕስ ለንባብ የበቁት በውሃ ፖለቲካ ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው። ሌሎች ያልታተሙ ስራዎች አሏቸው። አብዛኛውን የስራ ጊዜያቸውን ከትምህርት ጋር በተያያዘ ጉዳይ ያሳለፉት አቶ ገብሩ፣ ለትምህርቱ ዘርፍ የተለየ ፍቅር አላቸው።**

**ከዚህ የተነሳ ስራቸውን የጀመሩት በመምህርነት ነው፤ አሁንም የሚሰሩት ከትምህርት ጋር የተያያዘ ስራ ነው። እስከመጨረሻው መስራት የሚፈልጉት ከትምህርት ዘርፍ ጋር ተያያዥነት ያለው ስራ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ማንበብንና መጻፍን አጥብቀው የሚወዱ ናቸው፡፡**

**አዲስ ዘመንም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ የሆኑትን የዘጠኝ መጻሕፍት ደራሲና የታሪክ ምሁሩን አቶ ዳኛው ገብሩን በተለይ ከቀይ ባሕር ቀጣና ጋር አያይዞ የዛሬ እንግዳው አድርጎ አቅርቦላችኋል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በርከት ያሉ መጻሕፍትን ለንባብ አብቅተዋል፤ ይዘታቸው ምን ይመስላል?**

**አቶ ዳኛው፡-** ለንባብ ያበቃኋቸው ዘጠኝ ያህል መጻሕፍትን ናቸው፤ ከእነዚህም መካከል ሁለቱ የሚያጠነጥኑት በትምህርት ላይ ነው። የተቀሩት ደግሞ በታሪክ እና ፖለቲካ ጉዳይ ላይ ነው። ከጻፍኳቸው መጻሕፍት ውስጥ በተለይ ሁለቱ በውሃ ፖለቲካ ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው። እነዚህም መጻህፍት አንዱ “ቀይ ባሕር” በሚል፣ ሁለተኛው “በሰላም ውስጥ ያለ ጦርነት” በሚል ርዕስ ያሳተምኩት ነው። ለጊዜው ለንባብ ያበቃሁት ዘጠኝ መጻሕፍትን ይሁን እንጂ ገና ያልታተሙ ስራዎችም በእጄ ይገኛሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቀይ ባሕር የሚለው መጻፍዎ በቀይ ባሕር ጉዳይ ላይ በስፋት ትንተና የሚያደርግ ነው፤ ስለመጻፉ ማእከላዊ ጭብጥ የተወሰነ ነገር ቢነግሩን?**

**አቶ ዳኛው፡-** ያለንበትን የቀይ ባሕር ቀጣና ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታውን ስንመለከት የዓለምን ትኩረት በእጅጉ የሚስብ ነው። ትኩረት የሳበበት ምክንያት ሁለት ሲሆን፣ ሁለቱም ውሃ ነው። አንደኛው እንደሚታወቀው የዓባይ ወንዝ ነው፤ ዓባይ አብዛኛው የኢትዮጵያ ውሃ ይሁን እንጂ፤ ከስምንት በላይ የሚሆኑ አገሮችን አቆራርጦ የሚሔድ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ረጅም ከሚባሉ ወንዞች ደረጃ የሚመደብ ወንዝ ነው። ከዚህ የተነሳ በርካታ አገሮች በዓባይ ላይ ያተኩራሉ። በዓባይ ላይ ፍላጎቱና ተሳትፎውም አላቸው።

በርካታ ሰው የሚያስተውለው ዓባይ የሚመነጭበትን አገርና አልፎ የሚሔድባቸውን አገሮችን ብቻ ነው፤ ነገር ግን ዓባይን በመዳረሻነት የሚፈልጉ ብዙ አገሮች አሉ። ከግብጽ አልፎ በግብጽ በኩል ሳውዲ አረቢያም አንደኛዋ ፈላጊ ናት። በተመሳሳይ እስራኤልም ውሃውን ትፈልጋለች፤ ሌላው ቀርቶ አልተሳካላቸውም እንጂ ሌሎቹ የሰሜን አፍሪካ አገሮችም እንደ ሊቢያ አይነቶቹ ከዓባይ ውሃ በግብጽ በኩል ቢያገኙ ደስተኞች ናቸው።

ግብጽም ይህን ምኞታቸውን “አሳካላችኋለሁ” ስትል ቃል ስትገባ ቆይታለች፤ በዚህ መልኩ ከራሷም አልፎ በውሀው ጉዳይ ቃል የምትገባ አገር ነች፤ እንዲያውም በአንድ ወቅት ከቀድሞዎቹ አንዱ የሆኑት የግብጽ መሪ፣ ግብጽ ከእስራኤል ጋር በታረቀችበት ወቅት “የዓባይን ንጹህ ውሃ አብረን እንጠጣለን” በሚል ያሰሙት ንግግር የሚታወስ ነው።

የዓባይን ጉዳይ ብዙ አገሮች አፍጥጠው የሚመለከቱት በውሃ ፖለቲካ ውስጥ ቁጥር አንድ አጀንዳ በመሆኑ ነው፤ እኛም በዚህ ቀጣና ውስጥ የምንገኝ አገር ነን። እሱ ብቻ ሳይሆን በአጋጣሚ ሆኖ ኢትዮጵያ በጂኦፖለቲካዊ አቀማመጧ ምክንያት 12 ወንዞቿ ድንበር ተሻጋሪ ናቸው። አገር አቋርጠው ይሄዳሉ። ከዚህ የተነሳም ጎረቤቶቻችን ተጠቃሚዎች ናቸው። በአንጻሩ እኛ ግን ከጎረቤቶቻችን ብዙ ተጠቃሚዎች አይደለንም። በውሃው ምክንያትም ሁሉም ጎረቤቶቻችን በጥርጣሬ ሲያዩን ኖረዋል። ብዙ ሰው ግብጽን ብቻ በጥርጣሬ የመመልከት እንጂ እርሷ ብቻ አይደለችም፡፡

ሁለተኛው የቀይ ባሕር ጉዳይ ነው፤ ቀይ ባሕርን ስናነሳ ለአንድ ደቂቃ እንኳ ቢሆን የዓለም አይን የማያንቀላፋበት ቀጣና መሆኑን እናስተውላለን። በዓለም አቀፍ ደረጃ የዓለም ትኩረትን የሚሹ ወደ አምስት የሚጠጉ ኮሪደሮች አሉ። ከእነዚህ አምስት ትልልቅ ኮሪደሮች መካከል ቀይ ባሕር፣ ከስዊዝ ካናል እስከ ኤደን ባሕረ ሰላጤ ድረስ ያለው ቦታ ብዙ አገሮች በትኩረት የሚመለከቱትና እጅግ በርካታ ጠቀሜታ ያለው ነው።

አካባቢው ለአንድ ወር ወይም ለአንድ ሳምንት ያህል ቢረበሽ ዓለም በኢኮኖሚና በፖለቲካ ጉዳይ ልትመሰቃቀል ትችላለች። ከዚህ ቀደም በአንድ ወቅት በ1960ዎቹ አካባቢ በእስራኤልና በአረብ ግጭት ምክንያት በተፈጠረ አለመግባባት የኢኮኖሚ ቀውስ ተፈጥሮ እንደነበር የሚታወስ ነው። ይህ ቀጣና እኛንም ጨምሮ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሁሉ በትኩረት የሚያየው ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ታድያ ኢትዮጵያ በዚህ ቀጣና ውስጥ የምትገለጸው እንዴት ነው?**

**አቶ ዳኛው፡-** ከዚህ ውስጥ ኢትዮጵያን ስንመለከት በዓባይ ጉዳይ ላይ ትልቅ ተሳትፎ ያላት አገር ናት። በቀይ ባሕርም ደግሞ ተሳትፎ የነበራትና ያላት አገር ናት፡ የሁለቱም የትኩረት አቅጣጫዎች በዋናነት የሚያርፈው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። የቀይ ባሕርም ሆነ የዓባይ ጉዳይ የችግር መነሻውን የሚያደርገው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ የቀይ ባሕርም የዓባይም ባለይዞታና ባለቤት ናት።

እሱ ብቻ ሳይሆን ከሌሎቹ አገሮች ጋር ኢትዮጵያ ስትነጻጸር ተጽዕኖ ልትፈጥር ትችላለች ተብሎ በሌላው የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ግምት የተሰጣት ናት። ምናልባትም ኢትዮጵያ የምስራቅ አፍሪካ አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም ያላት አገር ናት፤ ከዚህ

**እንዳንዶች እንደሚሉት ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠባባቂ ጦር ነው። ክተት ሲባል ከትቶ ኢትዮጵያን ሊያድን የሚችል ሰራዊት ያለው አገር ቢኖር ኢትዮጵያ ናት። ሌሎች አገራት ተጠባባቂ ጦር ያዘጋጃሉ። ኢትዮጵያ ግን ተጠባባቂ ጦር አያስፈልጋትም፤ ክተት ሲባል ብድግ ማለት የሚችልና ከፍተኛ የማሸነፍ ስነ ልቦና ያለው ሕዝብ ባለቤት ናት**

የተነሳ ዓለም በትኩረት የሚመለከታትና አልፎ አልፎ አንዳንዶቹም በስጋት የሚያይዋት ናት።

ሁለተኛው የሚነሳው ነገር ውሃን በተመለከተ ነው። ውሃ የዓለም ፖለቲካ ቁጥር አንድ አጀንዳ ነው። እንዲያውም ብዙ አገሮች እና ብዙ ምሁራን እንደሚሉት፤ ውሃ ከነዳጅም ከወርቅም የሚበልጥ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ሰማያዊ ወርቅ ነው። ሌሎቹ ሀብቶች በሌላ ሊተኩ ይችላሉ፤ ውሃ የማይተካ ሀብት ነው። ምናልባትም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሶስተኛው የዓለም ጦርነት የሚነሳ ከሆነ መነሻው ውሃ ነው ብለው ብዙዎቹ ምሁራን በስጋትነት ይተነብያሉ። ምክንያቱ ደግሞ የዓለም ሕዝብ በውሃ ጥማት ውስጥ መኖሩ ነው።

እንደሚታወቀው ከዓለም ክፍል 71 በመቶ የሚሆነው ውሃ ነው። ከዚህ ውስጥ በቀጥታ ለሰው ልጅና ሕይወት ላለው አካል ጥቅም ላይ መዋል የሚችለው የውሃ መጠን ሶስት ነጥብ አምስት በመቶው ብቻ ነው። 96 ነጥብ አምስት በመቶ የሚሆነው ውሃ በቀጥታ ለአገልግሎት የማይውል ነው። ውሃው እንኳ ቢኖር ለጥቅም ማዋል የሚቻለው በከፍተኛ ወጪ ነው።

ዓለም የሚሻኮተውና የሚራኮተው ሶስት ነጥብ አምስት በመቶው ውሃ ላይ ነው። ከሶስት ነጥብ አምስት በመቶ ከሚሆነው ውሃ ውስጥ ደግሞ 61 በመቶ የሚሆነው ውሃ የሚገኘው ሰው በማይገኝበት ወይም በማይኖርበት በአርክቲክና በአንታርክቲክ ነው። ይህ ማለት ዓለም አፍጥጦ የሚመለከተው ከአንድ ነጥብ አምስት በመቶ ያልበለጠ ድርሻ ባላቸው አገር አቋራጭ ወንዞች ላይ ነው።

ዓለም፤ በውሃ አስተዳደር፣ አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ከፍተኛ የሆነ ቀውስ ውስጥ ነው። በዚህ ምክንያት ደግሞ አገሮች ይጣላሉ፤ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ አገሮች የሚዋጉት በውሃ ምክንያት ነው። ብዙ አገሮች የሰላም እጦታቸው እና የችግር መነሻቸው ውሃ ነው። ምናልባትም ወደፊት የውሃ እጥረቱ በርካታውን የዓለም ሕዝብ ወደ እልቂት ውስጥ ያስገባዋል ተብሎ ይጠበቃል።

ስለዚህ የውሃ ፖለቲካ በዓለም ላይ ትልቅ አጀንዳ ነው። እኛም ያለነው በዚሁ የውሃ ፖለቲካ ውስጥ ነው። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያን ስንመለከት በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ማዕከል የሆነች አገር ናት። የመጀመሪያ የኢትዮጵያን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## “ኢትዮጵያ የቀይ ባሕርም፤ የዓባይም...

ከ7ኛው ገጽ የዞረ

የውጭና የአገር ውስጥ ፖለቲካ ሲወስን የቆየው የዓባይ እና የቀይ ባሕር ጉዳይ ነው።

ኢትዮጵያ ባሳለፈችባቸው በውጭ ፖሊሲ፣ የውጭ ግንኙነት፣ የውስጥ ችግሯና ግጭቷ አባባሽ እና መነሻው የዓባይና የቀይ ባሕር ጉዳይ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ እነዚህን ሀብቶቿን በብዛት ሳትጠቀም የዘለቀች፤ በተለይም ዓባይን ሳትጠቀምበት የቆየች ውሃ በመሆኑ ጠላት ጠርቶባታል። እስካሁንም ድረስ ዓባይ ጠላት ሲጠራብን ቆይቷል፡፡

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ለመጠቀም አቅም አልነበረንም፤ ሲደረግ የነበረውም ሙከራ ጥቂት ነበር። ከዚያ ይልቅ ለወንዛችን ዓባይ ስናዜምለት ቆይተናል። ከዚህ የተነሳ እርሱም ጠላት ሲጠራብን ቆይቷል። ከጠላቶቻችን መካከል ደግሞ ቁጥር አንድ የሆነችው ግብጽ በአገራችን ላይ ችግር ስትፈጥር ዛሬ ላይ የደረሰች አገር ናት። እስካሁንም ድረስ ከግብጽ ጋር የሚያጣላን ጉዳይም ነው፡፡

ሁለተኛው ቀይ ባሕር ነው። ቀይ ባሕር ጥንትም ቢሆን የተወሰነው ክፍል የኢትዮጵያ ይዞታ እንደነበር ይታወቃል። ቀይ ባሕርን ያጣነው አለአግባብ ነው፤ ሰዎች የወደብ ጉዳይን ከሸቀጥ ጋር ቢያመሳስሉትም፤ ይህ በጣም የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው። እኛን ጨምሮ ዓለም በቀይ ባሕር ላይ ያለው ፍላጎት የወደብ ብቻ አይደለም፤ የሕልውናም ጉዳይ ጭምር እንጂ።

እኛ በአሁኑ ወቅት መውጫ ኮሪዶር እንፈልጋለን ስንል የወደብ ጉዳያችን ብቻ ሆኖ ሳይሆን ሕልውናችንንም ጭምር ለማስጠበቅ በማሰብ ነው። ስለዚህ የቀይ ባሕር ጉዳይ የወደብ ጉዳይ ብቻ አይደለም። የዓለም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ ሊፈጠርበት ወይም ደግሞ ላይፈጠርበት የሚችል ወሳኝ ጉዳይ ነው። ይህን ባሕር በስህተት አጥተነው ቆይተናል። ቀይ ባሕርን በሸሸነው ቁጥር የአገራችን ሕልውና እየተቃወሰ ይሄዳል።

ቀይ ባሕርን ቀረብ ብለን ስመለከተው በርካታ ጸጋዎች ያሉት ነው። ከጤና ጥቅም አንስቶ እስከ ትራንስፖርት ድረስ ባለው አገልግሎቱ ከፍ ያለ ፋይዳ አለው። አንደኛ ዓለም ተጠቃሚ የሚሆነው ሸቀጦችን እና ጥሬ ሀብቶችን ከአንዱ ቦታ ወደሌላው ቦታ ለማጓጓዝ ርካሽ የሚባለው የውሃ ላይ ትራንስፖርት ነው። የዓለም ሸቀጥና ጥሬ ሀብት በውሃ ላይ መጓጓዝ ካለበት ደግሞ ዋናው ማዕከሉ ቀይ ባሕር ነው። ምክንያቱም ብዙ ጸጋ ባለበት ኢስያ እና አፍሪካ እንዲሁም በአውሮፓ መካከል ያለ ስትራቴጂክ ቦታ ነው፡፡

እንደሚታወቀው አፍሪካ ሰፊ ጥሬ ሀብት ያለው አህጉር ነው። ኢስያም ተመሳሳይ ነች፣ ሰፊ የሸቀጥ ዝውውር የሚካሔድበት አህጉር ነው። አውሮፓም ተመሳሳይ ነው። ከዚያ ባሻገር ደግሞ ጎልቶ መሳፍርት የሌለው የዓለም ሕዝብ የሚኖርበት ቀጣና ነው፡፡

የአፍሪካና የኢስያ ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ለሸቀጦች ስርጭት ሰፊ ገበያ ያለው አካባቢ ነው። ስለሆነም በንግዱ ስራ አትራፊ መሆን የሚቻለው ዓለም በቀይ ባሕር ላይ ሲጓጓዝ ነው። ነገር ግን ቀይ ባሕር አሁን ያለው በችግር ውስጥ ነው፡፡

ቀይ ባሕር፤ 24 ሰዓት የማያንቀላፉ፣ 24 ሰዓት የሚያንቀላፉና ችግር ጠማቂዎች ያሉበት ቀጣና ነው። እንዲህ ሲባል አንደኛ 24 ሰዓት አፍጥጦ የሚከታተሉ አገሮች አሉ፤ እንደሚስተዋለውም ሁሉም በሚያስብል ደረጃ ተረባርቦ በቀይ ባሕር አካባቢ ከጂቡቲ እስከ ሱማሊያ ድረስ ወደብና የጦር ሰፈር እየተከራየ የተቀመጠበት ሁኔታ አለ።

ይህ ወደብ ፍለጋ አይደለም። ለፖለቲካዊ፣ ለኢኮኖሚያዊና ለወታደራዊ አቅም ስትራቴጂክ ቦታ የመፈለግና የመያዝ ጉዳይ ጭምር ነው። ምክንያቱም ቀይ ባሕር ላይ በመራኮት ላይ ያሉ አገሮች ወደብ የሞላቸው ናቸው። እነዚህ የማያንቀላፉ አገሮች ናቸው። የአፍሪካንና የኢስያን ኢኮኖሚ ሊቀራመቱ፣ ሰፊ የሆነውን የሰው ጉልበት ሊበዘብዙና ገበያውን ሊጠቀሙ የሚችሉ አገሮች 24 ሰዓት አይናቸውን ከቀይ ባሕር ላይ አይነቅሉም፤ አያሸልቡምም።

ሁለተኛው ደግሞ 24 ሰዓት የሚተኙቱ ናቸው፣ እነዚህም የአካባቢው አገሮች ናቸው ማለት ይቻላል። ሱዳን፣ ሱማሊያ፣ የመንም እንቅልፋሞች ናቸው። እነዚህ የአካባቢው አገራት እንቅልፋም ባይሆኑ ኖሮ፤ በተናጠል ጥቅማቸውን ማስከበር ባይችሉም፤ ሕብረት በመፍጠር ጥቅማቸውን ያስከብሩ ነበር።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ እየጠየቀች ያለችው ኅብረት



እንፍጠር ነው። ሰጥቶ በመቀበል መርህ አንድነታችንን በመፍጠር ጥቅማችንን እናስከብር ነው። ይህንን የተለያዩ አገሮች የሚያዩን በስጋት ነው። የአካባቢው አገራት ቀድሞም ቢሆን ደካማ ናቸው፣ በተናጠል መራመዳቸው ደግሞ የሌሎቹ 24 ሰዓት የማይተኙ አገሮች መረማመጃ መሆናቸው አይቀሬ ነው።

ሶስተኛው ደግሞ ቀጣናው ችግር የሚጠመቅበት ነው፤ በአካባቢው ድሮን ጭምር በመጠቀም ዓለምን የሚያስቸግሩ ቀጣናውንም የሚያምሱ አካላት ያሉበት ነው። ከዚህ የተነሳ ቀይ ባሕር ወንበዴዎች ያሉበት አካባቢ በመሆኑ የተጨነቀ ነው። የመን የፈረሰች አገር ናት፤ በተመሳሳይ ሶማሊያም እንደዚያው ናት። ሱዳንም በትርምስ ውስጥ ነች። ከሁሉ በላይ ቀይ ባሕርን ስናነሳ የአረብና የእስራኤል ግጭት ያለበት አካባቢ ነው። ሁለቱ ደግሞ የበረታ አለመግባባት የሚስተዋልባቸው ናቸው።

በዚህ በችግር ውስጥ ባለ ቀጣና የሚገኙ ሀገራት የሕልውና ስጋት አለባቸው። ስለዚህ እኛም ሸቀጦቻችንና ጥሬ ሀብቶቻችን በሰላም በባሕሩ ላይ እንዲተላለፉ ባለቤት በመሆን ጥቅማችን ማስከበር መቻል አለብን። ሁለተኛው ደግሞ የትኛውም አገር እኛን እንዳይተነኩሰን የራሳችንን ኃይል ቀይ ባሕር ላይ መፍጠር መቻል ይጠበቅብናል።

ቀይ ባሕር ከወደብ በዘለለ የኢትዮጵያ የሕልውና ጉዳይ ነው፤ በመሆኑም ቀይ ባሕር ላይ መውጫ ኮሪደር ያስፈልገናል በሚል የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የወሰዱት ወሳኝ አቋም ነው ባይ ነኝ። ይህ ደግሞ ትክክለኛ ነገር ነው። እኔ በመጻሕፌ ውስጥ ስለቀይ ባሕር ስናነሳ መሸኮርመም የለብንም፤ ባለቤቶች ነን፤ ስለሆነም የተወሰደብንም ቀይ ባሕር ይዞታ መመለስ አለበት፤ ጥያቄ ስናነሳ መላ ኢትዮጵያዊ ሊተባበረን ይገባል እንጂ አንዱ ዘርጣጭ አንዱ ደግሞ ተራማጅ ሊሆን አይገባም ብያለሁ። ምክንያቱም ቀይ ባሕር ላይ ድርሻ የማይኖረን ከሆነ ዘለቄታ ያለው ሕልውና ሊኖር አይችልም።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገሮች የሚኖራት ግንኙነት ምን መምሰል ይኖርበታል ይላሉ?**

**አቶ ዳኛው፡-** አገራችን ሰጥቶ በመቀበል መርህና ፍትሐዊ በመሆን ጥቅም የምታምን ናት። ጎረቤቶቻችንም ሰጥቶ መቀበልን መለማመድ አለባቸው። ጎረቤቶቻችን ከእኛ የሚያገኙት ብዙ ነገር አለ። በዚያው ልክ ልናሳጣቸውም የሚያስችለን በርካታ ነገር አለ። ለምሳሌ ሶማሊያን ብንወስድ ሕልውናዋ የተመሰረተው በኢትዮጵያ ወንዞች በዋቤ ሸበሌና በገናሌ ላይ ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ ገና በእነዚህ ወንዞች ላይ ያልተጠቀመች ናት። የሶማሊያ ሕልውና በኢትዮጵያ ወንዞች ላይ የተንጠለጠለ ሆኖ ሳለ፤ ሶማሊያዎች እኛን ባሕር ሊከለክሉን አይገባም። ሰጥቶ መቀበል ካቃታቸው እኛም ያለመስጠት መብታችን የተጠበቀ ነው።

የዓለምም ሆነ የተፈጥሮ ሕግ ሰጥቶ መቀበልን የሚደግፍ ነው። ራስ ገዟ ሶማሌላንድ ለኢትዮጵያ የባሕር በር ሰጠች ተብሎ የዚያን ያህል ማለቃቀስ አያስፈልግም። ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር ስለተዋዋለች የተለያዩ ጠላቶችን በዙሪያቸው እየጠሩ የሚያሰባስቡና ኅብረት የሚፈጥሩበት አካሄድ እራሳቸውን አንቀው እንደመግደል የሚቆጠር መሆኑን ሊረዱ ይገባል።

እንቅስቃሴያቸው የሚጎዳው ኢትዮጵያን ሳይሆን እራሳቸውን ነው። ሶማሊያውያን ከአቅም በላይ እየተንጠራሩ ነው። እስካሁን ድረስ ሕልውናቸውን እያስጠበቀ ያለው የኢትዮጵያ ወታደር ነው። ከዚያ በፊትም ሲያድባሬ “ታላቋን ሱማሊያ መሰርታለሁ” በሚል ሲቃዡ፤ ታናሿን ሶማሊያ ፈጥረው አረፈዋል። አገሪቱ ፈራርሳ ለጎረቤት ጭምር ስጋት የምትሆን ሶማሊያን ትተው አልፈዋል።

ሱማሊያውያን ከቀድሞው መሪያቸው ቅዥት መማር አለባቸው። ጎረቤቶቻችን ደግሞ ሕልውናቸው የተያያዘው ከእኛ ጋር እስከሆነ ድረስ ከእኛ መተባበር ግዴታቸውም ጭምር መሆኑን መረዳት አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ሱማሊያ ከግብጽ ጋር ለመተባበር ሽር ጉድ የማለቷ ነገር ለራሷ ለሱማሊያ አዋጭነቱ የት ድረስ ነው ይላሉ?**

**አቶ ዳኛው፡-** እርግጥ ነው ሶማሊያ ለግብጽ ጥሪ አድርጋለች። ኢትዮጵያና ግብጽ ታሪካዊ ጠላቶች መሆናቸውን የምታውቀው ሶማሊያ፤ ግብጽን ወደምድሯ ጠርታ በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት የመሰንዘር ሀሳቧ እራሷን የመጥፋት ሙከራ መሆኑን መረዳት አለባት።

ሶማሊያን በዘላቂነት ተጠቃሚ የሚያደርጋት ከኢትዮጵያ ጋር የምታደርገው ትብብር ነው። ከኢትዮጵያ የምትጠቀመው ውሃ አለ፤ ጠላት በጠራች ቁጥር ኢትዮጵያ የራሷን ርምጃ እንድትወስድ እየጋበዘቻት ነው ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው ግብጽ ራሷ እስካሁን ድረስ በብቸኝነት የተጠቀመችበት ዓባይም ሆነ በቀይ ባሕር ላይ ያለውን ይዞታ ለመከልከል የምታደርገው ጥረት ከዚህ በኋላ ግብጽን የማያዋጣት አይደለም። ግብጾች አለኝ የሚሉትን ሕልም እኛ ኢትዮጵያውያን የምንቆጥረው እንደ ቅዠት ነው።

ግብጽ ኢትዮጵያን ከአንዴም ሁለት ሶስቴ ሞክራለች፤ ይሁንና አለኝ የምትለውን ሰራዊት አራግፋና ትታ የሮጠች አገር ስለመሆኗ ለማስታወስ እንገደዳለን። እንዲያውም በአንደኛው ወቅት ለሰራዊቱ ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ የተበደረችውን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሏ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር የወደቀች አገር ናት።

ኢትዮጵያን በቀጥታ ጦርነት ገጥማ የተሸነፈች አገር ናት። የግብጽ ታሪክ ብዙ መሳሪያ የመታጠቅ ነው፤ ነገር ግን ስታሸንፍ ተስተውላ አታውቅም። የግብጽ ስነ ልቦና ሁሌም የተሸነፈና ኢኮኖሚዋም ጦርነትን መሸከም የማይችል ነው። በዚህ ጉዳይ ኢትዮጵያን ጦርነት ትገጥማለች ተብሎ አይታሰብም። በጎረቤቶቻችን ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር ደረጃም ሆነ የማሸነፍ ስነ ልቦና ያለው ወታደር ባለቤት የሆነ ከኢትዮጵያ የበለጠ አገር የለም፡፡

አንዳንዶች እንደሚሉት ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠባባቂ ጦር ነው። ክተት ሲባል ከትቶ ኢትዮጵያን ሊያድን የሚችል ሰራዊት ያለው አገር ቢኖር ኢትዮጵያ ናት። ሌሎች አገራት ተጠባባቂ ጦር ያዘጋጃሉ። ኢትዮጵያ ግን ተጠባባቂ ጦር አያስፈልጋትም፤ ክተት ሲባል ብድግ ማለት የሚችልና ከፍተኛ የማሸነፍ ስነ ልቦና ያለው ሕዝብ ባለቤት ናት።

ግብጾች እኛን ሊጎዱ የሚችሉት በውክልና ጦርነት ነው። እስካሁንም በውክልና ጦርነት ሲያተራምሱን ቆይተዋል። ለዚህ ስራቸውም ከፍተኛ በጀት በጅተው የሚንቀሳቀሱ ናቸው። እኛ በውስጥ ጉዳዮቻችን መጠናከርና አገርን ማዳን የግድ የሚለን ነው። አገራችን እንድትድን ከተፈለገ ከውክልና ጦርነት ነጻ መውጣት መቻል አለብን። የውስጥ ጉዳያችንን በውይይትና በንግግር መፍታት ይጠበቅብናል። አገር ከሌለን በአገር ጉዳይ ላይ ልንወያይ አይቻለንም።

አፋሮች፤ “አገሩን የማያውቅ ምድር እየረገጠ ምድርን ይረግማል” የሚል አንድ አባባል አላቸው። ይህ ብቻ አይደለም፤ በምስራቅ አፍሪካ ያለ አንድ የኬንያ ማሳይ የተባለ ታላቅ ጎሳ “ጦርህን ዘቅዝቀህ አታይዝ፤ ምድር ትቆስላለች፤ ምድር ትደማለች” ይላል። እያንዳንዱ አገር ለአገሩ በዚህ ልክ ይቆረቆራል። በሀገራቸው ላይ የውክልና ጦርነት የሚያካሄዱ ኃይሎች የውክልና ጦርነት እንደማይጠቅመን አውቀን ለአገራችን መቆርቆር ይኖርብናል።

**አዲስ ዘመን፡- ለአንደኛው መጻሕፍዎ የሰጡት ርዕስ —በሰላም ውስጥ ያለ ጦርነት“ የሚል ነው፤ ምን ማለት ነው ?**

**አቶ ዳኛው፡-** ሁልጊዜ ከግብጾች ጋር ያለን ሁኔታ በሰላም ውስጥ ያለ ጦርነት ነው። ጦርነት መሳሪያ መማዘዝ ብቻ አይደለም፤ ሰላም መንሳትም ጭምር ነው። ጦርነት ማለት ቃታ መሳብ መጨረሻው ነው። ነገር ግን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሒደትን ሰላም መንሳትም በራሱ ጦርነት ነው። ግብጾች ሁልጊዜ ስለወታደሮቻቸው እንደነገሩን፣ በተለያየ ሁኔታ ተጽዕኖ ሊያሳርፉብን እንደሚችሉ እንዳስታወሱን፣ ያላቸው የጦር መሳሪያ ዘመናዊ መሆኑን እንዳሳወቁን፤ የዓባይን ውሃ ብትነኩ በቀጥታ ጦርነት እንገጥማችኋለን ሲሉ እንደፎከሩብን፤ እስካሁንም እንደዛቱብን እዚህ ደርሰናል። ነገር ግን አሳፍረን ከመለስናቸው በኋላ ፊት ለፊት ሞክረውን አያውቁም፡፡

በጠቀስሸው መጻሕፌ ውስጥ ያልኩት ግብጽን ሲነኩት የሚደማውን ስስ ብልት እናውቀዋለን፤ ከዚህ በኋላ ግን ግብጾች ኢትዮጵያን እንነካለን ካሉ ዓባይ እንደ ከዚህ ቀደሙ የሚያጓጉዘው ንጹህ ውሃ አይኖርም። በርግጥ እኛ መርህ ያደረግነው ፍትሃዊነት ላይ ነው። ከጎረቤቶቻችንም ጋር ቢሆን ጥሩ ነው የምንለው ሰጥቶ የመቀበል መርህን ነው።

በቀጣናው አካባቢ ያሉ አገራት ማንቀላፋታቸውን ትተው በጋራ በመሆን ለጋራ ጥቅም ወደማስከበሩ ቢመጡ መልካም ነው። በቀጣናው ያለነው አገሮች በሙሉ በተናጠል የምናደርገው እንቅስቃሴ ጉልበት የሌለው በመሆኑ በጋራ ለጋራ ጥቅም ወደልማት ፊታችንን ብናዞር የተሻለ ነው፡፡

በተለይ ደግሞ ጎረቤቶቻችን ምንም አይነት ጉልበት የሌላቸው በመሆኑ ከኢትዮጵያ ጋር ቢተባበሩ ትልቅ አቅም መፍጠር እንችላለን ባይ ነኝ። ጉልበት መፍጠር ከቻልን ከየትኛውም ያደገ አገር ጋር በእኩልነት መደራደር እንችላለን። ማንም አገር ወደቀጣናው መጥቶ በአካባቢው ያለውን የትኛውንም አገር ሊረማመድበት አይችልም። በቀይ ባሕርና በዓባይ ወንዝም ሊፈነጭ አይችልም።

ኅብረት ብንፈጥር ተጠቃሚዎች እንጂ ተጎጂዎች አይደለንም። ለዚህ ትብብር ጎረቤቶቻችን መልካም ፈቃዳቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያ ግን በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥም ብትሆን በቀጣናው ተጽዕኖ ፈጣሪነቷ መቀጠሉ አይቀሬ ነው።


**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ በመሆንዎ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ዳኛው፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ቅድሚያ ለሥራ ቦታ የአዕምሮ ጤና!

**አስናቀ ፀጋዬ**




እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ከሆነ የአዕምሮ ጤና ሲባል የራስን ማንነት አውቆ ራስን መምራት መቻል፣ ኃላፊነትን ማወቅና መወጣት፣ ምክንያታዊ ካልሆነ ጭንቀት ነፃ የሆነ ሕይወት መምራት፣ እንዲሁም ካሉበት ማኅበረሰብ ጋር በመግባባት ተግባርን ማከናወንና በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ያለው የኑሮ ዘይቤን የመከተል ሁኔታን ያመለክታል።

ከዚህ በተቃራኒ በአዕምሮ ሕመም ክስተቶች ዙሪያ ሳይንሳዊ የሆነና በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመረኮዘ ትምህርት ያልተስፋፋ በመሆኑ አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ስለ አእምሮ ሕመም ያለው ግንዛቤ በጣም አነስተኛና በባህል ሲወርዱ ሲወራረዱ በመጡ አባባሎች ላይ የተመሰረተ ነው።

የአእምሮ ሕመምን በተመለከተ ከሳይንሳዊ መረጃዎች ውጪ ያሉ የተለመዱ አባባሎች እንደሚያስቀምጡት ልክፍት ወይም ቁጣ ሳይሆን ማንኛውም የሰው አካል እንደሚታመም ሁሉ አእምሮም እንደሚታመም፤ በተለያዩ ምክንያቶችም መረበሽ እንደሚደርስበት የስነ አእምሮ ሕክምና ባለሙያዎች ይገልፃሉ። የአእምሮ ሕመም የእርኩስ መንፈስ ውጤት ሳይሆን እንደማንኛውም የሰውነት ሕመም በተወሰነ የክፍሉ አካል/አንጎል/ መታመም የተነሳ የሚፈጠር መሆኑንም ባለሞያዎች ይጠቁማሉ። ይህም በአብዛኛው እርስ በእርስ ሰላም ማጣት፣ ካለመከባበርና ካለመተባበር ጋር እንደሚያያዝም ያስቀምጣሉ። የአዕምሮ ሕመም እንደማንኛውም የአካል ሕመም በሕክምና ሊድን የሚችል መሆኑንም ያስረዳሉ።

አእምሮን ጤነኛ ወይም ሕመምተኛ ብሎ ለመፈረጅ የሚያስችል መስፈርት ወይም መመዘኛ ግልፅ በሆነና ሁሉም ሰው ሊስማማበት በሚችል መልኩ የተቀመጠ አይደለም። የአንድ ሰው አእምሮ ጤነኛ ወይም ሕመምተኛ ለማለትና ለመገምገም እንደሕብረተሰቡና እንደየአካባቢው ባህልና ግንዛቤ እንደሚወሰን የሕክምና ባለሞያዎች ይናገራሉ። በዚህም የአንድ ሰው አእምሮ ጤነኛ አይደለም ለማለት ከሚያስችሉ አጠቃላይ መስፈርቶች ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከአንድ በላይ ሲኖረው እንደሆነ አብዛኛዎቹ ምሁራን ይስማማሉ።

የግለሰቡ አእምሮ ለራሱ ጭንቀትን የሚፈጥር ከሆነ፣ ለሰላማዊ ማሕበራዊ ግንኙነት ወይም ከሰዎች ጋር በመግባባት ለመኖር እንቅፋት የሚሆን ከሆነ፣ በራሱ ወይም በሌሎች ላይ የአካል፣ የመንፈስ ወይም ማሕበራዊ ቀውስን የሚያስከትል ከሆነ፣ ቤተሰቡን የመንግስት ስራውን፣ ትምህርቱን ወይም ማሕበራዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዳይወጣ ባሕሪው እንቅፋት ከሆነውና የመሳሰሉት ሲከሰቱ ወይም ሲታዩ የግለሰቡ አእምሮ ጤነኛ አይደለም ለማለት ያስችላል።

የዘንድሮው የዓለም አእምሮ ጤና ቀን «በሁሉም የስራ ቦታ ቅድሚያ ለአእምሮ ጤና! ግዜው አሁን ነው!» በሚል መሪ ቃል በጥቅምት ወር መግቢያ ላይ ተከብሯል። ይህ መሪ ቃል ሊመረጥ የቻለውም ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢ አለመኖር ብዙዎችን ለአእምሮ ጤና ችግር እያጋለጠ በመምጣቱ ነው። ባልተመቻቸ፣ ጭቅጭቅ በሞላበት፣ ከልክ ያለፈ ክትትልና ማስጨነቅ በበዛበት የስራ ቦታና አካባቢ መስራት የሰዎችን አእምሮ ጤና ከማወክ ባሻገር አጠቃላይ ሕይወታቸውን በማቃወስ በስራቸው ወይም በምርታማነት ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በእጅጉ እየጎዳ በመምጣቱም ነው።

ይህ እውነታ በኢትዮጵያም የሚንፀባረቅ ሲሆን አሁን ባለው መረጃ መሰረት ከአምስት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ የአእምሮ ታማሚ እንደሆነ ይነገራል። ይህም በተለያዩ መንስኤዎች ምክንያት በኢትዮጵያ የአእምሮ ጤና መታወክ የሚደርስባቸው ሰዎች ቁጥር ምን ያህል እየጨመረ እንደመጣ ይጠቁማል። ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢ አለመኖር ደግሞ ይህን አሃዝ ከፍ ካደረጉ መንስኤዎች ውስጥ በዋናነት ይጠቀሳል። መረጃዎች የሚያሳዩትም ይህንኑ ነው።

አቶ ሳሙኤል ቶሎሳ በአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የተመላላሽ ሕክምና ክፍል ኃላፊ ሲሆኑ በሞያቸው ደግሞ የአእምሮ ጤና ስፔሺያሊስት ሃኪም ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፣ የዓለም አእምሮ ጤና ቀን ሁሌም ጥቅምት 10 ቀን ይከበራል። በኢትዮጵያም ቀኑ ሁሌም በየዓመቱ ይከበራል። ይህም የሆነው የአእምሮ ሕክምና ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው የሕክምና ትምህርት ዘርፍ በመሆኑና በዓለም አቀፍ ደረጃ ፆታ፣ ዘርና ቀለም ሳይለይ ሁሉንም ሰው ሊያም የሚችል በመሆኑ ነው። ለአእምሮ ሕመም የሚያጋልጡ ምክንያቶችም ብቻ ናቸው እንጂ የሚለያዩት ሕመሙ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ይነካል። የአዕምሮ ጤና ድርጅትም ከመስከረም ወር ጀምሮ የአእምሮ ጤና ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች እየተከበረ እንዲያልፍና ጥቅምት 10 ቀን ደግሞ ቀኑን ታሳቢ በማድረግ በየዓመቱ እንዲከበር ያደርጋል።

ቀኑ በየዓመቱ ሲከበር የየቀኑ መሪ ቃል ይኖረዋል። ቀኑን በየዓመቱ ለማክበር ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ በአእምሮ ጤና ዙሪያ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ ለመፍጠር፣ ማሕበረሰቡ ስለ አእምሮ ጤና ችግር ያለውን የተዛባ አመለካከት እንዲያስተካክል ለማድረግ በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያን ጨምሮ ገና ታዳጊ በሆኑ ሀገራት ያለውን የአመለካከት ክፍተት ለመሙላት ነው። ሰዎች ለአእምሮ ጤና ችግር የተሻለና ዘመናዊ የሕክምና አማራጭ መኖራቸውን እንዲያውቁና በቶሎ ሕክምና ቢያገኙ ወደ ጤንነት የሚመለሱበት እድል ሰፊ መሆኑን ለማስገንዘብም ጭምር ነው።

የዘንድሮው የአእምሮ ጤና ቀን መሪ ቃል «በሁሉም የስራ ቦታ ቅድሚያ ለአእምሮ ጤና! ግዜው አሁን ነው!» የሚል ሲሆን ከዚህ ቀደም ከነበረው መሪ ቃል የሚለየው በስራ ቦታ ላይ የሚፈጠሩ የአእምሮ ሕመሞችን ትኩረት ለመስጠትና ለመከላከል ያለመ ነው። በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ምክንያቶች በስራ ቦታዎች ላይ የሚከሰቱ የአእምሮ ሕመሞች አሉ። በኢትዮጵያም በተለያዩ ምክንያቶች በስራ ቦታ ላይ የሚያጋጥሙ የአእምሮ ጤና ችግሮች እየጨመሩ መጥተዋል። በተለይ የስራ ሰዓት አመቺ አለመሆንና አስተማማኝ የስራ ላይ ደህንነት ያለመኖር ከአጋላጭ ምክንያቶች ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው።

ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች ታዳጊ ሀገራት ላይ በዋናነት የሚስተዋለው ለስራ ላይ ደህንነት በቂ ትኩረት ያለመስጠት ነው። ከሌሎች የጤና ጉዳዮች አኳያ ለአእምሮ ጤና የሚሰጠው ትኩረት በተመሳሳይ ዝቅተኛ በመሆኑ ሰዎች በስራቸው ውጤታማ ያለመሆንና ምርታማነታቸውም ዝቅ የማለት ሁኔታዎች ይታያሉ። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ወጣትና አምራች ኃይል ነው። ስለዚህ ይህ አምራች ኃይል በተለያዩ ምክንያቶች ለአእምሮ ጤና ችግር ሊጋለጡ ይችላሉ።

ወጣቱ ለተለያዩ ሱሶች ተጋላጭ እንደመሆኑ ሱስ አምጪ ነገሮችን ተጠቅሞ ወደ ስራ ሊገባ ይችላል። ስራ እየሰራ በሱሱ ምክንያት ስራውን አቋርጦ ለመጠቀም ይሄዳል። የተለመዱ የአእምሮ ጤና ችግሮች የሚስተዋልበት የእድሜ ክልልም ነው ወጣትነት። ወጣትነት ቤተሰብ የሚመሰረትበት እድሜ ነው። ሌሎችን የሚደግፉበት እድሜ ነው። አለመግባባቶች የሚፈጠሩበት፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር በቀላሉ ተግባብቶ ለመኖርም አስቸጋሪ የሆነና ያለመብሰል የሚታይበት እድሜ እንደመሆኑ በነዚህ ምክንያቶች ወጣቶች ለአእምሮ ሕመሞች ሊጋለጡ ይችላሉ።

ቀላል የሚባሉ የአእምሮ ሕመሞች በግዜ ካልታከሙና እያደጉ ከሄዱ ከባድ የአእምሮ ሕመም ሊያስከትሉ ይችላሉ። አንድ ሰው የአእምሮ ሕመም ከገጠመው ደግሞ ራሱንና ቤተሰቡን ሊረዳ አይችልም። በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያደርሳቸው ጉዳቶችም ይኖራሉ። ስለዚህ የአእምሮ ሕመም ድምር ውጤቱ ቤተሰብን ያፈርሳል። ማህበረሰብን ይጎዳል። እንደሀገርም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና ይፈጥራል። ከዚህ አኳያ ስራ ቦታ ላይ የሚኖሩ የስነ አእምሮ ደህንነቶችንና ጤንነቶችን እንዲከበሩ ማድረግ የሁሉም ኃላፊነት ይሆናል። ይህን በማድረግ ረገድ ደግሞ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ማስተካከል ያስፈልጋል።

የሰራተኞችን አካላዊና ስነ አእምሯዊ ደህንነታቸውን እንዲሁም ማህበራዊ ሕይወታቸውን መጠበቅ ለአእምሮ ጤናና ለምርታማነት ብሎም ለሀገርም እድገት በጣም ወሳኝ ነው። ከዚህ አንፃር የዘንድሮው የዓለም አእምሮ ቀን በሁሉም ስራ ቦታ ላይ ቅድሚያ ለአእምሮ ጤና ትኩረት እንዲያደርግ ታሳቢ በማድረግ ተከብሯል።

አቶ ሳሙኤል እንደሚናገሩት፣ የአእምሮ ሕመምን በሚመለከት በተለያዩ ሀገራት ላይ የተሰሩ ጥናቶች አሉ። ለምሳሌ በታዳጊ ሀገራት ከ10 እስከ 15 ከመቶ የሚሆነው በስራ ላይ ያለ የሕብረተሰብ ክፍል ለተለመደ የአእምሮ ሕመሞች ተጋላጭ ነው። ከዚህ ውስጥ ደግሞ አብዛኛዎቹ ማለትም ከ90 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ሕክምና አያገኙም። ይህም በስራቸው ውጤታማ አይሆኑም ማለት ነው።

ለምሳሌ በድብርት ወይም በመከፋት ስሜት ውስጥ ያለ ሰራተኛ ስራውን በተሟላ ትኩረት ለመስራት ይቸግረዋል። የተሰጠውን ስራ ሌሎች ሰራተኞች በሚጨርሱበት ሰዓት ሳይሆን በጣም ዘግይቶ ሊጨርስ ይችላል። ስራ ላይ ሊያንቀላፋ ይችላል። በስራ ገበታው ላይ በሰዓት ላይገኝ ይችላል። እነዚህ ምልክቶች ሰራተኛው ከዚህ በፊት የነበረው ብቃት እየቀነሰ ስለመምጣቱ ጠቋሚ ናቸው። ስለዚህ እነዚህን ምልክቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት በስራ ቦታ ለአእምሮ ሕመም አጋላጭ የሆኑ ምክንያቶችን መለየትና የስራ አካባቢን ምቹና ደህንቱ የተጠበቀ ማድረግ ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ የስራ አካባቢ በሚታሰበው ልክ ለአካላዊና ስነ አእምሯዊ ጤንነት የተመቻቸ አይደለም። ሰዎች የሚሰሩባቸው የስራ ቦታዎች የተጨናነቁና ብዙ ረብሻ ያለባቸው ናቸው። ቢሮ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችም ከሚቀመጡባቸው ወንበሮች ጀምሮ ስራውን ለማስኬድ ጥቅም ላይ የሚውሉ መሳሪያዎች አመቺ አይደሉም። በፋብሪካዎች አካባቢ ደግሞ የደህንት መሳሪያዎች በአግባቡ ያለመጠቀም፣ ረጅም ሰዓት መስራት፣ ለሰሩበት ስራ ተመጣጣኝ ክፍያ ያለማግኘት፣ ወጣ ብለው የሚዝናኑባቸው ፕሮግራሞች በስራ ተቋማት ውስጥ ያለመኖር በስነልቦና፣ ማህበራዊና አእምሮ ጤናቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል።

ስለዚህ በቁጥራዊ መረጃዎች ላይ እንደሀገር ጥናት አልተደረገም እንጂ ምቹና ደህንነቱ ባልተጠበቀ የስራ አካባቢ ላይ በመስራት ምክንያት የሚከሰቱ የአእምሮ ሕመሞች ከፍተኛ እንደሆኑ ይገመታል። ለአእምሮ ሕመም ብቻ ሳይሆን ከዚህ ሕመም ውጪ በሆኑ ሌሎች አካላዊ ሕመሞች ሲጋለጡም ይታያል። ሰዎች ሳያማቸው ሀኪም ቤት የመሄድ፣ የሕክምና እረፍት መፈለግ፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከስራ ገበታ ላይ መቅረት፣ እረፍት ማብዛትና እነዚህን መሰል ነገሮችን የማብዛት ሁኔታዎች አሉ። አዕምሮ ሕመም ኖሮባቸውም ከስራ መቅረት፣ የሕክምና እርዳታ መፈለግና አዕምሯቸውን እንዳመማቸው መናገሩ ደግሞ ልገለል እችላለው የሚል ፍራቻ ሊያድርባቸው ይችላል፡፡

በኢትዮጵያ በርካታ ሰራተኞች የአእምሮ ሕክምና ክትትል ያደርጋሉ። በግዜ ለመታከም የመጡት ተሽሏቸው በስራቸው ውጤታማ ሆነዋል። ነገር ግን አብዛኛው ሰራተኛ በተለይም በሚሰራበት ቦታ ላይ በአእምሮ ሕመም ውስጥ ያለ ሰው የአእምሮ ሕክምና አገልግሎት አያገኝም። በሌላ አባባል በአእምሮ ሕክምና ተደራሽ አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ተቋማት ላይ በሚደረገው ድጋፍ አካላዊ ሕመም አለብኝ ብለው የሚመጡ አብዛኛዎቹ ሰራተኞች የሕመማቸው መነሻ አእምሮና ስነ ልቦናዊ ነው። ስለዚህ ሰዎች የሕክምና አማራጮችን ለማግኘት በተለያዩ አቅጣጫዎች ይሄዳሉ። ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የአእምሮ ታማሚዎች ከዘመናዊው ሕክምና ውጪ ወደ እምነት ተቋማት ሊሄዱ ይችላሉ። ወደ ተለያዩ ሱሶች ውስጥ የሚገቡና ሱስን ለአእምሮ ሕመም እንደመደበቂያ የሚጠቀሙም አሉ።

አቶ ሳሙኤል እንደሚገልፁት፣ የስራ ላይ የአእምሮ ሕመም ጉዳይ እንደሀገር ብዙ ባለድርሻ አካላትን ይመለከታል። አንዱና ትልቁ ነገር የፖሊስ ማሕቀፍ ሊኖር ይገባል። ስራ ቦታዎች ደረጃቸውን የጠበቁና ለሰራተኞች አመቺ ብሎም ደህንታቸው የተጠበቀ ሊሆኑ ይገባል። ሰራተኞች የሚያርፉባቸውና የሚዝናኑባቸው ቦታዎች መኖር አለባቸው። አሁን ላይ በተለይ በአንዳንድ ትላልቅ የመንግስት ተቋማት ላይ የስራ አካባቢን የመቀየር፣ የማሳመርና ፅዱ የማድረግ ሁኔታ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ሁሉም ተቋማት ላይ በዚህ ልክ መሰራት አለበት። ከዚህ ባለፈ ሰራተኞች በቂ እረፍት ሊያገኙ ይገባል። በአሰሪና ሰራተኛ እንዲሁም በአመራርና ፈፃሚዎች መካከልም ጤናማና መልካም የስራ ግንኙነት ሊኖር ይገባል።

በሌላ በኩል የማኔጅመንት ስርዓትንም መቀየር ያስፈልጋል። በጣም ጥብቅ ክትትል፣ በሆነው ባልሆነው የት ገባህ የት ወጣህ የሚል አሰራር ካለ ሰራተኛውን ለፍርሃት በመዳረግ ለአእምሮ ጤና ችግር ስለሚያጋልጠው እንዲህ አይነቱ የማኔጅመንት ስርዓት መቀየር ይኖርበታል። በዚህ ጥብቅና ክትትል በበዛበት የማኔጅመንት ስርዓት ምክንያት ሰራተኞች የሚሰሩበትን ተቋም እንዲጠሉና ደሞዝ ቀንሰውም ቢሆን ሌላ የተሻለ ተቋም እንዲገቡ ያስገድዳቸዋል። ስለዚህ ሰራተኞች በተቋም ውስጥ ደስተኛ ሆነው እንዲቆዩ የስነ አእምሯዊና ስነ ልቦናዊ ጤንነታቸው እንዲጠበቅ የሚያደርጉ አሰራሮችን ዘርግቶ መተግበር ያስፈልጋል።

በተቋማት ውስጥ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን መገንባት፣ ቤተ መፅሃፍቶችን ማዘጋጀት እንዲሁም ሰራተኞች ማህበራዊ መስተጋብራቸውን የሚያጠናክሩበት ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ከከተማ ወጣ ብለው እንዲዝናኑና አእምሯቸውን እንዲያድሱ ማድረግ በጣም ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ስለዚህ እንደየተቋማት ባህሪ የሰራተኞችን ስነ ልቦናዊና ስነ አእምሯዊ ጤና የሚጠብቁ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## በ60 ሺ ብር መነሻ ባለ 60 ሚሊዮን ብር ካፒታል

ኃይሉ ሣሕለድንግል

በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን ሶዶ ከተማ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝነት በመደራጀት የአንድ ቀን ጫጩቶችን በመረከብ የ45 ቀን ጫጩቶችን ለተጠቃሚዎች ያቀርባል። የዶሮ ስጋና እንቁላል ልማትም ያካሂዳል።

በወተት ሀብት ልማት ላይም የተሠማራው ድርጅቱ በቀን ከ150 እስከ 200 ሊትር ወተት ያመርታል። የወተት ምርቱን ለአካባቢው ማኅበረሰብና ድርጅቶች ያቀርባል። በግብርናው ዘርፍ ላይ የሚሠራ የትምህርት ተቋም ከፍቶ በዲፕሎማ ደረጃ ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል።

ድርጅቱ ‹‹ኤግዞደስ ፋርም› ይባላል፤ የዚህ ድርጅት ባለቤቶች አምስት ቢሆኑም ድርጅቱ እንዲመሠረት ባለራዕይ በመሆን በ2002 ዓ.ም ከወላይታ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ የእንስሳት ሕክምና ትምህርት ክፍልን የተቀላቀሉ 24 ተማሪዎች ይጠቀሳሉ። ተማሪዎቹ ዩኒቨርሲቲውን ከተቀላቀሉበት ጊዜ አንስቶ በዚያ እድሜያቸው ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ስለሚሠሩት ሥራ በእጅጉ ያስቡ ነበር። በወቅቱ ሕጋዊ ባይሆንም ማኅበር በመመሥረት በዚህ ጉዳይ ላይ በትኩረት መክረዋል።

የ«ኤግዞደስ ፋርም» ዋና ሥራ አስኪያጅና ከድርጅቱ ባለቤቶች አንዱ የሆኑት ተሻለ አላጋው (ዶ/ር) እንዳሉት፤ ተማሪዎቹ በተማሪነታቸው ይህን ያህል እንዲያስቡ ያደረጋቸው ደግሞ በወቅቱ የመንግሥት ሥራ ማግኘት ከባድ መሆኑና ሥራ አጥነት መንሰራፋቱ ነው።

ተማሪዎቹ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ተመርቀው ቢመለሱ በአንድ ወረዳ ሊያስፈልግ የሚችለው የእንስሳት ሐኪም አንድ ብቻ እንደነበር ታያቸው። በወላይታ ዞን ያሉት ወረዳዎች ደግሞ 12 ብቻ መሆናቸውን ሲያስቡ ነገሮች ይበልጥ ዳገት ሆኑባቸው። እነሱ እስከሚመረቁ ድረስ በእንስሳት ሕክምና የሚመረቁ ተማሪዎች በርካታ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲያስቡም ያሉትም ቦታዎች ሊያዙ እንደሚችሉ ተገነዘቡ፡፡

ይህ ሁሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተመርቀው የመንግሥት ሥራ ሊይዙ እንደማይችሉ አስቀድመው እንዲገነዘቡ አደረጋቸው። ሊሆን በሚችለው ሁሉ ተስፋ አልቆረጡም፤ ትምህርቱ ሰፊ መሆኑና በሙያቸው ብዙ ሊሠሩ እንደሚችሉ ሲገነዘቡ ስለመውጫው ወደ መምከር ገቡ።

በጉዳዩ ላይ ለሦስት ዓመታት የመከሩት ተማሪዎቹ፣ ሰፊ ውይይታቸው ሥራ የመፍጠር ሀሳባቸው አሸናፊ መሆኑን አሳወቃቸው። ከሦስተኛ ዓመታቸው አንስተው እያንዳንዱ ተማሪ ለተለያዩ ጉዳዮች ከቤተሰቡ ከሚላክለት ገንዘብ የተወሰነውን በየወሩ ማዋጣት ጀመረ፤ በየእረፍት ወቅታቸውም የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን በግልም፣ በቡድንም በማካሄድ ገንዘብ ማጠራቀሙን ተያያዙት። እንደ ክረምት ወቅት ባሉት እረፍቶቻቸውም በጎች እየገዙ በማሞከትና በመሸጥ ገቢያቸውን ማሳደጋቸውን ቀጠሉ። በሦስት ዓመት ውስጥ ያጠራቀሙት ገንዘብ ተመርቀው ሲወጡ ባለ 60 ሺ ብር አደረጋቸው፡፡

በግላቸው ሥራ በመፍጠር ለመሥራት ሲመክሩ የነበሩት እነዚያ ባለራዕዮች ቁጥራቸው በተለያየ ምክንያት ቀንሶ ሁለት ብቻ ቀርተው ነበር፤ ዓላማቸው ግን እንደጸና ቀጠለ። የተቀሩት ሁለት ተማሪዎች እንደተመረቁ በትምህርት ቤት ያገኙትን የእንስሳት ሕክምና እውቀት፣ ሥራን በራስ በመፍጠር የመሥራት ሀሳብንና ያጠራቀሙትን ገንዘብ ምርኩዛቸው አድርገው ራዕያቸውን ለማሳካት ታጥቀው ተነሱ።

በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው በተመረቁበት ሙያ ለመሥራት እንደሚፈልጉ ለሚመለከተው የሶዶ ከተማ የመንግሥት አካል አመለከቱ። ሁለቱ ነባር የማኅበሩ አባላት ሌሎች ሦስት አባላትን አካተው ኢንተርፕራይዛቸውን ኤግዞደስ ፋርምን መሠረቱ።

ማመልከቻቸውም ተቀባይነት አገኘ። ይህ ሁሉ አቅማቸው፣ ጽኑ ፍላጎታቸውና ተነሳሽነታቸው፣ ብዙ ወጣቶች ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ሥራ ሲፈልጉ ዓመታትን በሚያሳልፉበት ሁኔታ እነሱ በዚህ ልክ ዝግጁ ሆነው መገኘታቸው የመንግሥት አካላትን በእጅጉ ማስገረሙን የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ያስታውሳሉ። በአንድ ወር ውስጥም ሕጋዊ ማኅበር ሆነው፣ ብድርና ቦታም ተመቻችቶላቸው ሥራ መጀመራቸውን ተሻለ (ዶ/ር) ይናገራሉ።

እነ ተሻለ (ዶ/ር) መጀመሪያ ላይ ከብት ማድለብ ላይ ፕሮፖዛል ሠርተው ቢያቀርቡም፣ ይህን ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልገው ገንዘብ ወደ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር ሆነ፤ መንግሥት ደግሞ ይህን የሚያመቻቸው አልሆነም። “ለማኅበር እኛ የምንሰጠው ከ50 እስከ 100 ሺ ብር ብቻ ነው፤ በዛ ቢባል ደግሞ 150 ሺ ብር ነው›› የሚል ምላሽ ተሰጣቸው።

እናም የከብት ማድለቡን ፕሮጀክት መቀየር የግድ ሆነ፤ የከተማዋ ከንቲባ በአንድ ቀን ጫጩት ልማት እንዲሠሩ ያቀረቡላቸውን ሀሳብ ተቀብለው፣ የ300 ሺ ብር ብድር ተመቻችቶላቸውና ቦታም ተሰጥቷቸው በቀጥታ ወደ አንድ ቀን ጫጩት ልማቱ ገቡ።

ይህን ሥራ አሀዱ ብለው ሲጀምሩ አራት ሺ ጫጩቶችን ማስገባታቸውን ተሻለ(ዶ/ር) ጠቅሰው፣ በሂደት ከዚህም በላይ ጫጩቶችን ለኅብረተሰቡ እያቀረብን ነው፤ እኛም እንቁላል ጣይ ዶሮ እንዲሁም የሥጋ ዶሮ ማሳደግ ውስጥ ገባን ሲሉ ያብራራሉ።

የሚረከቧቸውን የአንድ ቀን ጫጩቶች በ45 ቀናቸው ላይ ይሸጣሉ። በአራት ሺ ጫጩት የተጀመረው ሥራ በአሁኑ ወቅት በአንድ ዙር እስከ 18 ሺ ጫጩት ወደ ማስገባት መሸጋገሩንም ይገልጻሉ።

በጫጩት፣ በእንቁላልና የሥጋ ዶሮ ልማቱ የሚገኘውን ምርት ከአካባቢዎቻቸውም አልፈው በተለያዩ ክልሎች በሰፊው እያቀረቡ እንደሚገኙም ጠቅሰው፣ በክልል ደረጃም በ45 ቀን ዶሮ አቅራቢነት ድርጅታቸው እንደሚታወቅም ገልጸዋል።

“የኤግዞደስ ፋርም” ልማት በዚህ ላይ ብቻ እንዳልተወሰነም ነው ዶክተር ተሻለ የሚናገሩት። የዶሮ ኩስም ሌላው የድርጅቱ ገቢ ማስገኛ በመሆን እያገለገለ መሆኑን ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል የሚሠሩበት ቦታ ሰፋ ያለ መሆኑ ወደ ወተት ላም እርባታና ወተት ልማት እንዲገቡ አደረጋቸው። በሁለት ላሞች ሥራውን የመጀመረው ድርጅቱ፣ አሁን የላሞቹ ብዛት ወደ ሠላሳ ደርሷል። በዚህም ሰፊ የወተት ምርት እያገኙ ምርቱንም ለአካባቢው ማኅበረሰብ ያቀርባሉ።

በእንስሳት መኖ እና መገልገያ መሣሪያዎችን ለአካባቢው ከብትና ዶሮ አርቢዎች እያሰራጩ መሆናቸውንም ዶክተር ተሻለ ተናግረዋል። “እኛም ወደ ዶሮ ልማቱ ስንገባ በመኖ አቅርቦት ሳቢያ በጣም እንቸገር ነበር” ሲሉ አስታውሰው፣ አሁን ከፋብሪካዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ከቢሾፍቱና አዲስ አበባ መኖውን በመረከብ ወደ አካባቢው እንደሚያመጡም ገልጸዋል።

የተቀናጀ ሥራ /ኢንቴግሬትድ የሆነ ነገር/ መሠራት እንዳለበት በማመንም ድርጅቱ ከፈራው ሀብትና ከሙያቸው ባሕሪ በመነሳት በ2014 ዓ.ም የክልሉን ትምህርት ዘርፍ የሚመራውን አካል ፈቃድ በመጠየቅ በግብርና ዘርፍ ላይ የሚሠራ ተቋም አቋቁመዋል። ተቋሙ እስከ ስምንት የሚደርሱ የትምህርት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ሰፊ የትምህርትና ሥልጠና ሥራ በዲፕሎማ ደረጃ/ከደረጃ አንድ እስከ አራት የሚባለውን/እየሰጠ ይገኛል። በ2016 ዓ.ም ወደ 312 የሚደርሱ ተማሪዎችንም አስመርቋል።

አሁንም ተማሪዎችን በመቀበል የቀለም ትምህርቱን ከተግባራዊ ትምህርት ጋር በማቀናጀት ተማሪዎች እውቀትና ክህሎት እንዲጨብጡ ለማድረግ እንደሚሠራም ተሻለ (ዶ/ር) ጠቅሰዋል።

ከሌማት ትሩፋት ጋር የተያያዘ ሥራ በመሥራታቸው እጅግ በጣም መጠቀማቸውንም ተሻለ (ዶ/ር) አስታውቀዋል። በሌማት ትሩፋቱ መንግሥት ባስቀመጠው አሠራር መሠረት ኅብረተሰቡም ዶሮ ማርባት ይኖርበታል፤ ይህም የዶሮ ምርታችንን ቀጥታ ለመሸጥ የበለጠ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮልናል፤ ሁኔታው የበለጠ እንድናመርት የሚያበረታታም ሆኖልናል ብለዋል።

ቀደም ሲል ዶሮ አርብተን በአርባ አምስት ቀናት ለመሸጥ ብዙ አካባቢዎች ላይ መንቀሳቀስ የግድ ይለን ነበር ያሉት ተሻለ (ዶ/ር)፣ የሌማት ትሩፋቱ ምርቶቻችንን ፍለጋ የኛን ክልል ጨምሮ በርካቶች ደጃችን እንዲመጡ እያደረጋቸው ነው ሲሉም አስታውቀዋል።

እነ ተሻለ (ዶ/ር)ወደ ቀድሞ ከብት ወደ ማድለብ ሕልማቸው መመለስ በጣም ይፈልጋሉ። “እኛ



እያካሄድናቸው በሚገኙ የልማት ሥራዎች ታዳጊዎች ነን። ገና በጣም መሠረታዊ ነገሮች ያስፈልጉናል። የወተት ልማት ማካሄድ ወይም ላሞችን ማርባት ብቻውን በቂ አይደለም፤ ለእነሱ የሚሆኑ ግብዓቶች ያስፈልጉናል፤ ያፈራነውን ሀብት በአጠቃላይ በዚያ ላይ እናውላለን›› ሲሉ አብራርተዋል።

በዶሮ ልማቱም እንዲሁ ለዘርፉ ሥራ የሚያስፈልጉትን በሙሉ ማሟላት ያስፈልጋል ሲሉ ጠቅሰው፣ ለትምህርት ቤቱም እንዲሁ ሰፋፊ ላቦራቶሪዎችን፣ የመማሪያ ክፍሎችን ለማደራጀት በራሳችን ገንዘብ ስለምንሠራ ያለንን ሀብት በሙሉ በቀጥታ መሬት ላይ የዋለ ነው። በመሆኑም ከብት የማድለብ ሥራውን አሁን ለማካሄድ እንቸገራለን፤ ፍላጎቱ ግን አለን ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የከብት ማድለብ ሥራ ለራሱ ብቻ የሚሆን ሰፊ ቦታና ግብዓቶችን ይፈልጋል። ያለን ቦታ ግን ውስን ነው። የማድለቡ ሥራ የማስፋፊያ ሥራ ማካሄድን ይፈልጋል። ለራሱ ፕላን በማድረግ ለመሥራት እየታሰበ ይገኛል።

በዶሮና በወተት ልማት አንዱ ይገጥማል ተብሎ የሚታሰበው ችግር የገበያ እጦት እንደሆነ ይገለጻል:: “ኤግዞደስ ፋርም” ግን የገበያ ችግር ጨርሶ የለበትም። እስካሁን ጫጩት ማምረት ውስጥ አልገቡም፤ ከሚያመርቱት እየገዙ ለ45 ቀናት እያቆየ ለገበያ እያቀረቡ ናቸው። “ጫጩት ጠይቀን ለማግኘት ረጅም ጊዜ እንጠብቃለን። እኛ በፈለግን ጊዜ ጫጩት ብናገኝ ኖሮ ብዙ ርቀት በተጓዝን ነበር ሲሉም ያመለክታሉ፡፡.

“ኤግዞደስ ፋርም” በወተት ሀብት ልማቱም በጣም እየተሠራ ስለመሆኑ ይገልጻሉ። እሱንም ለማስፋፋት ታስቦ በወተት ልማት ላይ ከሚሠራ ከኔዘርላንድ ከመጣ ድርጅት ጋር እየሠራ ነው።

“ድርጅቱ ከመንግሥት ፈቃድ የምታገኙበት ሁኔታ ካለ ለወተት ማቀነባበር የሚያስፈልጉ ማሽኖችንና ግብዓቶችን በቀጥታ እንልክላችኋለን ብለውናል” ያሉት ተሻለ (ዶ/ር)፣ በዚህ አይነት መንገድ ከሠራችሁ በጣም ጥሩ ደረጃ መድረስ ትችላላችሁ ሲሉም የድርጅቱ ባለሙያዎች ገልጸውልናል›› ብለዋል።

“ኤግዞደስ ፋርም” በቀን ከ150 እስከ 200 ሊትር ወተት ያመርታል። ምርቱም በአካባቢው ኅብረተሰብ በእጅጉ ይፈለጋል፤ አሁን ለትምህርት ቤት ምግባ ማቅረብ ጀምረናል፤ የኛ ምርት ብቻ ለዚህ በቂ አይደለም። ትላልቅ ሆቴሎችም ከኛ ለመግዛት ይፈልጋሉ፤ በዚህ ላይ የኛም ካፍቴሪያ ወተት ይወስዳል›› ሲሉም ወተቱ ምን ያህል ተፈላጊ ስለመሆኑ ገልጸዋል።

በአካባቢው ብቻ ከፍተኛ የወተት ፍላጎት መኖሩን በመረዳታቸውም ጠቅሰው፣ ወደ 50 የሚሆኑ ተጨማሪ የወተት ላሞችን ለማስገባት መታቀዱንና ለዚህም ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን ተናግረዋል።

እነ ተሻለ (ዶ/ር) ያሰቡትን ከማሳካት አልፈው በሁሉም የድርጅቱ ተቋማት በጊዜያዊና በቋሚ ሥራ ለ100 የማያንሱ ሠራተኞች የሥራ ዕድል ከፍተዋል። የድርጅታቸውም አጠቃላይ ካፒታል ከ60 ሺ ብር ተነስቶ ከ60 ሚሊዮን በላይ ደርሷል።

‹‹ኤግዞደስ ፋርም›› በእንሳሳት ዘርፍ የጀመራቸውን ሥራዎች ከጥናት ምርምር ጋር በማያያዝ ትልቅ ኢንስትቲዩት የመሆን ራዕይ አለው ሲሉ ጠቅሰው፣ ግብርናው ዘርፍ ላይ ዓለም ዛሬ ከደረሰበት ደረጃ ላይ መድረስ እንፈልጋለን ብለዋል።

በሀገሪቱ ደረጃውን የጠበቀ የግብርና ተቋም በመገንባት የግብርውን ዘርፍ አመራረት በቴክኖሎጂ ለመደገፍ አቅማቸውን አሟጠው ለመሥራት ድርጅቱ ሀሳቡ እንዳለው ጠቅሰው፣ ሰፊ ምርት በማምረት የኅብረተሰቡን ፍላጎት ማርካትም ራዕያቸው መሆኑን አስታውቀዋል።

ድርጅቱ ማኅበራዊ ኃላፊነትን እየተወጣ መሆኑንም ይገልጻሉ። ምርቶቻችን ማኅበረሰቡን ማዕከል ያደረጉ መሆናቸው፤ የፈጠርናቸው የሥራ ዕድሎች፣ በኮሌጁ በሚሰጡ አጫጭር ሥልጠናዎች ዜጎች በቀጥታ በዚህ ዘርፍ እንዲሠማሩ ለማድረግ እየተከናወነ ያለው ተግባር ማኅበራዊ ኃላፊነትን መወጣት ናቸው ብለን እናስባለን ሲሉ ተሻለ (ዶ/ር) አስታውቀዋል።

ይህን ሁሉ የተሠራው ብዙ ተግዳሮቶች ታልፈው መሆኑን ጠቅሰው፣ የከብት ማድለብ ፕሮጀክታቸው ከፋይናንስ እጥረት ጋር ተያይዞ አለመሳካቱ አንድ ችግር እንደሆነ አመልክተዋል። ችግሩ ሌላ አማራጭ እንዲያዩ እንዳደረጋቸው አስታውቀዋል።

ለሥራችን ፈተና የሆነብን ትልቁ ችግር የካፒታል እጥረት ነው የሚሉት የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ይህን ችግር ለመፍታት ብድር መመቻቸት አለበት ይላሉ። አሁን ድርጅቱ የሚሠራበት ቦታ ሕጋዊ ሆኖ በስማቸው አለመመዝገቡንም እንደ ችግር ጠቅሰው፣ በርካታ ሀብት ያፈሰስንበት ይህ ቦታ በማኅበሩ ስም ቢሆን ሰፊ ገንዘብ አግኝተን ትልቅ ሥራ መሥራት እንችል ነበር ብለዋል።

ለዚህም ፕሮፖዛል አዘጋጅተን ከኛ የሚጠበቀውን ሁሉ አድርገን ከ2014ዓ.ም ጀምሮ ለመንግሥት አመልክተናል፤ ችግሩ እንዲፈታ በተደጋጋሚ መንግሥትንም ጠይቀናል ይላሉ። ይህ ችግር ቢፈታ ድርጅቱ ሰፊ የኢንቨስትመንት ራዕይ እንዳለውም አስታውቀዋል። ከ500 በላይ ሠራተኛ የመቅጠር አቅም አለን ሲሉም ጠቁመዋል፡፡

ለኢንተርፕራይዞች የተሰጠ ቦታ መልሶ የሚወሰድ ስለመሆኑ አሠራር እንዳለ ጠቅሰው፣ እኛ ግን በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ አይደለንም፤ ትልቅ ድርጅት ነን፤ እኛ እነዚህ ሼዶች በሚተዳደሩበት መንገድ መተዳደር የለብንም፤ ሲሉ አመልክተዋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

# የቡድን ፀብ መጨረሻ

ምሕረት ሞገስ



የካ አባዶ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ባለአራት እና ባለስድስት ወለል ፎቅ የጋራ መኖሪያ ቤት በስፋት ተገንብቶ ሰዎች መኖር ከጀመሩ ዘጠኝ ዓመታት ተቆጥረዋል። በአንድ ሕንፃ ላይ አነስተኛው አርባ ከፍተኛው ስልሳ አካባቢ የሚደርሱ ቤተሰቦች የሚኖሩባቸው ሲሆኑ፤ የአካባቢው ማህበረሰብ በእጅጉ መላመድ ጀምሯል። የኢትዮጵያውያን እሴት የሆነው የሴት፣ የወንድ እና የእራት እድር ከማቋቋም በተጨማሪ እቁብ በማሰባሰብ ወላጆች እርስ በእርስ መደጋገፍ እና መመካከር ጀምረዋል።

ወጣቶች በአካባቢው ባሉ ሜዳዎች እና ጎዳናዎች ላይ ስፖርት መስራት፣ ሩጫ መወዳደር እና በቡድን እግር ኳስ መጫወት እንደልማድ መቆጠር ከጀመረ ሰነባብተዋል። በተለይ አመሻሽ ከ11 ሰዓት በኋላ የየካ አባዶ ሜዳዎች በማንኛውም ቀን በሰው የተሞሉ ናቸው። ገሚሱ እግር ኳስ ሲጫወት ገሚሱ ቮሊቦል ይጫወታል። የተቀረው ተመልካች ሆኖ ቆሞ እያፏጨ ያጨበጭባል። በዛ መሃል ደግሞ አንዳንዴ ፀብ ይነሳል።

የወጣቶቹ ፀብ እጅግ አስፈሪ ነው። እስከ ሕይወት መጠፋፋትም ይዘልቃል። ሜዳ ላይ በድጋፍ ወይም በሌላ ምክንያት የተነሳ ፀብ ውሎ አድሮ እየከረረ ይቀጥላል። ቡድን ሰርተው አንዱ ሌላውን እያስፈራራ አንዱ ሌላውን እየመታ እና እየጎዳ ወላጆች ጭንቀት ውስጥ መግባት ጀምረዋል። ወጣቶቹ ስለቀጣይ ሕይወታቸው የሚያስቡ አይመስሉም። ስለት ይዘው እስከ መወጋጋት ይደርሳሉ። ምክንያታችሁን ግልፁ ሲባሉ ደግሞ ውሃ የሚያነሳ መልስ አይሰጡም።

የአንደኛው ቡድን ወጣት የሌላኛውን ቡድን ወጣት ካገኘ አሳዶ ይመታል፤ ከቀላል እስከ ከባድ ጉዳት ያስከትላል። ብቻ ወጣቶቹ እርስ በእርስ እየተጋጩ መግቢያ መውጫ አጡ። በግጭቱ ውስጥ በዋነኛነት ቀንደኛ ሆነው ከሚሳተፉት መካከል ሃይመን ጄላን አንዱ ነው። ሃይመን ድርድር አያውቅም፤ የተቃራኒ ቡድን አባላትን ካገኘ ከመደባደብ ወደ ኋላ አይልም። በተለይ እርሱ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ በተቃራኒ ጎራ ከተሰለፉ ቡድኖች አንዱን ወጣት ካገኙ መግቢያ እስኪያጣ አሳደው ይጎዳሉ።

## ወንድምየው

ፍቃዱ ወንድሙ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ቦታው የካ አባዶ ኮንደሚኒየም አካባቢ አገር ሰላም ብሎ ከገደራ አካባቢ በእግሩ ቀስ እያለ ወደ መስቀለኛ ሲራመድ፤ ከሩቅ እርሱን እና የእርሱን ጓደኞች አሳድደው በመያዝ የሚደበድቡ ወጣቶች ማለትም እነ ሃይመንን ተመለከተ። እነርሱ ሳያዩት በተለምዶ ‘ጂ ሰቨን’ ተብለው ከሚጠሩት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሕንፃዎች ጀርባ መሮጥ ጀመረ። ሲሮጥ የተመለከቱት እነ ሃይመን አሳደዱት፤ እግሬ አውጪኝ ብሎ የ’ጂ ሰቨን’ ሕንፃዎችን ጨርሶ ዋናውን አስፓልት ከተሻገረ በኋላ ሮጦ ደህንነቱ ወደ ሚጠበቅበት ባለ አራት ፎቅ ሕንፃ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ወደ ቤቱ አቅራቢያ ደረሰ። ከሚኖርበት ቤት ሕንፃ ጀርባ ዞሮ አጎንብሶ ተነፈሰ።

ከጓሮ ቁጭ ያለውን ቃልአብን ሲያይ፤ ቁና ቁና እየተነፈሰ እነ ሃይመን አግኝተውት እንደነበረ እና ከሩቅ አይቷቸው ሲሮጥ እንዳሳደዱት እንዲሁም ሮጦ እንዳመለጠ ነገረው። ይህ መሳደድ እና ማሳደድ ለወጣቶቹ ከፍተኛ ጭንቀት ፈጥሮባቸዋል። ነገሩ ይበልጥ እየተጋጋለ ቢቀጥልም፤ ገላጋይ ጠፍቶ ወጣቱ ወጥቶ ለመግባት ተቸግሯል። ቃልአብ እና ፍቃዱ ከሚኖሩበት ሕንፃ ጀርባ ባለ የአትክልት ቦታ ላይ ቁጭ ብለው እየተነጋገሩ ቆዩ። ስለሁኔታው ፍቃዱ እያስረዳ ቃልአብ ደግሞ እያዳመጠ፤ ሌላኛው ጓደኛቸው ልክ እንደፍቃዱ እያለከለከ ደረሰ፡፡

ጓደኛየው ፍቃዱን ሲያይ ‹‹ወንድምህን እነ ሃይመን ይዘውታል፡፡›› አለው፤ ፍቃዱ ሮጦ ያመለጣቸው ወጣቶች፤ ወንድሙን እንደያዙ ሲሰማ፤ ፍቃዱ ዘሎ ቤት ገብቶ የሽንኩርት ቢላዋ ይዞ ሊጋፈጣቸው ወጣ። ከቤቱ ወጥቶ ጓደኛውን ወንድሙን የት አካባቢ እንደያዙት ጠየቀ። መስቀለኛ አካባቢ ላይ መሆናቸውን ሲነግረው፤ ወደ ግራ ሄዶ በአስፓልቱ ቁልቁል እየተንደረደረ መሮጥ ጀመረ። ጓደኞቹ እየሮጡ ተከተሉት።

እርሱ ከእነ ቤተሰቦቹ የሚኖረው ባለ አራት ፎቅ ሕንፃዎች ባሉበት አካባቢ ነው። ከ’ጂ ሰቨን’ ልጆች ጋር ፍፁም መጣጣም አልቻሉም። አሁን ደግሞ ወንድሙን እያጠቁበት መሆኑ አንሰፈሰፈው፤ በመጨረሻም ሚያዚያ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ወጣቶቹ ከባድ ስህተት ፈፀሙ። ስህተት ተብሎ የሚታለፍ ሳይሆን ሕይወታቸውን የሚያበላሽ ወንጀል ውስጥ ገቡ። ቀድሞ እንደቀልድ የታየው ጠብ መዘዙ የወጣቶቹን ሕይወት እስከ ወዲያኛው የሚበጠብጥ ሆነ።

## ደብዳቢው ቡድን

ሃይመን የሚንቀሳቀሰው ታጅቦ ነው። በዘመኑ የጋንጊስተር ቡድን ለመመስረት ያሰበ ይመስላል። በአጀብ ሲንቀሳቀስ እየጠራ የፈለገውን ይሰድባል፤ የፈለገውን በጥፊ አልያም በእርግጫ ካልሆነም ማንበርከክን እንደመብቱ ቆጥሮታል። ዕድሜያቸው ከፍ ያሉ ወጣቶች እርሱን የማይደግፉ ከሆነ ወዮላቸው፤ ጠብቆ ብቻውን ሳይሆን ሌሎችንም አደራጅቶ ያጠቃቸዋል።

አንድ ወጣት ካየ ተያይዞ ማሯሯጥን እንደጀግንነት የሚቆጥረው ተግባር ነው። መስቀለኛ ጋር ሆኖ ከሩቅ ኬላው ጋር ያዩትን ፍቃዱ አሯሩጠው ሊይዙት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። በገዛ መንደራቸው ተሹለክልኮ አመለጣቸው። እርሱ እንዳመለጣቸው እርግጠኛ ሆነው በአስፓልቱ ቁልቁል ወደ መስቀለኛ ሲራመዱ ያመለጣቸው የፍቃዱ ወንድሙ ወንድም የሆነውን ሙሉቀን ወንድሙን አገኙት። እርሱ እንደፍቃዱ ቀድሞ አላያቸውም። ሮጦ ማምለጥ አልቻለም።

ሃይመን ጄላን ሙሉቀንን ሲያይ በደስታ እና በድል አድራጊነት ፈገግ አለ። ወንድምህ ቢያመልጠንም አንተን አገኘንህ ብሎ በመጠጋት ሆዱን በቦክስ መታው፤ ይህንን ከሩቅ ሲመለከት የነበረው የወንድማማቾቹ ጓደኛ እየሮጠ ወደ እነ ፍቃዱ ቤት አቀና። ሕንፃው አካባቢ ፍቃዱን ቢመለከትም ማግኘት አልቻለም። ከጀርባ ሲያይ ቃልአብ እና ፍቃዱ ተቀምጠዋል። ሙሉቀንን እንደያዙት ሲነግራቸው፤ ፍቃዱ ተነስቶ ቆመ።

## የሞት ፅዋ

ከላይ ቁልቁል እየተንደረደረ እነ ሃይመን አቅራቢያ የደረሰው ፍቃዱ ወንድሙ ሙሉቀን ወድቆ ሲያይ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ። አንድ ማህፀን የተጋራው የውድ ወንድሙ ደም ሲፈስ ሲያይ የሚሆነውን አጣ። ሙሉቀን መሬት ላይ ወድቆ ደሙ እየፈሰሰ የነበረው ሃይመን ጄላን ጀርባው ላይ በስለት ስለወጋው ነበር። ይህንን የተመለከቱት የሃይመን ጄላን አጃቢዎች የደሙን መፍሰስ ተከትሎ ሃይለኛ ድንጋጤ ውስጥ ገቡ።

የሙሉቀን ወንድም ፍቃዱ መምጣቱን ቢያዩም ደፍረው ለመጠጋት አልሞከሩም። ፍቃዱ የያዘውን የሽንኩርት ቢላዋ መዘዝ አድርጎ የእናቱን ልጅ ወንድሙን በስለት የወጋበትን ሃይመንን ለመውጋት ተጠጋ። ማንም ሊያስጥለው አልሞከረም። ፍቃዱ የልብ ልብ ተሰማው፤ ወንድሙን ሲያይ የሙሉቀን ደም እየፈሰሰ ነው። ፍቃዱ ቢላዋውን ወደ ሃይመን አንገት ሰነዘረ። አልሳተውም የሃይመንን አንገት ቆረጠው።

ሃይመን ከሙሉቀን ጎን ወደቀ። ደሙ ከሙሉቀን በላይ መፍሰስ ጀመረ። የሃይመን ወዳጆች ብዙ በመሆናቸው አውራቸው ሲወጋ ግርግር ፈጠሩ። ነገር ግን አውራቸውን ማዳን አልቻሉም። በሌላ በኩል በአብዛኛው ሲጠቃ የነበረው የእነ ፍቃዱ ቡድን አባላት በፍጥነት ባጃጅ አምጥተው ሙሉቀንን ይዘው በአካባቢው ወዳለ ጤና ጣቢያ አፈተለኩ።

ሙሉቀን ምንም እንኳ ደሙ እየፈሰሰ ቢቆይም በሕክምና ባለሙያዎች እርዳታ ሕይወቱ ተረፈ። የሃይመን ቡድን አባላት አውራቸውን ሕክምና ቦታ አላደረሱትም። እዛው አስፓልት ላይ እንደተጋደመ ሕይወቱ አለፈ። ጩኸት በረከተ፤ እናቶች ተጠራርተው ነጠላቸውን እያዘቀዘቁ ወደ መስቀለኛ ሮጡ።

ፖሊስ ተጠራ፤ የፖሊስ የምርመራ ቡድን አስከሬኑን ለምርመራ ከላከ በኋላ ማጣራት ጀመረ። ፍቃዱ ወንድሙን ጨምሮ የቡድን ፀብ ውስጥ ሲሳተፉ የነበሩትን በሙሉ ሃይመንን ገድላችኋል በሚል ግንቦት 5 ቀን 2012 ዓ.ም ተጠርጣሪዎቹን በቁጥጥር ስር አዋለ። በመጨረሻ ጥርጣሬው ወደ ፍቃዱ በማድላቱ ሌሎቹ ተለቀው ከዛ ጊዜ ጀምሮ ፍቃዱ ወንድሙ እስር ቤት ሆኖ ሲከራከር ቆየ።

## የክሱ ዝርዝር

የፖሊስ የምርመራ ቡድኑ ማስረጃዎችን አሰባሰበ። በብርቱ ጥረት ድርጊቱን ማን እንደፈፀመ አረጋገጠ። በመጨረሻም ለአቃቤ ሕግ እነ ፍቃዱ ወንድሙ በሚል ክስ እንዲመሰረት ይደረግ ሲል፤ መረጃውን እና ማስረጃውን ለአቃቤ ሕግ አቀረበ። ዐቃቤ ሕጉም ሚያዚያ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከ30 አካባቢ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ቦታው የካ አባዶ ኮንደሚኒየም መስቀለኛ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተጠርጣሪው ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር በመሆን፤ የቡድን ፀብ አንስቷል። በተነሳው የቡድን ፀብ ሟች ሃይመን ጄላን የተባለውን ወጣት አንገቱ ላይ በመውጋት ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርጓል ሲል ክስ መሠረተ።

ክርክሩ በአቃቤ ሕግ እና በእነ ፍቃዱ ወንድሙ መካከል ሲካሄድ፤ አቃቤ ሕግ የሰው ምስክር እና ከሰው እና ከሆስፒታሉ ማረጋገጫ የሰነድ ማስረጃ አቀረበ። የሟች አስከሬን የምርመራ ውጤትና የወንጀሉን አፈፃፀም እንዲሁም ሟች ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን የሚያሳይ ገላጭ ፎቶዎች በማስረጃነት ሰጠ።

ከማስረጃዎቹ መካከል የሟች ማንነት ጉዳቱ የደረሰበትን የሟች የሰውነት ክፍል፣ የወንጀሉ ሥፍራ እና ወንጀሉ የተፈፀመበትን ቢላዋ ለማሳየት የተነሱ ፎቶ ግራፎች ለፍርድ ቤት ቀርበዋል። ይህንን ሁሉ ማስረጃ ያቀረበው ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ቤቱ ብይን ሰጥቶ የቅጣት ውሳኔ ሊያሳልፍ ይገባል ሲል ጠየቀ።

## ውሳኔ

**ተከሳሽ ፍቃዱ ወንድሙ ሰው በመግደል ወንጀል የተከሰሱ በመሆኑ፤ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ 1ኛ ምድብ ወንጀል ችሎት በጥቅምት 23 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክስና ማስረጃው ከሕግ ጋር አገናዝቦ የወንጀል ፈፃሚውን ያርማል ሌሎችን ያስተምራል ብሎ ባመነበት በ21 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ውሳኔ አስተላልፏል፡፡**

# መረጃውን - በማስረጃ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የሰውልጅ ለኑሮው አመቺነት ሲል «ይበጀኛል» ብሎ የሚመርጣቸው ወሳኝ ጉዳዮች ይኖራሉ። እነዚህ እውነታዎች ብዙ ጊዜ በሌሎች ዘንድ እንደቅንጦት ሊቆጠሩ ቢችሉም አንዳንዴ ደግሞ ከምርጫ በላይ ሆነው አስገዳጅ የሚሆኑበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡

ብዙ ጊዜ በኑሮ ሂደት ምርጫ በታጣ ጊዜ ከራስ አቅም በላይ ከሆነ ጥግ ማረፍ የግድ ይላል። አንዳንዶች እንዲህ ሲያደርጉ ከኪስ አቅማቸው ሞልቶ ተርፏቸው ሳይሆን ምርጫ የማጣት ግዴታ ላይ ስለወደቁ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡

ለዚህ ሀሳብ እንደ ማሳያ ቢረዳ ቀለል የሚል አንድ ምሳሌ ላንሳ። የጋራ መኖሪያ ቤቶች /ኮንዶሚኒየም/ እና የውዴታ ግዴታውን ጉዳይ። አብዛኛው የሚባለው የጋራ ቤቶች ነዋሪ የኋላ ታሪክ ቢጠና ቀድሞ በግቢ አልያም በመሬት ቤቶች ላይ ይኖር እንደነበር ማረጋገጡ ቀላል ነው። የእንዲህ አይነቱ ነዋሪ የቀደመ ህይወት ታዲያ እንደዛሬው ከዘመናዊነት ይተዋወቅ ዘንድ የሚያስገድድ አልነበረም፡፡

በነዚህ መንደሮች ኑሮና ህይወት ሲመራ የቆየው አስገዳጅ ይሉት ህግ ተሰምሮለት አልነበረም። ምናልባትም እንደ ባለቤቱ አቅምና ፍላጎት አመቺነቱ ተመርጦና፣ተለይቶ እንጂ። በአካባቢው ሁሉም በሚባል መልኩ ኑሮው ተመሳሳይና አንድ አይነት ነው። ማንኛዋም እናት ከኩሽናዋ ገብታ በእንጨት እንጀራ ብትጋግር፣አሻሮ ብትቆላ፣ እርጥብ ከደረቅ ማግዳ ብታጨስ ብታጫጭስ እንዴት የሚላት አይኖርም። ለምን ቢሉ ጎረቤቶቿና አካባቢው ሁሉ የእሷን አይነት ኑሮ መጋራታቸው ብርቅ ባለመሆኑ።

ዘመን ተቀይሮ አካባቢ ሲለወጥ፣ቦታ ሲቀየር ደግሞ የትናንቱ ህይወት ዛሬ ላይ ላይደገም ግድ ይሆናል። ይህ አይነቱ ህይወት በጋራ መኖሪያዎች ላይ ሲሆን ደግሞ የኑሮው ለውጥ ከአስገዳጅ መስመር ውስጥ ሊገባ በሩ ይከፈታል። ቀድሞ በእንጨት፣ በቅጠል፣የሚጋገረው እንጀራና ዳቦ ዛሬ በኤሌክትሪክ ምድጃዎች ሊተካ፣የእጅ ወፍጮ፣የእንጨት ሙቀጫና ዘነዘና ታሪክ በመሰል ቴክኖሎጂዎች ሊለወጥ የኑሮው ባህርይ ከዘመናዊነት ያዛምዳል።

ይህ አይነቱ አጋጣሚ በሰው ልጆች የህይወት መስመር ላይ በገባ ጊዜ የውዴታ ግዴታ ይሉትን ማንነት መጀመሩ አይቀሬ ነው። ይህን የማድረጉ አቅም የሌላቸው ነዋሪዎች ቢኖሩ እንኳን ብዙሀኑን ሊመስሉ የግድ ይላቸዋል። በዚህ የጋራ ህይወት ኑሮ ሲጀመር በእንጨት መጋገር ይቀራል፣ ከማጀት ዘልቆ አሻሮ መቁላት ጠላ ጠምቆ በጋን እንስራ መሙላት ከኋላ ቀርነት ይቆጠራል፡፡

ትናንት በዛሬ ተተክቶ ቀን መሽቶ በነጋ ቁጥር ሁኔታዎች እንደቀድሞው በነበሩበት አይቀጥሉም። አብዛኞቹ የኑሮ ልማዶች በነበር ተተክተው ባህርያቸው ይለወጣል። የኑሮ ልማድ መልኩን ቀይሮ በሌላ ዘመን ወለድ አጋጣሚዎች ይተካል። ይህ እውነታ እንግዲህ ሰዎች ወደውም ይሁን ተገደው የሚገቡበት የህይወት መስመር ሆኖ ይቀጥላል። በአቅም ማጣትና በሌሎች ችግሮች ከዚህ የኑሮ መስመር ልውጣ ልዛነፍ የሚል ቢኖር በሀሳቡ አይቀጥልም፣ የኑሮው አስገዳጅነት ከበርካቶች የህይወት መልክ ጋር እንዲመሳሰል ምሪት ይሆነዋል፡፡

ልክ እንደጋራ ቤቶቹ የህይወት ተመሳስሎ ሁሉ በርካቶች ከዘመኑ መልኮች ጋር ተቆራኝተው እንዲጓዙ ግድ የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራል። እነዚህ ወገኖች የትናንትናው የኑሮ ቀለም ሲቀየር ከወቅቱ ጋር ሊራመዱ የሚያስገድዳቸው ጊዜ ወለድ ለውጦች በርካቶች ይሆናሉ። ለምሳሌ የልጆች አስተዳደግና ውሎ፡፡

ከጥቂት ዓመታት በፊት በነበረው ተሞክሮ ወላጆች ልጆቻቸውን ለማሳደግ እንደዛሬው ከበዛ ጭንቅ የሚገቡበት አጋጣሚ ነበር ለማለት አያስደፍርም። የዛኔ የኪስ አቅም በሚችል ክፍያ ሰራተኛ መቅጠር፣ ከገጠር የዘመድ ልጆች ማስመጣት ፣ ብርቅ አልነበረም።

ለቤት ሰራተኞች የሚከፈለው ደመወዝም ቢሆን እንደአሁኑ ዋጋው የዶላር ያህል አልናረም። ታላላቆቹ ልጆች ታናናሾቻቸውን አዝለውና አቅፈው እንዲያሳድጉ ግዴታ ነበረባቸው። ይህን የሚያደርግ ቤተሰብ ቢታይ ደግሞ ማንም ለምን ሲል የሚጠይቅ፣ የሚኮንነው አይኖርም። የዛኔ ልጅን ለጎረቤት አደራ ሰጥቶ ካሻው ከርሞ መምጣት፣በተራው የሌላውን ልጅ ተቀብሎ እንደራስ መያዝ ፣ማሳደግ ተገቢ ልምድ ነበር፡፡

ይህ አብሮነት የፈጠረው እውነታ ለዓመታት እንደ ባህል ፀንቶ መዝለቁ፣ ‹‹ነበር›› ብሎ መወሳቱ ከተፋዘዘ ግን ዓመታት መቆጠር ይዘዋል። ዛሬ አብዛኛው ነዋሪ ግላዊነትን ምርጫው አድርጓል። ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ አቋራጭ መንገዶችን እየተጠቀመ ነው። ዘንድሮ ልጅን ለጎረቤት፣ለሰራተኛ ጥሎ መውጣት ጉዳቱ ቢያመዝን አማራጮች ሰፍተዋል።

በትናንቱ ጎዳና የመራመድ ዕድል በጠበበት በአሁኑ ዘመን ሰዎች ወደተሻለው መስመር ማምራታቸው ያለምክንያት አይደለም። ልክ እንደጋራ ቤቶቹ /ኮንዶሚኒየም/ ኑሮ ሁሉ እነዚህ የተሻሉ ምርጫዎች አስገዳጅ እየሆኑ ነው ለማለት ያስደፍራል። የሞግዚቶች ደመወዝ ማሻቀብ፣ የታማኝነታቸው ጉዳይ ማስጋትና ሌሎችም ምክንያቶች ወላጆችን ይበጃል በሚሏቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች እያሻገሩ ነው፡፡

አሁን ላይ ልጆችን ከጨቅላነት ዕድሜ አንስቶ ለመቀበል የተዘጋጁ የህጻናት መንከባከቢያዎች ተበራክተዋል። እነዚህ በየመንደሩ የተከፈቱ በተለምዶ ‹‹ደይ ኬር›› የምንላቸው ማቆያዎች የወላጆችን የድካም ትከሻ ለማሳረፍ ታላቅ መፍትሄዎች ሆነዋል።

የህጻናት ማቆያዎቹ ከዚህም አልፎ ልጆችን ከማንኛውም የአደጋ ስጋት ጠብቆ የወንጀል ሰለባ እንዳይሆኑ ለመታደግ ጭምር ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። ኃላፊነትን በአግባቡ ተቀብለው ልጆችን በአደራ የሚያውሉ አካላት የራሳቸው ጠቀሜታና ጉድለት ቢኖራቸውም አቅሙ ላላቸው ወላጆች ግን የቀኝ እጅ ያህል ድጋፋቸው የበረታ ነው፡፡

አንዳንዴ ግን በነዚህ ህጻናት ማቆያዎች ላይ የሚነሳ ቅሬታ መሰል አስተያየት አይጠፋም። ማቆያዎቹ ለእንክብካቤ የሚያውሏቸውን ቁሳቁሶች በግልጽ ማስጎብኘታቸው የተለመደ ነው። ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ የጤንነትን ጉዳይ አስመልክቶ ከግድግዳቸው ላይ የሚለጥፉት ጌጠኛ የህክምና ባለሙያ ፈቃድ ከግልጽ ስፍራ ላይ እንዲታይ ያደርጋሉ።

የህጻናት ማቆያዎቹ ይህን ማድረጋቸው በማዕከሉ የጤና እንክብካቤ በተገቢው የህክምና ባለሙያ ይከወናል ለማለት ነው። ይህን ያደርጉ ዘንድ ደግሞ በእነሱ ደረጃ የተቀመጠው ደንብና መመሪያ ያስገድዳል። ወደ እውነታው መለስ ሲባል ግን ውጤቱ ከሌላ ጥግ የሚያደርስ ይሆናል ፡፡

ይህን የግድግዳ ላይ ነብር በተግባር አዛምደን አይተነዋል የሚሉ ታዛቢዎች እንደሚሉት ግን ማስረጃው ከእይታ ያለፈ ጠቀሜታ የለውም። በማቆያዎቹ እንደተባለው ሆኖም ተገቢው የህክምና ባለሙያ አይገኝም። ይህ አይነቱ እውነታ በአብዛኛዎቹ የህጻናት ማቆያዎች ዘንድ የተለመደና ተጠያቂነትን የሚያስነሳ ነው።

እርግጥ ነው በየትኛውም አገልግሎት ሰጪ ማዕከላት ውስጥ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ አገልግሎትን መተግበሩ የግድ ይላል። በተለይ ደግሞ ህጻናት በሚገኙበት አጸድ የጤና ነገር በአግባቡ ዕውን እንዲሆን ህጉና መመሪያው ሊተገበር ያስገድዳል። ከምንም በላይ ግን ቃል በተግባር ተተርጉሞ፣ መረጃው ፣በማስረጃ ተደግፎ በታማኝነት መቆም ሙያን ያስከብራል፣ ማንነትን በወርቃማ ስም ያደምቃል።

## ዓለም አቀፍ

# አክራሪ አሜሪካዊያን ሴቶች በወንዶች ላይ የወሲብ ማዕቀብ እንዲጣል ያለመ ዘመቻ ጀመሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አክራሪ አሜሪካዊያን ሴቶች በወንዶች ላይ የወሲብ ማዕቀብ እንዲጣል ያለመ ዘመቻ ጀመሩ፡፡

ባሳለፍነው ማክሰኞ የተደረገው የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ጉዳይ አሁንም የዓለምን ትኩረት መሳቡን ቀጥሏል፡፡

የምርጫው ዋነኛ ተፎካካሪዎች የሆኑት ዶናልድ ትራምፕ እና ካማላ ሀሪስ በምርጫ ቅስቀሳቸው ወቅት ጽንስ ማቋረጥ ጉዳይ ዋነኛ የክርክር አጀንዳ ነበር፡፡

የዲሞክራት ፓርቲ ዕጩዋ ካማላ ሀሪስ ጽንስ ማቋረጥ ጉዳይ የሰዎች መብት መሆን አለበት፣ ውሳኔው ለግለሰቦች መሰጠት አለበት በሚል ስትከራከር የሪፐብሊካኑ ዶናልድ ትራምፕ ደግሞ ይህ የሰዎች መብት ቢሆንም በጉዳዩ ዙሪያ መወሰን ያለባቸው ግዛቶች ናቸው የሚል አቋም አላቸው፡፡

ሁለቱም እጩዎች በጉዳዩ ዙሪያ አቋማቸውን ግልጽ ማድረጋቸውን ተከትሎ ወንዶች እና የሀሳቡ ደጋፊ የሆኑ ሴቶች ድምጻቸውን ለዶናልድ ትራምፕ መስጠታቸውን ተከትሎ ምርጫውን አሸንፈዋል፡፡

የምርጫው ውጤት መታወቁን ተከትሎ የሴትነት አክራሪ አሜሪካዊያን ሴቶች መብታችን ተነፍጓል በሚል ሴቶች በወንዶች ላይ የወሲብ ማዕቀብ ሊጥሉ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በማህበራዊ የትስስር ገጾች ላይ የተጀመረው ይህ ዘመቻ ወንዶች ነጻነታችንን ነፍገው በአካላችን መደሰት አይችሉም ሲሉም ጥሪያቸውን እንዳስተላለፉ ዘ ቴሌግራፍ ዘግቧል፡፡

ከተላለፉ መልዕክቶች በተጨማሪም ሴቶች ለፍቅር አጋር መፈለጊያ ተብለው የለሙ የመገናኛ መተግበሪያዎችን ከስልካቸው ላይ እንዲያጠፉ እና ክልከላውም ለቀጣዮቹ አራት ዓመታት እንዲቆይ የሚሉም ይገኙበታል፡፡

ከአሜሪካ ባለፈም መሰረቱን በደቡብ ኮሪያ ያደረገው “4ቢ” የተሰኘው የሴትነት ንቅናቄ የዶናልድ ትራምፕን መመረጥ መቃወሙን እና ዘመቻውን እንደተቀላቀለ አስታውቋል፡፡

“4ቢ” የተሰኘው ይህ ንቅናቄ የኮሪያ ቋንቋ አራት ቃላት የተፈጠረ ሲሆን ትርጉሙም የፍቅር ቀጠሮ አንይዝም፣ ልጅ አንወልድም፣ ወሲብ አንፈጽምም፣ አናገባም የሚል ትርጉም ያለው ነው፡፡



# የቱርኩ ፕሬዚዳንት ኤርዶጋን ትራምፕ እስራኤል ጦርነቱን እንድታቆም ይነግሯታል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቱርኩ ፕሬዚዳንት ታይፕ ኢርዶጋን በድጋሚ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ዶናልድ ትራምፕ እስራኤል ጦርነት እንድታቆም ይነግሯታል የሚል ተስፋ እንዳላቸው በትናንትናው ዕለት ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንቱ ለእስራኤል የጦር መሳሪያ ድጋፍ ማቆም ጥሩ ጅምር ሊሆን እንደሚችልም አስተያየት መስጠታቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

“ትርምፕ ግጭቶችን ለማቆም ቃል ገብተዋል... ያ ቃል እንዲፈጸም እና እስራኤል ጦርነት እንድታቆም እንዲነገራት እንፈልጋለን” ብለዋል ኢርዶጋን።

ኢርዶጋን አክለው እንደተናገሩት፤ እስራኤል በፍልስጤም እና ሊባኖስ የምታደርገውን ወረራ እንድታቆም ትራምፕ አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገውን የጦር መሳሪያ ድጋፍ ካስቆመ ጥሩ ድምር ይሆናል።

ቱርክ እስራኤል በፍልስጤም እና በሊባኖስ ግዛቶች የምታካሂደውን ወረራ አጥብቃ የምታቀወም ሲሆን ከእስራኤል ጋር ያላትን የንግድ ግንኙነት አቋርጣለች። ቱርክ በእስራኤል ላይ በዓለም አቀፉ የወንጀሎች ፍርድ ቤት የቀረበውን የዘር ማጥፋት ክስ ደግፋ ለመከራከርም ያመለከተች ሀገር ነች።

የትራምፕ ፕሬዚዳንት መሆን በመካከለኛው ምስራቅ ባለው የኃይል ሚዛን ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል ያሉት ኢርዶጋን፤ አሁን ያለውን የአሜሪካ ፖሊሲ መከተል በቀጣናው ያለውን ቀውስ እንደሚያባብሰው ገልጸዋል።

ቱርክ ከአሜሪካ ጋር ያላት ግንኙነት በአዲስ መልክ እንዲስተካከል የሚፈልጉት ኢርዶጋን፤ ከትራምፕ ጋር በስልክ ማውራታቸውን እና ቱርክን እንዲጎበኙ ግብዣ ማቅረባቸውን ተናግረዋል። ኢርዶጋን አክለውም ትራምፕ ግብዣውን እንደሚቀበሉት ተስፋ አለኝ ብለዋል።



## መጋቢ አዕምሮ

# አዕምሮን መቆጣጠር

**አስናቀ ፀጋዬ**

አዕምሯችን የምንፈልገውን ብቻ እንድናስብ የምናደርገው እንዴት ነው? ራልፍ ዋልዶ ኤመርሰን የተባለ ደራሲ ‹‹የሰው ልጅ ማለት በቀን ውስጥ ደጋግሞ ያሰበውን ነው›› ይላል። ምን ማለቱ መሰላችሁ፣ እናንተ በቀን ውስጥ የምታስቡት ምንድን ነው? ብሶት ነው፣ ቁጭት ነው፣ ንዴት ነው፣ ራስን መውቀስ ነው፣ መጥፎ ሃሳብ ነው? እንደዛ ከሆነ በሕይወታችን ውስጥ መጥፎ ሃሳብና ብሶታችን ሁሉ ይገለጣል። መጥፎ እንሆናለን። ሕይወታችን ወደ መጥፎ ሁኔታ ያመራል። ለምን? ደጋግመን የምናስበው መጥፎ ሃሳብ ነዋ! ቁጭት ነዋ! ሃሳባችንን መቀየር አለብን። እሱን ማራገፍ አለብን። እንዴት? ካላችሁ እንደሚከተለው........

በቅድሚያ ግን አዕምሮን በመቀየር ወደ ብርሃን የሚወጣው እንዴት ነው? በጎውንና መልካሙን ማሰብ የሚቻለውስ በምን መልኩ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ አራት አይነት መጥፎ ሃሳቦችን መለየት ያፈልጋል። የትኛው ሀሳብ እኛን እንደተቆጣጠረንና እኛው ውስጥ የትኛው እንዳለ መለየት ይገባል። ከአራቱ ምድብ የእናንተን ምድብ ከለያችሁ በኋላ መፍትሄውን አውቃችሁ ወደተግባር ትቀይሩታላችሁ። በጣም ወሳኙ ነገር ደግሞ እውቀት ሳይሆን ተግባር ነው።

አዕምሯችን በቀን ውስጥ ከ60 ሺ በላይ ሀሳቦችን ያስባል። የሚገርመው ግን ከ60ሺዎቹ ውስጥ አብዛኞቹ ወይም በሙሉ ተደጋጋሚ ናቸው። ትናንት ስናስበው ነበር። ከትናንት ወዲያም፣ የዛሬም ዓመት ስናስበው ነበር። ተደጋጋሚ ነው። ሕይወታችንን ግን ምንም አልቀየረውም። ለእኛ የሚጠቅሙን ሀሳቦች በጣም ጥቂቶች ናቸው። አብዛኞዎቹ ግን ተደጋጋሚ ናቸው። በዛ ላይ መጥፎ ናቸው። ግን የትኛው ምድብ ውስጥ ይወድቃሉ? እናንተ ናችሁ የምትፈርዱት። ከሚከተሉት አራት ምድቦች መካከል ደጋግመን የምናስበው ሀሳብ የት ውስጥ እንደሆነ ማወቅና መለየት አለብን። የመጀመሪው ስራም እሱ ነው።


**የመጀመሪያው ምድብ ውስጣዊ ወቀሳ ይባላል።** ራሳችሁን በጣም ትወቅሱታላችሁ? ቤተሰብ የነገራችሁን፣ ጓደኛ፣ የሰፈር ሰው፣ የምታውቁት ሰው፣ ዘመድ፣ መምህሮቻችሁ፣ ብቻ የምታውቁት ሰው የወቀሳችሁ ወቀሳ ይኖራል። ‹‹አንተ ሰነፍ ነህ ባክህ ለስራ አልተፈጠርክም፣ ለትምህርት አትሆንም፣ አትረባም፣ ለንግድ አትሆንም፣ ይቅርብህ›› የሚሉህ መጥፎ ወቀሳዎች ከበዙ እኛም ‹‹አዎ ባክህ አትችልም አንተ ይቅርብህ›› እንለዋለን። እንደዚህ አይነት ወቀሳ አለብን? እሱ ከሆነ አንተ የመጀመሪያው ምድብ ውስጥ ነህ።

**ሁለተኛው ምድብ ጭንቀት ነው።** አንዳንድ ሰዎች ገና ወደፊት ለሚመጣው ነገር ይጨነቃሉ። ‹‹እንዲህ ቢሆንስ ግን፣ እንዲህ ቢፈጠርስ፣ የሀገሪቷ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ በቃ አለቀልን እኮ፣ ቤተሰቦቼ እንዲህ ከሆኑ ምን ልሆን ነው ወደፊት፣ እንዴ! ደሞዝተኛ ሆኜ ልቀር ነው፣ ኑሮ እኮ እየተወደደ ነው፣ ደሞዜ ደግሞ እዛው ነው ትንሽ ነው የሚጨምረው፣ ምንድን ነው የምሆነው›› እያላችሁ ነገን በማሰብ ትጨነቃላችሁ? አንዳንድ ግዜ ደግሞ የማትቆጣጠሩት የመንግስት ጉዳይ፣ የቤተሰብ ጉዳይ ያስጨንቃችኋል? እንዳዛ ከሆነ እዚኛው ምድብ ላይ ናችሁ ማለት ነው።

**ሶስተኛው ምድብ ባለፈው መንገብገብ ነው።** ጭንቀት የወደፊቱን ማሰብ ነው። አሁን ደግሞ ያለፈው ነገር ነው የሚያንገበግባችሁ። ድሮ ላይ ነው ያላችሁት። ‹‹እንዲህ ባላደርግ እኮ ወይኔ!፣ አይ! አልረባም እኮ እኔ፣ እንዲህ አድርጌ፣ እንዲህ አጥፍቼ...›› የከሰርነው፣ ያበላሸነውን፣ የተበላሸብንን ወይ ያጠፋነውን ጥፋት እናስብና በጣም እንናደዳለን። በቃ! ብሶት፣ ንዴት ይሰማናል። ‹‹አዬ እንዲህ ባላደርግ ኖሮ›› እንላለን ሁልግዜ። ረሳነው ስንል ሰው ያስታውሰናል። ‹‹ኸረ አታስታውሰኝ እንደው ውይ! ውይ! ራስ ምታቴ ተነሳ፣ በቃ ጨጓራዬ ተቃጠለ›› የምንል ሰዎች አለን።

እዛ ድረስ ባይገፋ እንኳን ትናንትን ስናስብ የምንጨነቅ፣ በቃ! ቤታችንን ትናንት ላይ፣ ድሮ ላይ እየሰራን ሁልግዜ ስለ ትናንት የምናስብ ሰዎች አለን። ያጠፋነውን፣ ያበላሸነውን የምናስብ። ከዛ አሁን ያለው ነገር የሚያመልጠን አለን። እኛ እዚህ ምድብ ውስጥ ልንሆንም እንችላለን።

**አራተኛው ደግሞ ድብልቅልቅ ሀሳብ ምድብ ይሰኛል።** ይህ ማለት በቃ! ቁጭ ስትሉ የትናንቱም ያሳስባችኋል። እንዲህ ቢሆንኮ ኖሮ፣ እንዲህ ባላደርግ ባላጠፋ ትላላችሁ። ነገን ደግሞ ታስቡና እንዲህ ቢፈጠር ትላላችሁ። ከዛ ደግሞ ራሳችሁን ትወቅሱና እኔ እኮ አረባም ትላላችሁ። እንግዲህ ምድባቸውን መለየት ነው የመጀመሪያ ስራችሁ። ስለዚህ ራሳችሁን ነው የምትወቅሱት?፣ ወይስ ስለወደፊቱ ነው በጣም የምታስቡት?፣ ወይስ ስላለፈው ነው የምትቆጬት? አልያ ደግሞ የተደበላለቀ ሀሳብ ነው ያላችሁ? ከአራቱ አንዱን ለዩ።



**መጥፎ ሀሳቡና ትናንትናው ይቀርና አዲሱ ማንነት ይገነባል። ደጋግመን ያሰብነውን እንሆናለን። ለምሳሌ እጃችን ላይ ያለው ስልክ መጀመሪያ ሀሳብ ነበር። ያ ሃሳብ ተመላልሶ ቁስ ሆኖ እጃችን ላይ ገባ። ምንም ነገር ከመገለጡ በፊት አዕምሮ ውስጥ ታስቧል። ሃሳብ ነበር። እኛም ሕይወታችንን፤ ነጋችንን ማሰብ አለብን**

ምድባችሁን ስትለዩ ጠላታችሁ ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ። እንደውም ስም ስጡት። የኔ ችግር ወቀሳ ነው?፣ ነገን መፍራት ነው?፣ ብሶት ነው?፣ አትችልም የሚል መንፈስ ነው?፣ ወይስ ምንድን ነው?፣ ጭንቀት ነው? ስጋት ነው? ለዩት፤ ስም ስጡት። ስም ስትሰጡት ምን ጥቅም ይሰጣችኋል መሰላችሁ፤ ከማን ጋር እንደምትፋለሙ ታውቃላችሁ። አንዳንዴ ጠላታችሁ ማን እንደሆነ፣ የት እንዳለ እንዴት ሆኖ እንደሚጠብቃችሁ ካላወቃችሁ እኮ አትፋለሙም። ወዴት ትሄዳላችሁ ጠላታችሁን ካላወቃችሁት።

አያችሁ! አሁን እኔን እኮ የሚያስጨንቀኝ ስጋት ነው አሁን ነው የገባኝ፣ በቀን ውስጥ በአዕምሮዬ ውስጥ የሚመላለሰው ሁሉ መጥፎ ሃሳብ ነው አትችልም የሚል እንደው ይቅርብህ፤ አትጀምረው የሚል ተወው ቢዝነሱን፣ ትምህርቱ ይቅርብህ፣ ስራውንም ተወው የሚል ነው። ወይ ደግሞ ጭንቀት፤ ገና ለገና ይሆናል አይሆንም። ወይ ደግሞ ብሶት፤ ባለፈው የተፈጠሩ ነገሮች... አሁን ለየን። ስንለይ በጣም ጥሩ ነው። ከለየን በኋላ የሚጠብቀን መፍትሄ ነው። ምን እናደርጋለን መሰላችሁ?

አንዳንድ ግዜ መጥፎ ሀሳቦች እስከመጨረሻው ይጠፋሉ ማለት አይደለም። አንዳንድ መጥፎ ሀሳቦች ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ። የእኛም ጥፋት ሊሆን ይችላል። ይህን ነገር አላስበውም ትሉና መልሶ ይቆጣጠራችኋል። እንደውም እናንተ ልትረሱት በሞከራችሁት ቁጥር እሱ በደምብ እየተቆጣጠራችሁና እያስታወሳችሁት ትመጣላችሁ። መርሳት አለመቻላችሁን ስታስቡት ትናደዳላችሁ። እንደዛ ሲሆን ምንድን ነው ችግሩ ማለት አለብን። መፍትሄ መስጠት አለብን።

ለምሳሌ በቢዝነሱ እኮ የከሰርከው በቂ ዝግጅት ባለማድረግህ ሊሆን ይችላል። በትምህርት ውጤት ሳታመጣ የቀረኸው በበቂ ሁኔታ ስላላነበብክ ሊሆን ይችላል። የሆነ ነገር ያልተሳካው ካንተ ችግርም ሊሆን ይችላል። አየህ! ድክመትህን መረዳት አለብህ ማለት ይህ ነው። ስንፍናህን ሽፋፍነህ እንድታልፍ አይደለም። ድክመትህን እንድታውቅ ነው። ነገር ግን ከዛ ከዘለለስ? አይ እኔ ስንፍና ብዙ የለብኝም ግን መጥፎ ሃሳብ ይቆጣጠረኛል ካልክ መፍትሄው ለራስ ይቅርታ ማድረግ ነው።

ወቀሳውን አቁም። ለአዕምሮህ ንገረው። እስከዛሬ ድረስ ጥሩ አድርገህ ወቅሰኸኛል፣ የወደፊቱ እንደሚያሳስብህ ነግረኸኛል፣ ስለባለፈው ብዙ እንደምትጨነቅ፣ ብሶትህን ሁሉ ነግረኸኛል ከዚህ በኋላ ግን ይበቃል መንቃት አለብኝ በል። ከዚህ በኋላ ብሶት ያበቃል። ከዚህ በኋላ ስለመፍትሄው ነው ማሰብ ያለብህ። እስከዛሬ ብላችሁ እንዳትንገበገቡ። በቃ ዝም ብዬ ስኖር ነበር ለካ ተበልቻለሁ እንዳትሉ። ከዚህ በኋላ ያለው ነው ዋናው። ከዚህ በኋላ እናንተ ትቆጣጠሩታላችሁ። ስለዚህ ይቅርታ አድርጉለት። ትልቁ የስኬት ሚስጥርም እኛ የምንፈልገውን ብቻ ማሰብ ነው። ከዚህ በኋላ መፍትሄው በጣም ቀላል ነው። ሀሳብህን ነቅተህ ነው መጠበቅ ያለብህ።

እንግዲህ ከአራቱ ምድብ ውስጥ የእናት ብሶት ከሆነ ወይ ደግሞ ትችት፤ ራሳችሁን የምትወቅሱት ከሆነ፣ አንተ አትችልም፣ አትረባም የሚላችሁ ከሆነ ልክ እንደዛ ሲላችሁ እጅ ከፈንጅ ያዙት። አይ እኔ የማልረባ ሰው አይደለሁም፣ እረባለሁ፣ በጣም ጎበዝ ነኝ፣ ጀግና ነኝ፣ የምፈልገውን ነገር አሳካለሁ፣ እችላለሁ ብላችሁ መልሱለት። ልክ ወቀሳውን ሲያቀርብ እጅ ከፈንጅ ትይዙትና ትፋለሙታላችሁ፣ ትነግሩታላችሁ፣ ውስጣችሁ ያለው ድምጽ እንደጠላት ነው መጀመሪያ ሰሞን።

ለምን? የሚያውቀው እንደማትችሉ ነዋ! እሱን ነው የሚነግራችሁ አዕምሯሁ። እናንተ ደግሞ ተቃራኒውን ትነግሩታላችሁ። እንደምትችሉና ጀግና እንደሆናችሁ። ያኔ መመዝገብ ይጀምራል። ከቻላችሁ ብትፅፉት በተለይ አዕምሯችሁ ሲወቅሳችሁ እኔ በጣም እችላለሁ፣ ጎበዝ ነኝ ብላችሁ ስትፅፉ ለአዕምሯችሁ ጥሩ ነገር እየነገራችሁት ነው። እሱን መመዝገብ ይጀምራል።

ሌላኛው ደግሞ አንዳንድ ሰዎች ጭንቀት አለብኝ፤ ስለነገ እጨነቃለሁ ለምትሉ አዕምሯችን አንዳንዴ ሲጨናነቅ ጥሩ ምልክት እየሰጠን ሊሆን ይችላል። ስለምንቆጣጠረው ነገር ቢሆንስ እየተጨናነቀ ያለው? ማስተካከል የምንችለው ነገር እኮ ካለ ማስተካከል አለብን። መጨመር፣ መቀነስ የሆነ ማስተካከል ያለብን ነገር ካለ መቆጣጠር አለብን። ስለዚህ በሕይወታችን ውስጥ የምንቆጣጠራቸውን እናስተካክላለን። የእኔ አዕምሮ ስለማይቅመው ነገር ነው የሚጨነቀው ካላችሁ ግን አዕምሯችሁን ሃሳቡን ታስቀይሱታላችሁ። ከጭንቀት እንዲወጣ ሌላ ሀሳብ ትሰጡታላችሁ።

ለምሳሌ እጃችሁ ላይ ያለውን ነገር ታመሰግናላችሁ። ልክ ስለሀገር ጉዳይ ሲያስጨንቃችሁ፤ ወይ ደግሞ የማያሳስብ ነገር ሲያሳስባችሁ ተመስገን ጤና ሰጠኸኝ፣ እንዲህ አደረክልኝ፣ እንዲህ ሆንኩ እያላችሁና እጃችሁ ላይ ያለውን እየተመለከታችሁ ታመሰግናላችሁ። ያኔ ጭንቀታሙ አዕምሯችሁ አመስጋኝ ይሆናል።

ሌላው ደግሞ መጥፎ ሀሳብ የምታስቡ፣ ስላለፈው የምትጨነቁ ወይም ደግሞ ድብልቅልቅ የሚልባችሁ ሰዎች ምን ታደርጋላችሁ መሰላችሁ፤ ነጋችሁን፤ አላማችሁን አስታውሱት። እንዲህ እኮ ልሆን፣ እንደዚህ አይነት ሕልም አለኝ፣ እንደዚህ አይነት ሰው ልሆን ነው ማለታችሁን። የዛሬ አምስት ዓመት የሚኖራችሁ ማንነት ምን አይነት እንደሆነ እስኪ አይናችሁን ጨፍናችሁ አስቡት። ምን አይነት ገቢ ነው የሚኖራችሁ፣ ምን አይነት ትዳር ነው የሚኖራችሁ፣ ግዜያችሁን በምን አይነት ሁኔታ ነው የምታሳልፉት ...ወዘተ ነጋችሁን ማሰብ ስትጀምሩ አዕምሯችሁ እሱን መተካት ይጀምራል።

መጥፎ ሀሳቡና ትናንትናው ይቀርና አዲሱ ማንነት ይገነባል። ደጋግመን ያሰብነውን እንሆናለን። ለምሳሌ እጃችን ላይ ያለው ስልክ መጀመሪያ ሀሳብ ነበር። ያ ሃሳብ ተመላልሶ ቁስ ሆኖ እጃችን ላይ ገባ። ምንም ነገር ከመገለጡ በፊት አዕምሮ ውስጥ ታስቧል። ሃሳብ ነበር። እኛም ሕይወታችንን፤ ነጋችንን ማሰብ አለብን። ነገር ግን በተቃራኒው ጭንቀት፣ ብሶት ከሆነ ሀሳባችን እሱን ነው በሕይወታችን የምንገልጠው። በቃ! የሚያስጨንቅ ነገር፣ ብሶት ይገጥመናል። ስለዚህ ነጋችንን ብናስብስ? ስለሕልማችን ብቻ ብናስብስ?

ደግሞ አንድ ነገር አትርሱ አዕምሯችንን መቆጣጠር አለብን። መቆጣጠር የምንችለው ደግሞ በጣም ስንደጋግም ነው። መጥፎ ሃሳብ ሲያስብ እጅ ከፈንጅ ስንይዘው ነው። መጥፎ ሀሳብ ሲያስብ አይ! እኔ በጣም ጠንካራ ነኝ፣ እችላለሁ እንደዛ አትለኝም እያላችሁ መሞገት፣ መፃፍ፣ ልክ ሲያስጨንቃችሁ ደግሞ ማመስገን አለባችሁ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአየር መንገዱን ተቋማዊ ግዝፈት የሚያጎላ ተጨማሪ ስኬት!

የብሄራዊ ክብራችን መገለጫ የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአቬሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ከከፍታ በላይ ከፍ ብሎ እየበረረ ያለ የሕዝብ እና የሀገር አለኝታ ነው። አየር መንገዱ አሁን ላይ በአፍሪካ ቀዳሚ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ከ100 አየር መንገዶች 36ኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም መዳረሻዎቹን በማስፋት በሀገር ውስጥ በሚሰጣቸው አገልግሎቶቹ የዜጎች አለኝታ መሆን የቻለ ነው ፡፡

አየር መንገዱ ከምስረታው ጀምሮ ላለፉት 78 ዓመታት የኢትዮጵያን ባንዲራ ከአድማስ በላይ በማውለብለብ የሀገር እና የሕዝብ ባለውለታ ነው። በእነዚህ ዓመታትም ከፍተኛ ውድድር ባለበት የአቬሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ በስኬት መቆየት የቻለ፣ ከሀገር አልፎ የአፍሪካ ኩራት የሆነ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያውያን ሁለንተናዊ ብቃት መሳያ ተደርጎ የሚወሰደው አየር መንገዱ፣ በስሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ አንቱታ ያተረፈ የበረራ ትምህርት ቤት፣ ግዙፍ ሆቴል፣ የአውሮፕላን ጥገና ተቋም፣ ለበረራ የሚያስፈልጉ ምግቦችን የሚያዘጋጅ ድርጅት / ካተሪንግ/ ባለቤት ነው።

መንገደኞችንና ዕቃዎችን በማጓጓዝ በዓለም አቀፍ ፣ በአፍሪካ እና በሀገር ውስጥ በርካታ መዳረሻዎች ያሉት፤ ኢትዮጵያዊ በሆነው መስተንግዶው ከፍተኛ ከበሬታ ያተረፈ እና ተመራጭ የሆነ ፣ በዚህም በየጊዜው በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ የዕውቅና ሽልማቶችን ማግኘት የቻለ ነው።

በኮቪድ 19 ወቅት ሁሉም አየር መንገዶች ሊባል በሚችል መልኩ ሥራ ባቆሙበት ወቅት፣ የአቪየሽን ኢንዱስትሪው ያጋጠመውን ፈተና ወደ መልካም ዕድል በመለወጥ ፣ ለወረርሽኙ ተጠቂዎችና የህክምና ተቋማት መድኃኒትና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በማጓጓዝ ከፍ ያለ ከበሬታን አትርፏል።

ራሱን ዘመኑ በደረሰበት የአቪየሽን ቴክኖሎጂ በማዘመን ፣ ተወዳዳሪነቱን በየጊዜው እያሳደገ፣ ለረጅም ዓመታት በኢንዱስትሪው ውስጥ በስኬት መቆየት የቻለ ነው። አዳዲስ አውሮፕላኖችን ቀድሞ በማዘዝ እና ወደ ሥራ በማስገባት ከሌሎች ገናና አየር መንገዶች በቀዳሚነት የሚጠቀስም ነው።

አየር መንገዱ ሰሞኑን የተረከበው «ኤር ባስ ኤ 350- 1000 ለዚሁ እውነታ ተጨባጭ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። አውሮፕላኑ ወደ ሥራ መግባቱ በአቪየሽን ቴክኖሎጂ ያለውን ቀዳሚ ስፍራም የበለጠ የሚያጠናክርለት እንደሆነ ይታመናል።

አውሮፕላኑ ዘመኑን የዋጁ አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች የተገጠሙለት መሆኑ፣ ለመንገደኞች የበለጠ ምቾት ይዞ መምጣቱ፣ ነዳጅ ቆጣቢ እና በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችልን ብክለት የሚቀንስ መሆኑ፤ አየር መንገዱ ይዞት ለመጣው ስኬት ተጨማሪ ጉልበት የሚሰጠው ነው። ለአፍሪካ የአቪየሽን ኢንዱስትሪ ዘላቂነትም ትልቅ ዕድል ይዞ የመጣ ነው።

ለአፍሪካ የአቪየሽን ዘርፍ አዲስ ደረጃን ይዞ የመጣ፣ የአየር መንገዱን የ2035 ራዕይ ለማሳካት ለሚከናወኑ ተግባሮች ትልቅ አቅም በመሆን እንደሚያገለግል፤ ይህም አየር መንገዱ በአቪየሽን ኢንዱስትሪ ያለውን ከፍታ አስጠብቆ በተሻለ መልኩ ለማስቀጠል የሚያስችለው ነው። የደንበኞቹን ፍላጎት ለማርካት ያለውን ቁርጠኝነትም በተጨባጭ ያመላከተ ነው፡፡

አየር መንገዱ አሁን ላይ በአፍሪካ ትልቁ አየር መንገድ ብቻ ሳይሆን፤ በአፍሪካ ሁለተኛ የሆነውን አየር መንገድ በእጥፍ የሚበልጥ አቅም በመፍጠር ላይ የሚገኝ ፤ በቀጣይ በዓመት ከ100 እስከ 130 ሚሊዮን መንገደኞችን ማስተናገድ የሚችል ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ሲጠናቀቅ ፤ በአፍሪካ ትልቁ አየር መንገድ መሆን ብቻ ሳይሆን፤ ባለትልቁ አውሮፕላን ማረፊያም ይሆናል።

ይህም አየር መንገዱ አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው ክብርና ዝና በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ ወደላቀ ደረጃ የሚያሻግር፣ ለጀመርነው የብልጽግና ጉዞ ስትራቴጂክ አቅም ሆኖ እንዲቀጥል የሚያስችል ተቋማዊ ግዝፈት የሚፈጥር ተጨማሪ የስኬት ታሪክ ምእራፍ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከረሀብ ነጻ የሆነች ዓለም ለመፍጠር …

ራስወርቅ ሙሉጌታ

በዓለም ላይ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ ችግሮች ይልሱት ይቀምሱት ያጡ ሰዎች ቁጥር እያሻቀበ ይገኛል። ሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ ችግሮች ለርሃብ መከሰት መነሾ የሚሆኑ ጉዳዮች የሚተነበዩ ቢሆንም፤ ሳይታሰብ ተከስተው ብዙዎችን ለችጋር የሚያጋልጡ አጋጣሚዎች መኖራቸውም ይታወቃል። መነሻ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ረሀብ ጊዜ አይሰጥምና እነሱን መታደግ ይዋል ይደር የሚያሰኝ ስራ አይሆንም።

ለረሃብ የሚዳረጉ ሰዎች ትናንት በሞቀ በደራ ቤታቸው አብስለው ይበሉ፤ ቀድተው ይጠጡ የነበሩ ናቸው። ረሀብ የእነሱን ደጃፍ የማይነካ ይመስላቸው የነበሩም ብዙዎች ናቸው። በተለይም ከተፈጥሮ ችግሮች እንደ ጎርፍና መሬት መንሸራተት፤ ከሰው ሰራሽ ችግሮች እንደ ጦርነትና ግጭቶች ያሉት ሲከሰቱ ያበሰሉትን እስኪበሉ ጊዜ የማይሰጥ መሆኑን በተደጋጋሚ አይተናል።

ይህም ሆኖ በቅድመ ትንበያ ረሀብ ሊከሰት እንደሚችል ቢታወቅ እንኳን ለመከላከልም ሆነ ለችግር ታጋላጮችን ለመታደግ የሚሰሩ ሥራዎች የሚደርሰውን ጉዳት መቶ በመቶ ለማስቀረት የሚችሉበት እድል በጣም ጠባብ ነው። የሰው ልጅ ለርሃብ የሚጋለጥበትን እድል ሙሉ ለሙሉ የማስቀረቱ ጉዳይ ህልም ቢሆንም ለርሃብ የተጋለጡ ሰዎችን ለሞትና ለከፋ ጉዳት ሳይዳረጉ የመታደጉ አቅም ግን በራሱ በሰው እጅ ያለ እድል ነው።

ለዚህ ደግሞ ከቀዳሚዎቹ መፍትሄዎች መካከል በግብርና ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤ በድህረ ምርት ወቅት የሚከሰቱ የምርት ብክነቶችን መቀነስ እና በዘመናዊ መንገድ በመታገዝ ለረዥም ጊዜ ሳይበላሹ የሚቀመጡ ምርቶችን ማዘጋጀትና የመጠባበቂያ ክምችትን ማሳደግ ይጠቀሳሉ። በቅርቡ በተካሄደው «ከረሀብ ነጻ ዓለም» ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ እየተነሱ ያሉ ሃሳቦችም በግልጽ የሚያመላክቱት ይህንኑ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያን ብቻ እንደ ምሳሌ ብንወስድ ከላይ ያነሳናቸውን ሃሳቦች የሚያጠናክርልን መረጃ ማግኘት እንችላለን።

«ከረሀብ ነጻ ዓለም» በተሰኘው መድረክ የተገለጹ መረጃዎች እንዳመላከቱት፤ በኢትዮጵያ በየዓመቱ አርባ ስድስት ሚሊዮን ሰው መመገብ የሚችል ምርት በድህረ ሰብል ወቅት በአግባቡ ባለመሰብሰቡ ይባክናል። ይህ አሀዝ በሀገሪቱ በየዓመቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ (የእለት ጉርስ) ከሚያስፈልጋቸው ተረጂዎች ቁጥር አንጻር ሲታይ በእጅጉ የበዛ ነው። ባጭሩ ድህረ ምርት ብክነትን ብቻ መከላከል የምንችልበትን እድል ብንጠቀም በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ ችግሮች ለረሀብ የሚጋለጡ ዜጎቻችንን ለመታደግ ሌሎችን ደጅ መጥናት አይጠበቅብንም ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ከላይ የተጠቀሰውን አሀዝ መነሻ በማድረግ ያለማጋነን ቢያንስ የሶስት የጎረቤት ሀገራት ዜጎችን ለመቀለብ የሚያስችል ምርት በየዓመቱ እያባከንን መሆኑን መገመት አይከብድም። ጉዳዩ በዚህ ደረጃ ትኩረት ማግኘትና የሁሉንም ተሳትፎ ባካተተ መልኩ ሊሰራበት የሚገባ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የድህረ ምርት ብክነትን በመከላከል ይህን ያህል አቅም መፍጠር የምንችል ከሆነ ሌሎች ግብርናውን የሚያሳድጉ መንገዶችን አሟጠን መጠቀም ብንችል ምን ሊፈጠር እንደሚችል ማሰቡ ቀላል ነው።

ለምሳሌ በየአካባቢው ጦም የሚያድሩ መሬቶችን በሰብል መሸፈን ቢቻል፤ አቅም በፈቀደ አጠቃላይ የግብርና ስራው በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ማከናወን ቢቻል፤ ኩታ ገጠም እርሻ ማስፋፋት ቢቻል፤ የግብርና ምርቶችን በኢንዱስትሪ በመደገፍ እሴት ጨምሮ ለሀገር ውስጥ ሆነ ለውጪ ገበያ ለማቅረብ ቢሰራ ውጤቱ የሚያስጎመዠ ነው። እዚህ ላይ ሌላው ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ የግብርና ዘርፉን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማሳደግ ከላይ ከተዘረዘሩት በላይ ሰፊ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ነው።

ለምሳሌ «ከረሀብ ነጻ ዓለም» ዓለም መፍጠር ማለት ለእለት ጉርስ ሆድን መሙላት ብቻ ተደርጎ መወሰድ ያለበት አይመስለኝም። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የጤና መጓደል ጉዳይ ሲነሳ እንደ ማህበረሰብ ቀዳሚ ምክንያት ተደርገው ከሚወሰዱት ምክንያቶች መካከል በቂ ምግብ አለማግኘት መሆኑ ይታወቃል። በተለይም በህጻናት እድገት ላይ ከመቀንጨር ጀምሮ ህይወታቸውን ሙሉ ለሚከተሉ ችግሮች እየተዳረጉ ያሉት በለጋ እድሜያቸው በቂና የተመጣጠነ ምግብ ባለማግኘታቸው ነው።

**በኢትዮጵያ በየዓመቱ አርባ ስድስት ሚሊዮን ሰው መመገብ የሚችል ምርት በድህረ ሰብል ወቅት በአግባቡ ባለመሰብሰቡ ይባክናል**

ይህንን ተከትሎ ቤተሰብ ለውጣ ውረድ እና ለገንዘብ ወጪ ከመዳረጉ ባለፈ መንግሥት በከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ የህክምና ቁሳቀስና መድኃኒት እንዲያስገባ የሚገደድ መሆኑ የችግሩን ተሻጋሪነት አመላካች ነው። በሌላ በኩል አሁን ባለው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የግብርናው ዘርፍ አብዛኛውን ሰው የሚያሳትፍ መሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን መስኩ በዘመናዊ መንገድ የሚመራ ባለመሆኑ ከአድካሚነቱ እና ከልፋቱ አንጻር በቂ ትርፍ እየተገኘበት አይደለም።

በዚህም የተነሳ አብዛኛው የአርሶ አደር ልጅ በእርሻ ሥራ ላይ የሚቆየው በከተማ ለመኖር የሚያስችለውን አማራጭ እስኪያገኝ ድረስ ብቻ ነው። ምን አልባትም ብዙሀኑ የአርሶ አደር ልጅ በየተገኘው አጋጣሚ በአካባቢው ወዳሉ ከተሞች ወይንም ወደ አዲስ አበባ በማቅናት በግለሰብ ቤትና በቀን ሰራተኝነት ህይወቱን ለመግፋት ይገደዳል። ቀሪው ደግሞ በህጋዊም ሆነ በህገወጥ መንገድ በአየርም በባህርም ወደ ሌሎች ሀገራት በመሰደድ ለአስከፊ ህይወት ይዳረጋል።

የዚህ ሁሉ ጉዞ መዳረሻ ራስን ብሎም ቤተሰብን ከረሀብ ለመታደግና የተሻለ ኑሮ ለመኖር ነው። በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ለግብርና ትኩረት መስጠትና ግብርናውን ማዘመን በተዘዋዋሪ ከላይ ለተነሱት ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። እዚህ ላይ በጽሁፌ ውስጥ ለግብርናው ትኩረት መስጠት… ግብርናውን ማዘመን እያልኩ ያስቀመጥኳቸው ቃላትና ሀረጋት ድንች እንደመላጥ ቀላል አለመሆናቸውን አምናለሁ።

በትንሹ የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን ዞር ብለን ብንከልሰው የዛሬ ሃምሳ ዓመት ግድም የንጉሱን ሥርዓት በማስቆም ለውጥ ለማምጣት ሲሯሯጡ የነበሩት አካላት በርካታ ጥያቄዎችን ያነገቡ ነበሩ። ከእነዚህም ለውጥ የሚፈልጉ ሀገራዊ ጉዳዮች መካከል የአርሶ አደሩ ልፋትና ተጠቃሚነት ተመጣጣኝ አይደለም የሚለው ቀዳሚው ነበር። ለውጥ ፈላጊዎቹን የተኩትም ቢሆኑ እንደ ሀገር ትኩረት ከሚሹ ቀዳሚ አጀንዳዎች ተርታ ግብርናን በማዘመን አርሶና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረግና ሀገርን ከልመና ማላቀቅ ቀዳሚ እቅዳቸው ነበር።

በቅርቡም የተጀመረው አዲሱ የለውጥ እንቅስቃሴ ከመቼውም ጊዜ በላይ ለአርሶ አደሩ ብሎም አጠቃላይ ለአረንጓዴ ልማት ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን እያየን ነው። ዛሬም የብዙኃኑ አርሶና አርብቶ አደር እጣ ፈንታ በየእርሻ ማሳው በሬና ፈረስ ከመንተት የተላቀቀ ባይሆንም፤ ግብርናውን ከጓሮ አትክልት ልማት አንስቶ በማዘመን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እና አርሶና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረግ አማራጭ የሌለው መዳረሻችን በመሆኑ ሁላንችም ትኩረት ልንሰጣው ይገባል።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆአስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## በፅኑ ብርታት- ካንሰርን ድል መንሳት

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ገና በልጅነታቸው እናታቸውን በሞት ያጡት ልጆች አስተዳደጋቸው ሀዘን የሞላው ነበር። ወጣቷ እናት እነሱን በወጉ ሳታሳድግ፣ ዓለም ሲሳያቸው ሳታይ ድንገቴው ሞት ነጥቋታል። ይህ እውነት ለትንንሾቹ ልጆች ከሰቀቀን በላይ ነው፡፡

ልጆቹ ዛሬም ሞቷን እያመኑት አይደለም። አሁንም የእናታቸውን ውሎ መግባት ይሻሉ። ራሳቸውን እየዳበሰች፣ ዓይናቸውን በስስት እያየች በፍቅር እንድትጠራቸው ይናፍቃሉ። ሁሌም የእናት ጠረኗ ውል ይላቸዋል። ድምጽዋ ይሰማቸዋል። በልጅነት እናትን በሞት ማጣት ልብ ይሰብራል። ሆድ ያስብሳል፣ ይህ ዕድሜ ያለ እናት ሕይወት የሚጎድልበት፣ ኑሮ በእጅጉ የሚከብድበት ነው፡፡

**ሕይወት…**

እናቷን በልጅነት ዕድሜዋ ያጣችው ሕይወት ከታላቅና ታናሽ እህት ወንድሞቿ ጋር ይህን የመከራን ግዜ ኖራዋለች። እናታቸው ከሞተች ወዲህ ሁሉም በፈተና መሀል ተመላልሰዋል። የዛኔ ሕይወት በልጅነት ዕድሜዋ ስለእናቷ ሞት ሲወራ ምክንያቱን ጭምር ስትሰማው አድጋለች። እናታቸው በካንሰር ታማና ተሰቃይታ ብታልፍም በወቅቱ ግን ሕክምና አልወሰደችም።

ሕይወት ይህን እውነት ካወቀች ወዲህ ‹‹ካንሰር›› ይሉትን ቃል ስትፈራው፣ ስትጠላው ኖራለች። ይህ ሕመም እናቷን ከእሷ ነጥሎ ወስዷል። እህት ወንድሞቿን አሳቆ፣ በናፍቆት፣ አራቁቷል። እሷ በእናትና ልጅ መሀል የሰላ መቀስ ስለሆነው ካንሰር ያላት ምስል በዓዕምሮዋ



የገዘፈ፣ በማንነቷ ጎልቶ የተጻፈ ታሪክ ነው፡፡

**ከዓመታት በኋላ…**

እነሆ! ልጅነት እንደ ጥላ፣ እንደጤዛ ሆኖ አለፈ። በእናት ፍቆትና ፍቅር ተቋጥሮ፣ በሀዘን ትካዜ ተላብሶ የኋሊት የቀረው ይህ ግዜ አይረሴ ትዝታዎችን አዝሏል። እነዚህ መልኮች የሕይወት በጎ፣ ክፉ ገጽታዎች ናቸው። በእሷ ልቦና ጠብቀው ታስረዋል። በዋዛ የማይረሱ፣ በቀላሉ የማይተዉ ሀቆችን ይዘዋል።

ሕይወት ዛሬ ትልቅ ሰው ሆናለች። ልጅነቷ ከእናቷ ማንነት ተዛምዶ ቢጻፍም የራሷን ኑሮ ልትመሰርት ግድ ሆኗል። ትዳር ይዛ ጎጆ ወጥታለች። የልጆች እናት ከሆነች ወዲህ ደግሞ ብዙ ታስባለች ። በእሷ ያጣችውን የእናት ፍቅር በእነሱ አሻግራ ስታየው ውስጧ ይረበሻል። ሁሌም ክፉ እንዳታይ፣ እንዳትሰማ፣ ትመኛለች። ልጆቿ ለእሷ የጎደለ ዓለሟን የሚሞሉ፣ ያለፈ ታሪኳን የሚያስረሱ ምክንያት ናቸው።

**ዳባሾቹ ጣቶች…**

አንድ ቀን ሕይወት ከቤቷ ልጇን ታቅፋ ተቀምጣለች። ከወለደች ጥቂት ወራት አልፈዋል። የስድስት ወር ዕድሜ ያላት ጨቅላ እንደልማዷ እጆቿን ከእናቷ ጡት ጣል አድርጋ እየጠባች ነው። ሕይወት በድንገት ከአንድ ጡቷ ላይ የተለየ ምልክት ያየች መሰላት። በጥርጣሬ እጇን ሰደድ አድርጋ ብይ መሳዩን ጠጣር በስሱ ዳበሰችው። ሁኔታውን አላመነችም። እንደደነገጠች፣ እንደፈራች ዳግም ጣቶቿን እየቀያየረች ዳሰሰች፣ ዳሰሰች…፡ ፡፡

አሁንም የጣጠረ፣ ከዚህ ቀድሞ አይታው፣ ነክታው የማይታወቅ ነገር በእጆቿ መሀል መኖሩን አረጋገጠች። ሕይወት በስሙ ስትፈራውና ስትሸሸው የነበረው አስደንጋጭ ስም በዓይምሮዋ ውል አለባት። ‹‹ካንሰር››። ታመው የማይድኑት ክፉ ደዌ፣ እናትን ከልጆች የሚለያይ፣ ሕይወትን በአጭሩ የሚያስቀር ነጣቂ ሌባ።

ሕይወት ምልክቱን በጣቶቿ ዳብሳ ካረጋገጠች በኋላ ወደ ምርመራ እስክትሄድ አልቆየችም። በጡቷ ላይ ያየችው ነገር ‹‹ካንሰር›› ለመሆኑ በፍጹም ልቧ አምና ተቀበለች። ያለአንዳች ጥርጣሬ ለውስጧ ሀቁን ያቀበለችው ወይዘሮ ለቀናት ስጋቷን ይዛ በዝምታ መቀመጥ ውሳኔዋ ሆነ።

እናት ይህን እውነት ካወቀች ወዲህ ፈጽሞ በባህርይዋ ለውጥ አልታየም። ችግሯ ጎልቶ እንዳይወጣ በእርምጃዋ ሁሉ መጠንቀቅ ያዘች። እንደቀድሞው ለልጇ በረከቷን አልነፈገቻትም። ባሻት ሰዓት ጡቷን አውጥታ ታጠባታለች። ስታለቅስ እንደ ብሶቷ አብራት አታለቅስም። ሀዘን፣ ጭንቀቷን በውስጧ አምቃ ትብሰለሰላለች፡፡

ሕይወት በዝምታ ውስጥ መጓዟን ቀጥላለች። ትንሽዋ ዕባጭ አሁንም ከቀኝ ጡቷ ላይ እንደተቀመጠች ነው። ብይ መሳይ፣ የማትለሰልስ፣ የማታሟልጭ ጠጣር። ሕጻንዋ በዕድሜ እያደገች ነው። በየጊዜው የእናቷን ጡት ማግኘት ትሻለች። እናት ጥርጣሬ ቢገባትም ለልጇ ጡት መስጠቷን አልተወችም፡፡

ልጇ አንድ ዓመት ሲሞላት የጡቷ ወተት ቀነሰ። ይህን ተከትሎ ምልክት የታየበት ጡት ልዩነቱ ይስተዋል ጀመር። በየቀኑ እድገቱ ለውጥ እያመጣ፣ መጠኑ እየጨመረ ሄደ። ይህኔ ሕይወት በእጅጉ ጨነቃት። አሁን እስከዛሬ ደብቃ የያዘችውን ሚስጥር ለአንድ ሰው መተንፈስ፣ .ማካፈል ይኖርባታል። ወይዘሮዋ ለቀናት ከራስዋ ጋር ስትወዛገብ ቆየች። ከቀናት በአንዱ ግን ባለቤቷን ፊት ለፊት አስቀምጣ የሆነውን ሁሉ አንድ በአንድ ነገረችው፡፡

ባለቤቷ የሕይወትን ቃል በጥሞና አደመጠ። ቢደነግጥም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ከራሷ እንዲመጣ ፈልጓል። ውሳኔው ፈጣንና አይቀሬ የሚባል ነው። ወደ ሕክምና ዘልቆ ተገቢውን ምርመራ ማካሄድ። ይህን ጉዳይ ሕይወትም ብትሆን አሳምራ ታውቀዋለች። ቃሉ ከባሏ አንደበት ከመውጣቱ በፊት ግን በተለየ ማስጠንቀቂያ አገደችው፡፡

**ወደ ገጽ 17 ዞሯል**

# በፅኑ ብርታት- ካንሰርን. . .

ከገጽ 16 የዞረ

ባል በግርምታ እያስተዋላት ለምንና እንዴት? ሲል ጠየቀ። የሚስቱ ምላሽ አጭርና ፈጣን ነበር። «እኔ በፍጹም ወደ ሀኪም ቤት መሄድ «አልፈልግም» አለችው። ባል አሁንም ተጨማሪ ማብራሪያ ፈልጓል። ካልተመረመረች፣ ካልታከመች ዕጣ ፈንታዋ እያሳሰበው ነው። መልሶ ይህንኑ ስጋት በጥያቄ ደገመላት። ሕይወት ለምላሹ አልዘገየችም። ሆስፒታል ሄዳ፣ ከመመርመር፣ ይልቅ ለራሷ ብትጸልይና በሌሎችም ብታጸልይ እንደሚሻል አስረዳችው፡፡

ባለቤቷ ሀሳቧን አልተጋፋም። ሁሉም ውሳኔ ከራሷ እስኪመጣ መታገስ እንዳለበት ወሰነ። ቀናቶች እንደዋዛ አንድ ሁለት ብለው ቆጠሩ። ከወይዘሮዋ የመጣ አዲስ ውሳኔ የለም።

**አጋጣሚው...**

ከቀናት በአንዱ ወይዘሮዋ ከአንድ ሆስፒታል ተገኘች። በስፍራው የመሄዷ ምክንያት አልጋ ይዛ የተኛችን አንዲት ሴት ለመጠየቅ ነበር። እንደ ልምድና ወጉ ሕመምተኛዋን ጠጋ ብላ ስለጤናዋ አወጋቻት። በንግግራቸው መሀል ድንገት የሰማችው እውነት ግን ወደ ራሷ ሊመልሳት ግድ አለ። አጋጣሚ ሆኖ የሴትዮዋ ሕመም የጡት ካንሰር ነበር።

ሕይወት ይህን ካወቀች በኋላ ከራሷ ጋር አወጋች። እሷ ደብቃ የያዘችው ሚስጥር አንድ ቀን ለአደጋ እንደሚያጋልጣት አልጠፋትም። ያለፋታ ማሰብ መጨነቋ ቀጠለ። ያለፈችበት የልጅነት መንገድ፣ የእናቷ ሕመምና ስቃይ፣ የእሷ እጣፈንታና የቤተሰቦቿ ሁኔታ በዓይነ ሕሊናዋ ተመላለሰ። አሁን ውስጧ በእጅጉ እየሞገታት ነው።

ሕይወት በድንገት ዞር ስትል ከአንዲት ነርስ ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጨች። ነርሷ በትምህርት ዓለም የምታውቃት አብሮ አደጓ ነች። አንዳች ነገር ውስጧን ሲቀለው ተሰማት። ከብይ መጠን አልፎ የዕንቁላል ያህል አድጎ የሚሰማት ዕብጠት ዛሬም ከእሷ ጋር ነው፡፡

ሁለቱ ሴቶች ሰላም ከተባባሉ በኋለ ሕይወት ለባልንጀራዋ ስጋቷን ገለጸችላት። በጡቷ ላይ ያለውን ምልክት አሳይታም የሆነውን ሁሉ ተናገረች። የጤና ባለሙያዋ ጉዳዩን እንደዋዛ አላየችውም። ስለመዘግየቷ፣ ስለዝምታዋ ወቅሳ በአስቸኳይ የጤና ምርመራ ማድረግ እንደሚኖርባት አሳሰበቻት፡፡

**የነበረው - እንደነበረ ...**

ሕይወት ከባልንጀራዋ ከተለየች በኋላ ሁሉን ረስታ በቀድሞ መንገዷ ቀጠለች። ስለራሷ ማሰብ፣ ስለጤናዋ መጨነቅ ተወች። ለቀናት የነበረው እንደነበረው ሆኖ ቀጠለ። ከእሷና ከባለቤቷ በቀር ሚስጥሯን የሚያውቅ የለምና በነገሮች አልተጨነቀችም፡፡

ከቀናት በአንዱ ማለዳ የእጅ ስልኳ በድንገት አንቃጨለ። አንስታ አየችው። የምታውቀው ቁጥር አይደለም። ቢሆንም ጥሪውን አልገፋችም። ወደ ጆሮዋ አስጠግታ «ሀሎ» ስትል ምላሽ ሰጠች። በቅርቡ ያገኘቻት ነርስ ጓደኛዋ ነበረች። የስልክ ቁጥሯን ከምታውቃቸው ሰዎች መውሰዷን ነገረቻት፡፡

ነርሷ ቀጭን ትዕዛዝ ስትሰጣት አልዘገየችም። በማግስቱ ጠዋት በአስቸኳይ ከሆስፒታሉ ተገኝታ ምርመራውን እንድታደርግ አሳሰበቻት። ሕይወት እንደቀድሞው «እምቢኝ» ልትል አልደፈረችም። እንደምትመጣ ቃል ገብታ ስልኩን በስንብት ዘጋች። ሌቱ አልፎ ማለዳ ሆነ። ጨለማው መንጋቱ በወፎች ጫጫታ ተበሰረ።

ሕይወት «እንድትመጪ» በተባለችበት ጠዋት ከሆስፒታሉ ስትደርስ በውጣ ውረድ አልተቸገረችም። ነርስ ባልንጀራዋ ሁሉን አመቻችታ ጠበቀቻት። ዕለቱን ተገቢውን የጤና ምርመራ በወጉ ወስዳ አጠናቀቀች። ሁሉን ስትጨርስ የውጤቱን መልስ ለመስማት ቀነ- ቀጠሮ ወስዳ ነበር፡፡

**የምርመራው ውጤት...**

እነሆ! የቁርጡ ቀን ደርሷል። አሁን ወይዘሮዋ ከሀኪሟ ፊት ቀርባለች። እሷ ሁሉን ለመቀበል ዝግጁ መሆኗን ለራሷ ስትነግረው ቆይታለች። በግል ሙከራዋ ባደረገችው ጥረት ደግሞ ሊሆን የሚችለውን ስትገምት ነበር። እንዲያም ሆኖ ትክክለኛውን ውጤት ከተገቢው አካል ማወቅና መስማት አለባት፡፡

ዕለቱን ከሀኪሞች አንደበት የተሰማው የምርመራ ውጤት እንደተገመተው ሆነ። ሕይወት አንድ ጡቷ በካንሰር ተጠቅቷል። ወይዘሮዋ ይህን ውጤት አስቀድማ የገመተችው ቢሆንም እውነቱን አምና ለመቀበል ተሳናት። ለመቆም መቀመጥ እስኪሳናት ተንገዳገደች። ይህ ግዜ ለሕይወት እጅግ ከባድና ፈታኝ ነበር።

ውሎ አድሮ ራሷን ለማረጋጋት ሞከረች። በቀላሉ አልሆነላትም። መለስ ብላ ወደልጅነቷ ተጓዘች። እናቷ የሞቱት በካንሰር ታመው ነበር። በወቅቱ ሕክምና ያለማድረቻቸውን ታውቃለች። እንዲህ ከሆነ በርካታ ዓመታት አልፈዋል። ሕይወት ለቤቱ የመጨረሻ ልጅ ነች። በቤተሰቡ ታሪክ የእናቷ ዕጣ ፈንታ የተደገመው ግን በእሷ ላይ ሆኗል።

የሶስት ልጆች እናት ለሆነችው ሕይወት ይህን እውነት እንደዋዛ አምኖ መቀበሉ ይከብዳል። የእሷ አስተዳደግ ነፍስ ባላወቁ ልጆቿ እንዲደገም አትሻም። ጠዋት ማታ በለቅሶ፣ በሀዘንና ትካዜ አንገቷን ደፋች። አሁን ከአንድ ውሳኔ የምትደርስበት ግዜ ነው። ስለራሷ ጤና፣ ስለ ልጆቿ መኖር ታስባለች። እንደትናንቱ በዕምቢታ፣ በዝምታ መቀጠል የለባትም፡፡

ሕይወት የሚሆነውን ሁሉ በይሁንታ ከወሰነች በኋላ ለሕክምናው ራሷን አዘጋጀች። ከሀኪሞቿ የምትባለውን ለመፈጸምም ፈቃደኛ ሆነች። በወቅቱ ጡቷ ላይ ያለው ዕባጭ በቀላሉ ወጥቶ ሕይወቷ እንደሚቀጥል ገምታ ነበር። ከዚህ በኋላ ቀኝ ጡቷ ሙሉ ለሙላ እንደሚነሳ ሲነገራት ግን ክፉኛ ደነገጠች፡፡

ጡት ማለት ለሴት ልጅ ልዩ መገለጫ ነው። ይህ ተፈጥሮ ከውበት በላይ ሆኖ ሕይወትን ይታደጋል፤ የውስጡ በረከት የእናት ልጅ ፍቅር ማሰሪያ ገመድ ነው። ሕይወት የምትሰማው ሁሉ ከአቅሟ በላይ ሆኗል። ቀጥሎ ያለውን ሀቅ አንድ በአንድ እስከታውቅ አትጠብቅም። ይህ ከመሆኑ በፊት በሩጫ ስፍራውን ለቃ ወጣች፡፡

በወቅቱ ሕይወት የተሰማትን ለማስታወስ ይከብዳታል። በአካል ትኑር፣ ትሙት፣ ትውደቅ፣ ትነሳ የምታውቀው አልነበረም። በአየር ላይ የተንሳፈፈች ያህል፣ እየታያት ነው። ማንም ደርሶ ቢያጽናናት፣ አይዞሽ ብሎ ቢያቅፋት የምታይ፣ የምትሰማ አይደለችም። ልጆቿን እያሰበች ነው። በእሷ ስር የምታስተዳድራቸው ቤተሰቦች ውል ይሏት ይዘዋል። ወይዘሮዋ ከዚህ በኋላ ቤቷ ባትገባ ማንንም ባታይ፣ ትወዳለች። እንደነገሩ ኑሮ የጀመረችው ሕይወት በብዙ ጉዳዮች ጎዶሎዋቿ በረከቱ። ቤቷ አስጠላት፣ ልጆቿን መንከበካብ፣ በወጉ ከሰው ማውጋት ተወች፡፡

**የተስፋ ቃል...**

የሕክምና ባለሙያዎች በየግዜው በአሳዛኝ አጋጣሚዎች ያልፋሉ። ታካሚዎቹ ሲድኑላቸው የሚረኩትን ያህል ጉዳታቸውም ይሰማቸዋል። የዛን ቀን የሕይወትን ምርመራ የያዘው ዶክተር የድንጋጤ ሩጫዋን ባየ ግዜ በዓይኑ ብቻ አልሸኛትም። እስከ መውጫው በር ከኋላዋ ተከትሏታል። እሷ ግን ወደቀደመው ውሳኔዋ ለመመለስ ፈጥና ነበር። ደጋግማ «አልታከምም » ስትል ቁርጡን ነግራዋለች።

በሌላ ቀን ይኸው ሀኪሟ በመኪና እያለፈ ሕይወትን ከመንገድ ላይ አያት። እንዳላየ ፊቱን ማዞር አልፈለገም። ስለእሷ ዕንቅልፍና ሰላም ካጣ ቆይቷል። ገና ሲያያት ከእሷ አንድ ቃል ጠብቋል። መኪናውን አቁሞ መታከም ያለመታከሟን ጠየቃት። መልሳ የፊቱን ሀሳቧን ደገመችለት። «አልታከምም፣ ፈጽሞም አልመጣም» አለችው፡፡

አሁንም ጊዜያቶች እየነጎዱ ነው። ከምርመራዋ በኋላ ስምንት ወራትን የቆጠረችው ሕይወት አካል አይምሮዋ እየደከመ፣ ሁኔታዎች እየሰለቿት ነው። ከቀናት በአንዱ ግን ነባር ውሳኔዋ ሊሻር ቀኑ ደረሰ። እምቢታዋን ትታ ለሕክምናው እጅ ሰጠች። ሀኪሟ ፊት በቀረበች ግዜ የዓይኖቿ ዕንባ አልደረቁም፤ ያለማቋረጥ ታለቅስ፣ ታነባ ነበር፡፡

በየአፍታው በዕንባ የምትታጠበውን ወይዘሮ ያስተዋለው ሀኪም። በተስፋ የፈካ ገጽታውን ይዞ ወደእርሷ ቀረበ። በእግሮቿ ስር ተንበርክኮም «አይዞሽ እኔ በአግባቡ አክሜ አድንሻለሁ» ሲል ቃል ገባላት። ሕይወት ከዚህ ቃል በኋላ አዝላው የቆየችው ከባድ ጭንቀት ከትከሻዋ ሲወድቅ ተሰማት። ውስጧ በተስፋ ረሰረሰ፣ የመዳን ህልሟ ዕውን ሆኖ ታያት፡፡

**እንዳያልፉት የለም...**

ቀጣዩ ሕክምና ከመካሄዱ በፊት የሚሆነው ሁሉ ተነገራት። ዳግመኛ ምርመራ ማካሄድ ግድ እንደሚል አወቀች። ሕይወት ጭንቀቷ አገረሸባት። ያሳለፈችው ስቃይ በፊቷ ተመላለሰ። ምርመራውን ብትጠላውም ከባዱን ችግር ልትጋፈጥ መሆኑን ስታውቅ ራሷን አበረታች። ግራ ቀኝ አይታ ወሰነች። ጥንካሬን ለብሳ፣ በጽኑ ልብ ቆመች። ካንሰርን በብርታት ታግላ ድል ልትነሳው ቆረጠች፡፡

አሁን ሕይወት እንደትናንቱ በብቸኝነት አትጓዝም። የገጠማትን ሁሉ ለወዳጅ ዘመድ፣ ለጓደኛ ጎረቤት ነግራለች። እንዲህ ማድረጓ ብዙዎች በገንዘብ እንዲያግዟት በሀሳብ እንዲያበረቷት ምክንያት ሆኗል። ሕይወት ኬሞ ቴራፒውን በጽናት ካጠናቀቀች በኋላ ተጨማሪ የምትወስደው ሕክምና ይቀጥላል። እሱን ስትጀምር ከበዳት፣ አልቻለችም። ውስጧ የተረታ ያህል ተንገዳገደ። ግን አልወደቀችም፡፡

**ዛሬን ...**

አሁን ሕይወት በአዲስ ጎዳና እየተራመደች ነው። ትናንት ባለመመርመር ያባከነችው ግዜ አይረሴ ትምህርት ሆኖ በምሳሌነት ይታወሳል። እሷ ካንሰርን በጥንካሬ ታክማ ስትድን በበርካታ እሾኅማ መንገዶች ተመላልሳ ነው። ዛሬ ግን የዚህ መንገድ ሰበብ በርካታ ነፍሶችን አትርፏል። ትናንት የቆጠረቻቸው የማይነጉ ሌቶች፣ የማያልፉ የቀን ጨለማዎች ዛሬ ግራ ለገባቸው ሁሉ ብርሀን መፈንጠቅ ጀምረዋል።

እነሆ! ያጠናቀቅነው ወርሀ- ጥቅምት የጡት ካንሰር ወር ሆኖ ይከበራል። በዚህ ወቅት ሕይወትን የመሰሉ በጡት ካንሰር የተፈተኑ ብርቱዎች ጥንካሬያቸው ይመሰከራል። ለእነዚህ ጽኑ ሴቶች እያንዳንዷ ደቂቃ የተለየ ትርጉም አላት። ትናንትን እንደታሪክ፣ ዛሬን እንደ ዕድል፤ ነገን እንደ ተስፋ ይቆጥሩታል።

# መሠረተ ልማት

# ‹‹የሀገራችን ከተሞች ዋነኛው ችግር ከተማ እየቀደመ፣ እኛ መከተላችን ነው››

\- አቶ ተፈራ በዬራ

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የከተማና መሠረተ ልማት ተመራማሪ

በኃይሉ አበራ

ኢትዮጵያ ከተሜነት በፍጥነት እየተስፋፋባቸው ከሚገኙ ሀገሮች አንዷ ናት። መረጃዎች የሚያመለክቱትም ይህንኑ ነው፤ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የኢትዮጵያ የከተሞች ምጣኔ 25 በመቶ አካባቢ ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። የከተሜነት መስፋፋት ፍጥነቱም አምስት ነጥብ አራት በመቶ ነው። ይህም የኢትዮጵያ ከተሞች በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈጣን የከተሞች እድገት ከሚታይባቸው ሀገራት መካካል መሆናቸውን ያመለክታል።

ከተሞች በእቅድ እና በፕላን እንዲመሩ በማድረግ በኩል ግን ክፍተቶች ይስተዋላሉ። ክፍተቶቹን ለመሙላት የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ከችግሩ ስፋት ጋር በተያያዘ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት ሳይቻል ቆይቷል።

በአዲስ አበባ ከተማና በክልል ከተሞች የኮሪደር ልማት ማካሄድ ያስፈለገበት አንዱ ምክንያትም ይሄው እንደሆነ ይገለጻል። በኮሪደር ልማቱ መሰረተ ልማቶችን ከተሞችን በሚመጥን መልኩ መዘርጋት፣ አረንጓዴ ስፍራዎችን ማልማት፣ ለነዋሪዎች ምቹ የመኖሪያ አካባቢ መፍጠር ስራዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ።

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የከተማና መሠረተ ልማት ተመራማሪ አቶ ተፈራ በዬራ ከተማ በ21ኛው ክፍለዘመን ትልቁ የኢኮኖሚ መሰረት ተብሎ እንደሚወሰድ ይናገራሉ። ከተሞች ይሄንን ሚናቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ደግሞ በፕላን መመራት ይኖርባቸዋል ሲሉ ያስገነዝባሉ። የሚጠበቅባቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ለአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት እድገት ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንዲሆን በፕላን የግድ መመራት ይኖርባቸዋል። ከተሞች ሲስፋፉ የሚቀጥለው ትውልድ ጭምር ታሳቢ መደረግ ይኖርበታል። ትክክለኛ የከተማነት ሚናቸውን እንዲወጡ በእቅድ መመራት አለባቸው፡፡

የኢትዮጵያ ከተሞች አምስት ነጥብ አራት አካባቢ የሆነ ፈጣን የከተሜነት እድገት የሚታይባቸው መሆናቸውን ጠቅሰው፤ እነዚህ ከተሞች በፕላን ካልተመሩ ያለውን ህዝብ ለማስተናገድም ችግሮች የሚፈጥሩ ይሆናሉ ይላሉ። ከተሞቹ አስተዋፅኦ ማበርከት ሲጠበቅባቸው በተለያዩ ችግሮች የተወሳሰቡ ይሆኑና ችግር ፈጣሪ ይሆናሉ ሲሉ ያመለክታሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን በከተሞቻችን ከሚታዩ መሰረታዊ ችግሮች መካከል የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ በእቅድ አለመመራት፣ የከተሞች ያለ ቁጥጥር ወደጎን ማደግ፣ የትራፊክ መጨናነቅ፣ የስራ አጥነት መብዛት እንዲሁም ደካማ የአካባቢ ንፅህና እና የቆሻሻ አወጋገድ ይጠቀሳሉ። እነዚህ ችግሮች ተደማምረው በከተሞቻችን ለሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት የሚፈለግባቸውን ሚና እንዳይወጡ እያደረጋቸው ይገኛል።

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ መንግሥት አሁን እንደ ፕላን ስትራቴጂ እየተጠቀመ የሚገኘው ኮሪደር ልማት ስራዎችን ማከናወን መሆኑን ጠቅሰው፣ ቀደም ሲልም የስማርት ከተማ እቅድ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩን ጠቁመዋል። ከልማቱ ጠቀሜታዎች መካከል ከተማ ውስጥ ተሽከርካሪ ያለምንም ትራፊክ መጨናነቅ መንቀሳቀስ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አንዱ እንደሆነ ገልጸው፣ የስማርት ከተማ ስራውን ወደ ተግባር ለመለወጥ የኮሪደር ልማት እገዛ ከፍተኛ መሆኑን አመላክተዋል።

አቶ ተፈራ እንዳብራሩት ፤ የኢትዮጵያ አብዛኛዎቹ ትላልቅ ከተሞች ጭምር የተመሰረቱበት በፕላን ባልተመራ ሁኔታ ነው። መንገዶች በጣም ጠባብና የተጨናነቁ መሆናቸውም ይህንን ያመለክታል። ለብስክሌት የሚሆን መንገድ በአግባቡ አልተገነባም፤ ሰፊ የእግረኛ መንገድ እንዲሁም በቂ የመናፈሻ አረንጋዴ ስፍራዎች የሉም።

የኮሪደር ልማቱ መተግበር እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካ እና የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ብትሆንም በቂ የህዝብ መፀዳጃዎች የሏትም። የህዝብ መጸዳጃ በበቂ ሁኔታ ባለመሟላቱና መጸዳጃ ቤት በተወሰነ ርቀት ባለመኖሩ ተፈጥሮአዊ ለሆነው ጉዳይ በትክክል ምላሽ እየተሰጠ አልነበረም።



የከተማዋ እድገት ይህንንም የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባህሪ ከግምት ባስገባ መልኩ በአግባቡ ማስተናገድ እንዳልተቻለ አስታወሰው፤ ይህንን ጨምሮ በከተማዋ ያሉ የመሰረተ ልማት ችግሮችን በአግባቡ በመፍታት ከተማዋን ለማስተዳደር አሁን እየተከናወኑ የሚገኙት የኮሪደር ልማት ስራዎች እነዚህን ያካተቱ መፍትሔዎች ይዞ የመጣ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የኮሪደር ልማቱ የእግረኛ መንገድ ችግር መፍታት፣ ለብስክሌት መሄጃ የሚሆን መንገድ መገንባት፣ ሰፊ የእግረኛ መንገድና መናፈሻ ስፍራዎችን ማዘጋጀት፣ ታክሲዎችና አውቶቡሶች የሚጭኑና የሚያወርዱባቸውን ተርሚናሎች ማሟላት፣ አጠቃላይ የከተማዋን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠን የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶችን የመገንባት የጎላ ሚና እንዳለውም አስረድተዋል።

በአንዳንድ የከተማዋ ክፍሎች የመብራት ኃይል መሰረተ ልማት እንዲሁም የቴሌኮም ኬብሎች በአግባቡ አለመዘርጋታቸውን ጠቅሰው፣ በኮሪደር ልማቱ እነዚህ ችግሮች በአግባቡ እየተቀረፉ መሆናቸውንም ይጠቁማሉ። እነዚህም ድምር ስራዎች የከተማ ነዋሪ ህይወት ለማሻሻል ወሳኝ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከተሞች ሲመሰረቱ የወደፊቱን ትውልድ ታሳቢ አድርገው እና በአግባቡ ታቅደው መሆን እንዳለበት አመልክተው፣ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መሰረተ ልማት እየተሟላላቸው ማደግ እንደሚገባቸው አስታውቀዋል።

ከተሞች ተገቢ የመሰረተ ልማት እየተሟሉላቸው የማያድጉ ከሆነ አሁን የሚታዩት አይነት ችግሮች መከሰታቸው እንዳማይቀር አስገንዝበው፣ በተለይ የመንገድ መሰረተ ልማት ዋነኛው መከናወን ያለበት መሆኑን ይገልጻሉ። የኤሌክትሪክ፣ የፍሳሽ እና የመሳሰሉት መሰረተ ልማቶችም መንገድን ተከትለው የሚሄዱ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ አንድን ከተማ ከተማ የሚያሰኘው መንገድ በሚፈለገው ደረጃ ሲገነባ ነው ይላሉ።

አሁን መንግሥት ይሄንን ለማስተካከል ሲመጣ የከተማ ልማት የህዝብ መሆኑንና ለሚቀጥለው ትውልድ የሚሰራ ስራ መሆኑን ማወያየት፣ ህዝቡም ተሳትፎ በማድረግ እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል ሲሉም አስገንዝበዋል። ከዚህ አኳያ ግንዛቤ መፍጠር ላይ በስፋት መስራት አለበት ሲሉም ተናግረው፣ ህዝቡ ስራው የኔ ነው ብሎ ከተቀበለ መሰረተ ልማቱ ቀጣይነት እንደሚኖረውም አመላክተዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ተመራማሪው እንዳስታወቁት፤ በኮሪደር ልማቱ እንደ አዲስ እየተሰራች ያለችው አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በሌሎች ከተሞች እየተከናወኑ ያሉ የከተሞች ልማት ስራዎች በሀገሪቱ የከተማን ደረጃ የሚያሳድጉ ስራዎች በስፋት እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ማሳያ ይሆናሉ። ይህም ለከተሞቹ ነዋሪዎች ምቹ የመኖሪያ፣ የስራና የመሳሰሉትን አካባቢዎችን መፍጠር ያስችላል።

ስማርት ከተማ ሲገነባ ቱሩፋቶችን ይዞ እንደሚመጣ

**«በገጠር እና በከተማ ያለው ትስስር በተቀናጀ መልኩ ከተመራ፣ ከተሞቻችን እንዲመሩን ሳይሆን እኛ ወደ ምንፈልገው ደረጃ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ከተሞቻችንን መምራትና ማሳደግ እንችላለን»**

ገልጸው፤ ለአብነትም በከተሞች የሚሰሩ አረንጓዴ የውበት ስራዎችን ጠቅሰዋል። ይህ ልማት በሰው ሕይወት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል፣ መንፈስን ያድሳል፤ በእግር ለመንቀሳቀስ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤ የትራፊክ መጨናነቅን ይቀንሳል፤ በእግር መሄድ ለጤና ያለውን ሚና ያሳድጋል ሲሉ አብራርተዋል።

አቶ ተፈሪ እንዳሉት፤ የኮሪደር ልማቱ መከናወን ወይም በአካባቢው አስፈላጊው የመሰረተ ልማት መዘርጋቱ ቱሩፋቱ ብዙ ነው። ከቱሩፋቶቹ መካከል የአካባቢው የመሬት ዋጋ በዚያው ልክ የሚያድግ መሆኑ ይጠቀሳል፤ የአካባቢው ውበት ይጨምራል። የውበቱ መጨመር ለኢኮኖሚው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

የኮሪደር ልማቱ ዋነኛ ዓላማ የማህበረሰቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ነው። ሰው የተሻለ ተስፋ ማድረግ እንዲችል፣ በሀገሩ በዚህ መልኩ ማደግ እንደሚችል እንዲረዳ፣ መጪው ትውልድ የተሻለ አካባቢ እያየ ራእይ እንዲኖረው ያደርጋል። የኮሪደር ልማት በተሰራባቸው አካባቢዎች የሚታየው የሰዎች እንቅስቃሴ እና የመዝናናት ሁኔታም ለቱሪዝም ዘርፉ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የውጭ ቱሪስቱ ለጉብኝት እንዲመጣ በመስህብነት ያገለግላል። የአካባቢንና የከተማን ደረጃ ለመቀየር የጎላ አበርክቶ አለው።

ከዚህም በተጨማሪ በአዲስ አበባ የተገነባው የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ሲታይ በተያዘው ሳምንት ጭምር ከፍተኛ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች እየተካሄደበት መሆኑን አንስተው፣ የሀገሪቱ ዓለም አቀፍ ስብሰባ የማስተናገድ አቅም ላይ የራሱን ጉልህ ሚና እየተጫወተ መሆኑንም ይገልጻሉ፡፡ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን የማስተናገድ አቅም መጨመሩ ሌሎች በከተማዋ እና በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ የመናፈሻ ፓርኮችንም ለማስጎብኘት እድል ይፈጥራል ሲሉ አብራርተዋል።

በምሽት ላይ የሚታየው የከተማዋ ውበት ከቀደመው አኳያ ሲታይ የተለየ ስሜትን እንደሚያጭርም ተናግረው፤ የኮሪደር ልማቱ ለሀገሪቱና ለነዋሪው ምቹ ማድረግ እንደሚቻል ማሳያዎች መሆናቸውን አስታውቀዋል። የኮሪደር ልማቱ የሀገር ውስጥ ሀብትን በማንቀሳቀስ መንግስትና ባለሀብቱን በማስተባበር ሀገርን መለወጥ እንደሚቻል ያመላከተ የልማት ስትራቴጂ መሆኑን ያስረዳሉ።

በቀጣይ አይቀሬ በሆነው የከተሜነት መስፋፋት እያደገ የሚመጣውን የህዝብ ቁጥር ማስተናገድ የሚችልበት ሁኔታ አስቀድሞ መፍጠር ይገባል ያሉት አቶ ተፈሪ፣ ከተሞች አስፈላጊውን መሰረተ ልማት አሟልተው እንዲገነቡ ለማድረግ በእቅድ መመራት ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል። ለዚህም ከወዲሁ በመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ላይ መሰራት እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡

‹‹ዋነኛው የሀገራችን ከተሞች ችግር ከተማ እየቀደመ እኛ እየተከተልን መሆኑ ነው›› የሚሉት አቶ ተፈሪ፤ ቀድሞ አስቦ ከተማን መምራት እንደሚገባ አመልክተዋል። ከዚህ በፊት የነበረውን ምላሽ የመስጠት አካሄድ እንደነበር ጠቅሰው፣ ከተማ ከሄደ በኋላ በህገወጥነት ወደጎንዮሽ እየተስፋፋ ሲሄድ እየተከተልን ከተማ ስንል ቆይተናል ብለዋል።

አሁን ግን በከተማና ገጠር ትስስር እንዲሁም በመሬት አጠቃቀም ላይ በመስራት የትኛው አካባቢ ለየትኛው መዋል እንደሚገባው በመለየት ቀድሞ በማቀድ ከተማ መመራት እንዳለበት ተናግረዋል። ከተማ በእዚህ መልኩ የሚመራ ከሆነ ከተሞችን በሚፈለገው መልኩ ማሳደግ ይቻላል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ከተማ ዞሮ ዞሮ ወደ ገጠር የሚስፋፋ መሆኑን ጠቅሰው፣ ቀድመን ገጠርን የምንሰራ ከሆነ ፤ ሰዎች መንገድ ዳር መጥተው እንዳይሰፍሩ ማድረግ እንችላለን ብለዋል። ገጠሩን በእቅድ የምንመራው ከሆነ እና በገጠር እና በከተማ ያለው ትስስር በተቀናጀ መልኩ ከተመራ፣ ከተሞቻችን እንዲመሩን ሳይሆን እኛ ወደ ምንፈልገው ደረጃ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ከተሞቻችንን መምራትና ማሳደግ እንችላለን›› ሲሉ አቶ ተፈራ ተናግረዋል።

አሁን በኮሪደር ልማቱ የሚታዩ ማስተካከያዎች እና ከተማን እንደገና የማደስ ስራዎች አቅዶ ባለመስራት የተፈጠሩ ችግሮች የሚፈቱበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ከተሞቻችን በእቅድ እና በእቅድ ብቻ እንዲመሩ ማድረግ ይገባል ብለዋል። ቀድሞ ማቀድን መከተል ከተቻለ በቀጣይ ሊከሰቱ የሚችሉ የመሰረተ ልማት ችግሮችንም አስቀድሞ መፍታት እንደሚቻል አቶ ተፈሪ አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በሀገሪቱ እንደ ችግር የሚታየው የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ አለመኖሩ ነው። የትኛው አካባቢ ለየትኛው መዋል እንዳለበት የሚያሳይ ለቤት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለኮመርሻል፣ ለማኑፋክቸሪንግ፣ ለአረንጓዴ ስፍራዎች የሚለውን ቀድሞ ማቀድ እና ማስተዳደር ያስፈልጋል። አረንጓዴ ስፍራዎች የከተማ ሳምባ በመሆናቸው በእቅድ መቀመጥ ይኖርባቸዋል። ሁሉም አካባቢ በፎቅ የሚሞላ ከሆነ፤ ከተማ ሳምባ ያጣል፤ በመሆኑም አረንጓዴ ስፍራዎችንም ጭምር ማቀድ ይገባል።

ለአሁኑ ለሀገሪቱ የሚያስፈልገውን የከተማ ደረጃ ለማምጣት የኮሪደር ልማት ተጀምሯል። የህዝብ ቁጥሩ እየሰፋና እያደገ በመሆኑ አሁን ባለንበት የከተማ ደረጃ መቀጠል ስለማይቻል የኮሪደር ልማቱ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ይገባል ሲሉም አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከገጠር ወደ ከተማ ከፍተኛ ፍልሰት ይታያል። ይህንንም ችግር ለመቀነስ በእያንዳንዱ ከተማ ላይ መስራት ያስፈልጋል። ለምሳሌ በመዲናዋ የሚታየው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር በእያንዳንዱ ከተማ አስፈላጊ መሰረተ ልማት በመገንባት ለኢኮኖሚያዊ ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር ፍልሰቱ ሚዛናዊ እየሆነ ይሄዳል። የተመጣጠነ የከተማ እድገት ማምጣት ያሻል።

የገጠር እና የከተማ ትስስርን ማጠናከርም ያስፈልጋል ያሉት አቶ ተፈራ፤ አሁን ባለው ሁኔታ ቀድመው ባደጉ ከተሞች የኮሪደር ልማት ማካሄዱ አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ለዚህም ቀጣይነት ያለው ውይይት ማድረግ ላይ ሊሰራ እንደሚገባም ጠቅሰው፤፡ የህብረተሰቡን ድጋፍ ለማስቀጠል በልማቱ የተገኙ ውጤቶችን ለህብረተሰቡ ማስገንዘብ ተገቢ መሆኑን አንስተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ባለፈው ሳምንት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት ተገቢው የመሰረተ ልማት ሥራ በከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠር አካባቢዎችም ጭምር መካሄድ አለበት። መሰረተ ልማቱ አርሶ አደሩንም ታሳቢ ሊያደርግ እንደሚገባ ጠቅሰው፣ በገጠር አካባቢ መንገድ ዳር የሚሰፍረው አርሶ አደር ምርቱን ለገበያ ማቅረብ የሚችልበት ምቹ መሰረተ ልማት እንዲኖረው ማድረግ እንደሚያስፈልግም አስታውቀዋል።

# ስፖርት





# የንግድ ባንክ ሴቶች የመጀመሪያ የአፍሪካ ቻምፒዮንስ ሊግ ጨዋታ

**ዓለማየሁ ግዛው**

በ2024 የአፍሪካ ሴት ክለቦች ቻምፒዮንስ ሊግ ውድድር ተሳታፊ የሆነው ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመጀመሪያ ጨዋታውን ነገ ከናይጄሪያው ኤዶ ኩዊንስ ጋር ያደርጋል። ክለቡ በሳምንቱ አጋማሽ የሀገር ቤት ዝግጅቱን በማጠናቀቅ 21 ተጫዋቾችን አካቶ ወደ ውድድሩ ስፍራ አቅንቷል፡፡

የካፍ ሴቶች ቻምፒዮንስ ሊግ ዘንድሮ ለአራተኛ ጊዜ በሞሮኮ ካዛብላንካና እንዲሁም ከዚህች ከተማ በ96 ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ በምትገኘው ኤል ጃዲዳ የወደብ ከተማ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ኅዳር 14/2017 ዓ.ም ይካሄዳል። የኢትዮጵያ ተወካዩ ንግድ ባንክ በታሪኩ የመጀመሪያ ተሳትፎውንና የመጀመሪያ ጨዋታውን የሚያደርግ ይሆናል። ውድድሮቹ በላርቢ ዛኦዩሊ ስታድየም ካዛብላንካ እና ቤን ኤም መሀመድ ኤል- አዳዲ ስታድየም ይካሄዳሉ፡፡

ንግድ ባንክ ባለፈው ነሐሴ ወር በኢትዮጵያ የተካሄደውን የምሥራቅ አፍሪካ ዞን የካፍ ሴቶች ቻምፒዮንስ ሊግ ማጣሪ ውድድርን በማሸነፍ የመጀመሪያ የመድረኩን ተሳትፎ ማረጋገጡ የሚታወስ ነው። በቻምፒዮንስ ሊጉ ከየዞኑ ቻምፒዮን የሆኑ ስድስት ቡድኖችንና የአዘጋጅ ሀገር አንድ ክለብ እንዲሁም የአምና የመድረኩ ቻምፒዮን ክለብን ጨምሮ ስምንት ክለቦች ይፎካከራሉ፡፡

ስምንቱ ክለቦች በሁለት ምድቦች ተከፍለው በሚያካሂዱት አህጉራዊ ውድድር ንግድ ባንክ የመጀመሪያውን የምድብ ማጣሪያ ጨዋታውን ነገ ምሽት 2 ሰዓት ከናይጄሪያው ኤዶ ክዊንስ ክለብ በማድረግ ይጀምራል። በምድብ ሁለት ከጠንካራ የአህጉሪቱ ክለቦች የተደለደለው ንግድ ባንክ ከናይጄሪያው ክለብ ጋር የሚያደርገው ፍልሚያ ተጠባቂ ነው። ውድድሩ ዛሬ በምድብ አንድ በሚካሄዱ ሁለት ጨዋታዎች የሚጀምር ሲሆን፤ ነገም እንዲሁ ሁለት ጨዋታዎችን በማድረግ ይቀጥላል። የዲሞክራቲክ ኮንጎው ቲፒ ማዜምቤ ከደቡብ አፍሪካው ዩደብሊዩሲ ክለብ እና የሞሮኮው ኤኤስ ፋር ከሴኔጋሉ ኢግልስ ዴ ላ መዲና ክለብ የዛሬ ጨዋታዎች ሲሆኑ፣ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ ናይጄሪያው ኤዶ ክዊንስ እና ማሜሎዲ ሰንዳወንስ ከኤፍ ማሳር ነገ የሚካሄዱ ጨዋታዎች ናቸው።



ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በካፍ የሴቶች ቻምፒዮንስ ሊግ የመጀመሪያ ጨዋታውን ያደርጋል፣

ንግድ ባንክ በሀገር ቤት ረዘም ያለ ዝግጅት በማድረግ ከቀናት በፊት ወደ ውድድሩ ስፍራ ያቀና ሲሆን 21 ተጫዋቾችን በስብስቡ ማካተት ችሏል። የምድቡን ሁለተኛ ጨዋታ ከጠንካራውና የአምና አሸናፊው ማሜሎዲ ሰንዳወንስ በመጪው ሃሙስ ያደርጋል ተብሎም ይጠበቃል። ሶስተኛውን እና የምድቡን የመጨረሻ ጨዋታ የነገ ሳምንት ከግብፁ ክለብ ማሳር ጋር የሚያደርግም ይሆናል፡፡

የቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ብርሃኑ ግዛው፣ ከአፍሪካ ምርጥ የሴት ቡድኖች ጋር የሚደረገው ውድድር ከባድና ፈታኝ እንደሆነና ውድድሩ ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ በመምጣቱ ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ከካፍ አላይን ድረ-ገጽ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ አስተያየት ሰጥተዋል። የአፍሪካ እግር ኳስ ቡድኖች ጠንካሮች እንዲሁም ጎል ለማስቆጠር ረጃጅም ኳሶችን የሚጠቀሙ በመሆኑ፣ ኳስን መሰረት ያደረግ አጨዋወትን ይዞ እንደሚገቡ ተናግረዋል፡፡

በውድድሩ የሚሳተፉ 8ቱ የሴት ክለቦች እያንዳንዳቸው 150 ሺ ዶላርን የሚያገኙ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሁ በተሳትፎ ብቻ ይህን ገንዘብ ወደ ካዝናው የሚያስገባ ይሆናል። የካፍ የሴቶች ቻምፒዮንስ ሊግ ውድድር እኤአ በ2021 የተጀመረ ሲሆን፤ አሁን የሽልማት ገንዘብ መጠኑን 52 በመቶ በማሳደግ ወደ 2 ሚሊዮን 350 ሺ ዶላር ከፍ ማድረጉ ተገልጿል። የውድድሩ አሸናፊ ክለብ 600 ሺ የአሜሪካን ዶላር ሲበረከት ይሄ በአፍሪካ የሴቶች እግር ኳስን ለማሳደግ እና የካፍ ውድድሮች የሽልማት ገንዘብን በመጨመር ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ እንደሆነ ተመላክቷል። በዚህም 2 ኛ ደረጃ ይዞ የሚያጠናቅቅ የሴት ክለብ 400 ሺ ዶላር፣ 3ኛ ደረጃ 350 ሺ ዶላር፣ 4ኛ ደረጃ 300 ሺ ዶላር፤ የምድብ 3ኛ 200 ሺ ዶላር እና የምድብ 4 ኛ ክለብ 150 ሺ ዶላር ያገኛል፡፡

በውድድሩ የሴካፋ ቻምፒዮኑ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ጨምሮ የወቅቱ የውድድሩ አሸናፊ ማሜሎዲ ሰንዳውንስ፣ ኤዶ ኩዊንስ እና ኤፍሲ ማሳር በምድብ ሁለት የተደለደሉ ሲሆን፣ ቲፒ ማዜምቤ፣ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዌስተርን ኬፕ፣ ኤግልስ ዴ ላ መዲና እና ኤ ኤስ ፋር በምድብ አንድ የተደለደሉ ክለቦች ናቸው። ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ በሁለት አጋጣሚዎች ውድድሩን ያሸነፉት ማሜሎዲ ሰንዳውንስ እና የአዘጋጅዋ ሀገር ክለብ የሆነው እንዲሁም ከዚህ ቀደም ውድድሩን ያሸነፉት ኤ ኤስ ፋር ለአሸናፊነት ቅድመ ግምት ያገኙ ክለቦች ሆነዋል።